፳፩) በቱሪዝም መስዕቦች አካባቢ የሚገኘው ህብረተሰብ በቱሪዝም አገልግሎት ልማት ላይ በመሣታፊ ተጠቃሚ እንዲሆን ሁኔታን ያመቻቻል፣ ይደግፋል፤
፳፪) የቱሪስት መዳረሻና የታሪክ ቅርሶች ያሉባቸው ቦታዎች መሠረተ ልማቶችና የቱሪስት አገልግሎት ፋሲሊቲዎች እንዲዘረጉ ያደርጋል፣ ከግቡ እንዲደርስም ከሚመለከተው አካል ጋር ይሠራል፤
፳፫) የክልሉ የባህልና ቱሪዝም ሐብት በአገር ውስጥና በውጭ አገር እንዲታወቅ ከሚመለከተው አካል ጋር ይሠራል፤
፳፬) የባህልና የተፈጥሮ የቱሪዝም መስዕብ ሐብት እንዲጠበቅ የግንዛቤ መዳበሪያ ሥራ ይሠራል፣ ያለውን የመልማት ዕድል ያስተዋውቃል፣ የቱሪዝም ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋ ከሚመለከተው አካል ጋር ይሠራል ፤
፳፭) የባህልና ቱሪዝም ተቋማት ልማትን አስመልክቶ የቀረቡ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን ይገመግማል፣ ሙያዊ ሐሣብ ለሚመለከተው አካል ያስተላልፋል፣ ሙያዊ ድጋፍ ይሠጣል፣ ሥራቸውን ይከታተላል፤
፳፮) ዋጋቸው በተለየ ሁኔታ ሊወሰን የሚገባቸው የቱሪዝም መስዕቦች፣ የጉብኝት ገቢና ዋጋቸውን አስመልክቶ ሐሣቡን ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፣ ሲፀድቅም ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

**፴፪. የእንስሣትና ዓሣ ሀብት ልማት ቢሮ**

ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩) የእንስሣት ልማት ኤክስቴንሽን አገልግሎት ለአርሶ አደሮችና አርብቶ አደሮች ይሠጣል፣ የማዳበሪያና ብድር አቅርቦት ሁኔታን ያመቻቻል፤



20) Set criteria regarding the service delivery of Culture and Tourism institutions; issue professional license; renew; cancel; provide trainings in collaboration with concerned bodies; provide professional support; control; provide levels in collaboration with other bodies.
21) Facilitate conditions to make the population residing around the tourist attractions to participate on the tourism development activities and be beneficiary from same; give support;
22) Cause the expansion of developmental infrastructures and tourist service facilities at the tourist destinations and where there are historical heritages; work with the concerned body for the attainment of its goals.
23) Work with the concerned body to make the resources of culture and tourism of the region be known in the country and abroad;
24) Conduct awareness raising activities for the protection of the cultural and natural resources of tourist attractions; promote the existing development opportunities; work with the concerned body for the expansion of tourism investment;
25) Evaluate the investment projects submitted on the development of culture and tourism institutions; forward professional recommendations for the concerned body; provide professional support; follow up their activities;
26) Propose opinion to the concerned body regarding the income and tour fee of the tourist attractions the price of which shall be decided differently; cause its implementation up on approval;

**32. Livestock and Fisheries Development Bureau.**

The Bureau shall have the following powers and duties:

1) Provide livestock development extension service for the farmers and pastoralists; facilitate conditions for the supply of fertilizers and loans;

2) Sanyii beeyiladaa naannichaa ni fooyyessa; ni eega; ni too'ata;
3) Qabeenya bishaan uumamamaa fi nam-tolcheetti fayyadamuun qabeenya qurxummii ni misoomsa; ni deeggara; ni too'ata;
4) Misooma nyaata beeyiladaa ni gaggeessa; lafti dheedumsaaf daangeffame akka fooyya'uu fi eegamu ni hojjata;
5) Bakka hanqinni bishaan dhugaatii beeyiladaa jirutti argama bishaanii ni qorachiisa; qaama dhimmi ilaalu waliin ni misoomsa;
6) Teeknolojiiwwan misooma beeyiladaa biyya keessaasatti qoratamanii fi biyya alaatii galuun madaqan, bu'a qabeessumaan isaaniis mirkanaa'e ni babal'isa; hojiirra oolmaa isaanii ni too'ata; akkasumas fedhii fi rakkoolee gama misooma beeyiladaatiin hawaasa keessatti mul'atan akka qorataman qaama dhimmi ilaalu waliin ni hojjata;
7) Hojiiwwan misoomaa fi eegumsa fayyaa beeyiladaa naannicha keessatti ni babal'isa; ni deeggara; ni hordofa; ni too'ata;
8) Dhukkuboota beeyiladaa daddarboo biyyarraa biyyatti, naannoorraa naannootti darban qaama dhimmi ilaalu waliin ni sakatta'a; ni ittisa; ni too'ata; sochii beeyiladaa ni dhorka; barbachisaa ta'ee yoo argame beeyilada dhukkubaan faalamanii hawaas-diinagdee irratti miidhaa geessisuu danda'an ni maqsa;
9) Manneen qalmaa keessatti foon dhukkuba irraa bilisa ta'ee hawaasaaf akka dhiyaatu qorannoo qalma duraa fi boodaa ni gaggeessa; qalma seeraan ala gaggeeffamu qaama dhimmi ilaalu waliin ni too'ata; tarkaanfii seeraa ni fudhata;
10) Ulaagaalee manneen qalmaa naannichaa ni qopheessa; waraqaa ragaa gahumsaa ni kenna; ni haaromsa; ni haqa;
11) Naannicha keessatti dhukkuba daddarbaa fi manca'iinsa sanyii beeyiladaa too'achuudhaaf sochii beeyiladaa ni too'ata; kallattiin sochii beeyiladaa seeraan akka beekamu ni hojjata; wirtuuwwan kuwaaraantayinii fi sakatta'iinsaa ni hundeessa; ni gurmeessa; ni hordofa; ni too'ata;

፪) የክልሉን የእንስሳት ዝሪያ ያሻሽላል፣ ይጠብቃል፣ ይቆጣጠራል፤
፫) የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ የውሀ ሐብትን በመጠቀም የዓሣ ሐብት ያለማል፣ ይደግፋል፣ ይቆጣጠራል፤
፬) የእንስሣት መኖ ልማት ያካሔዳል፤ ለግጦሽ የተከለለ መሬት እንዲሻሻልና እንዲጠበቅ ይሠራል፤
፭) የእንስሣት መጠጥ ውሀ እጥረት ባለበት ሥፍራ የውሀ ማግኛ ያስጠናል፣ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን ያለማል፤
፮) በአገር ውስጥ የተጠኑና ከውጭ አገር በመግባት የተላመዱ፣ ውጤታማነታቸውም የተረጋገጡ የእንስሣት ልማት ቴክኖሎጂዎችን ያስፋፋል፣ ሥራ ላይ መዋላቸውን ይቆጣጠራል፣ እንዲሁም በህብረተሰቡ ውስጥ የሚታዩ የእንስሣት ልማት ፍላጎትና ችግሮች እንዲጠኑ ከሚመለከተው አካል ጋር ይሠራል፤
፯) የእንስሣት ልማትና ጤንነት ሥራዎች በክልሉ ውስጥ ያስፋፋል፣ ይደግፋል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤
፰) ከአገር ወደ አገር ከክልል ወደ ክልል የሚተላለፉ የእንስሳት በሽታዎችን ከሚመለከተው አካል ጋር ይፈትሻል፣ ይከላከላል፣ ይቆጣጠራል፣ የእንስሣት እንቅስቃሴን ይከለክላል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በበሽታ የተበከሉና በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት ላይ ጉዳት ሊያደርሱ የሚችሉ እንስሣትን ያስወግዳል፤
፱) በእርድ ቤቶች ዉስጥ ከበሽታ ነፃ የሆነ ሥጋ ለህብረተሠቡ እንዲቀርብ ከእርድ በፊትና በኃላ ምርመራ ያካሄዳል፤ በህገ ወጥ መንገድ የሚካሔድ እርድን ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን ይቆጣጠራል፤ ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል፤
፲) የክልሉን የዕርድ ቤቶች መስፈርቶችን ያዘጋጃል፤ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሠጣል፤ያድሣል፣ ይሠርዛል፤
፲፩) በክልሉ ውስጥ የተላላፊ በሽታና የእንስሳት ዝርያ ጥፋት ለመቆጣጠር የእንስሣት እንቅስቃሴን ይቆጣጠራል፣ የእንስሣት እንቅስቃሴ አቅጣጫ በህግ የታወቀ እንዲሆን ይሠራል፣ የኳራንታይን እና ፍተሻ መዕከሎችን ያቋቁማል፣ ያደራጃል፣ ይከታተላል ፣ ይቆጣጠራል፤

2) Improve the livestock species of the region; protect; supervise same;
3) Develop fish resources using the natural and man-made water resources; support; supervise;
4) Undertake live stocks forage development; work for the improvements and protection of the land enclosed for grazing;
5) Cause the conduct of surveys in search of water where there exists scarcity of potable water for the livestock; develop in collaboration with concerned body;
6) Expand the live stocks development technologies innovated in the country and adopted abroad whose effectiveness is approved; control their implementation and work with the concerned body for the demands and problems prevailing in the society in relation with live stocks development to be studied;
7) Expand the development and live stocks health protection activities in the region; support; follow-up and supervise;
8) Search; prevent; control communicable livestock's diseases transmitted from country to country and from region to region in collaboration with the concerned body; limit the movement of live stocks; where found necessary, it disposes away the live stocks contaminated with diseases which may cause socio-economic disasters;
9) Conduct pre and post slaughtering investigations so as to serve disease free meat product for the society in the slaughter houses; control the illegal slaughtering activities in collaboration with the concerned body; take legal measures on the same.
10) Set criteria for slaughter houses of the region; provide competency certificate; renew; cancel same;
11) Control livestock mobility so as to overcome communicable diseases and destruction of livestock species; work for the direction of movement of livestock to be legally known; Establish quarantine and searching stations; organizes; follow- up; supervise;

12) Nageenya beeyiladaa (animal welfare) akka eegamu ni taasisa; ni too'ata;
13) Daldala callaa guddistuu gosa adda addaa, qorichaa fi farra maxxantuu qaama alaa beeyiladaa seeran ala ta'an ni too'ata; qaama dhimmi ilaalu waliin tarkaanfii seeraa ni fudhata; kan yeroon tajaajilaa itti darbe akka maqfamu ni taasiisa;
14) Beeyiladaa fi bu'aa beeyiladaa gabaa biyya keessaa fi biyya alaaf ta'an qulqullinaa fi baay'ina gabaan barbaaduun akka omishamu ni hojjata; sadarkaa qulqullinaa fi gahumsaa bahe hojiirra ni oolcha; waraqaa ragaa qulqullinaa fi gahumsaa ni kenna; ni haaromsa; ni haqa; ni too'ata;
15) Oomishitoota, dhiyeesitootaa fi itti fayyadamtoota beeyiladaa fi bu'aa beeyiladaatiif deeggarsa ogummaa ni kenna; gahumsaa fi qulqullina oomishaa ni hordofa; ni too'ata;
16) Misooma qabeenya kanniisaa fi bu'aalee qabeenya kanniisaa kan dammaa fi gagaa karaa bu'aa qabeessa ta'een akka gaggeeffamu ni hojjata; ni deeggara; ni hordofa; ni too'ata;
17) Abbootii qabeenya dhuunfaa naannicha keessatti hojiiwwan misoomaa fi eegumsa fayyaa beeyiladaa irratti bobba'aniif ulaagaa ni qopheessa; waraqaa ragaa gahumsaa ni kenna; ni deeggara; ni hordofa; gahumsaa fi qulqullina hojichaas ni too'ata;
18) Bu'uuraalee misoomaa fi eegumsa fayyaa beeyiladaa kan akka giddugaleessota teeknolojiiwwan beeyiladaa baay'isanii fi oomishan, giddugaleessota laboratorii fi kilinikoota eegumsa fayyaa beeyiladaa ta'an ni hundeessa; ni gurmeessa; ni bulcha; ni too'ata.

**33. Biiroo Dhimma Hojjataa fi Hawaasummaa**

Biiroon kun aangoo fi hojii armaan gadiitti tarreefaman ni qabaata:

1) Imaammataa fi tarsiimoo dhimma hawaasummaa akkasumas, seerota dhimma hojjataa fi hojjachiisaa ilaalchisee bahan hojiirra ni oolcha; hojiirra akka oolu ni taasisa; ni too'ata; qaama seera darbee argame irratti tarkaanfii sirreeffamaa ni fudhata; akka fudhatamu ni taasisa;

፲፪) የእንስሳት ደህንነት እንዲጠበቅ ያደርጋል፣ ይቆጣጠራል፣

፲፫) ህገወጥ የሆኑ የተለያዩ አይነት የማዳበሪያ፣ የመድሀኒትና የከብቶች ውጫዊ አካል ተዋስያን ማጥፊያ ንግድን ይቆጣጠራል፤ ጉዳዩ ከሚመለከተዉ አካል ጋር ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል፤ የአገልግሎት ጊዜያቸው ያለፈባቸውን እንዲወገዱ ያደርጋል፤

፲፬) ለአገር ውስጥና ለውጭ አገር ገበያ የሚሆኑ እንስሳትና የእንስሳት ተዋፅዖዎች ገበያው በሚፈልገው ጥራትና ብዛት እንዲመረቱ ይሠራል፣ የወጣውን የጥራትና የብቃት ደረጃ ሥራ ላይ ያውላል፣ የጥራትና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሠጣል፣ ያድሳል፣ ይሰርዛል፣ ይቆጣጠራል፤

፲፭) ለእንስሳትና ለእንስሳት ተዋፅኦ አምራቾች፤ አቅራቢዎችና ተጠቃሚዎች የሙያ ድጋፍ ይሰጣል፣ የምርቱን ብቃትና ጥራት ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

፲፮) የንብ ሀብት ልማትና ውጤቶች የሆኑት ማርና ሰም ውጤታማ በሆነ መንገድ እንዲካሄድ ይሰራል፣ ይደግፋል፤ ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

፲፯) በክልሉ ውስጥ በእንስሳት ልማትና ጤና ጥበቃ ሥራዎች ላይ ለተሰማሩ የግል ባለ ሀብቶች መስፈርት ያዘጋጃል፤ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሠጣል፣ ይደግፋል፣ ይከታተላል፣ የሥራውን ብቃትና ጥራትም ይቆጣጠራል፤

፲፰) የእንስሳት መሰረተ ልማቶችና ጤና ጥበቃ እንደ እንስሰትን የሚያባዙና የሚያመርቱ ቴክኖሎጂዎች ማዕከላት፣ የእንስሳት ጤና ጥበቃ ላቦራቶሪና ክሊኒክ ማዕከላትን ያቋቁማል፣ ያደራጃል፣ ያስተዳድራል፣ ይቆጣጠራል፤

**፴፫. የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ**

ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩) የማህበራዊ ጉዳይ ፖሊሲና ስትራተጂ እንዲሁም የሠራተኛና አሠሪ ጉዳይን አስመልክቶ የወጡ ህጎችን ሥራ ላይ ያውላል፤ ሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤ ይቆጣጠራል፤ ህግን ተላልፎ የተገኘ አካል ላይ የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፤ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

12) Cause the protection of animal welfare; supervise same;
13) Control illegal trade of various fertilizers; medicines and anti-parasites of external bodies of live stocks; take legal measures in collaboration with the concerned body; cause the expired ones to be disposed;
14) Work for the live stocks and live-stock products to be delivered for the internal and external markets to be produced in quality and quantity that the market demands; enforce the quality and competency standard issued; issue the quality and compatibility standard certificate; renew; cancel; and supervise;
15) Provide professional support to the producers, suppliers, and consumers of live stocks and live stocks products; follow up the quality of their products; controls;
16) Work for the development of bees resources and outputs of bees resources like honey and its byproducts to be undertaken in an efficient manner; support; follow-up; supervise;
17) Set criteria for the private investors engaged in live stocks development and health protection in the region; provide competency certificate; support; follow-up; and supervise the efficiency and quality of the activity;
18) Establish, organize, administer and supervise the live stocks infrastructure development and health protection like live stocks multiplying and producing technology centers, livestock`s health laboratories and clinic centers.

**33. Labor and Social Affairs Bureau**

The Bureau shall have the following power and duties;

1) Implement the policies and strategies of social affairs and the laws issued regarding the employer and employees; cause their implementation; control; take rectifying measures on those who violate the laws; cause such measure to be taken;

2) Waldhabiinsi hojjataa fi hojjachiisaa gidduutti uumamu waliigalteen akka hiikamuu fi nageenyi industirii akka uumamu ni hojjata;
3) Hojjataa fi hojjachiisaan mirga waldaan gurmaa'uu fi waliigaltee gamtaa taasisuutti akka fayyadaman ni jajjabeessa; deeggarsa ni kenna;
4) Seerota dhimma hojjataa fi hojjachiisaa ilaalchisee bahan irratti qaama dhimmi ilaaluuf leenjii hubannoo cimsu qopheessee ni kenna; deeggarsaa fi gorsa barbaachisu ni kenna;
5) Waldaalee hojjataa fi hojjachiisaa ni galmeessa; ni hordofa; deeggarsa ogummaa ni kenna; waraqaa ragaa qaama seerummaa ni kenna; ni haaromsa; akka haqamu ni taasisa;
6) Waliigaltee gamtaa ni galmeessa; hojiirra ooluu isaa ni too'ata; deeggarsa ogummaa ni kenna;
7) Boordii murteessaa dhimma hojjataa fi hojjachiisaa naannoo baay'inaan jiranitti ni hundeessa; humna namaa barbaachisu ni ramada; ni bulcha; ni hordofa; ni too'ata;
8) Dhaabbilee misoomaa mootummaa fi dhuunfaa keessatti argamuun too'annaa haala hojii ni gaggeessa; tarkaanfii sirreeffamaa ni fudhata; akka fudhatamu ni taasisa;
9) Bu'uura haala hojii, fayyummaa, nagummaa, ogummaa fi naannoo hojii irratti qo'annoo ni gaggeessa; bu'aa argame hojiirra ni oolcha; hojiirra akka oolu ni taasisa;
10) Ragaalee industirii dhimma hojjataa fi hojjachiisaa ni sassaaba; ni qindeessa; ni xiinxala; dhaabbileef duubdeebii ni kenna; qaama dhimmi ilaaluuf ni gabaasa;
11) sadarkaa haala hojii ilaalchisee bahe hojiirra ooluu isaa ni hordofa; ni too'ata; tarkaanfii sirreeffamaa ni fudhata;
12) Haala qabeenya humna namaa naannichaa ni qorata; kan hojii irratti bobba'ee fi hin bobba'in addaan ni baasuun ni galmeessa; ni xiinxala; ni qindeessa; ragaa fi istaatistiksii ni qopheessa; qaama dhimmi ilaaluuf ni kenna;

፪) በሠራተኛና አሰሪ መካከል የሚፈጠር አለመግባባት በስምምነት እንዲፈታና የኢንዱስትሪ ደህንነት እንዲሰፍን ይሠራል፤
፫) አሰሪና ሠራተኛ በማህበር የመደራጀና የህብረት ሥምምነት የማድረግ መብትን እንዲጠቀሙ ያበረታታል፣ ድጋፍ ይሠጣል፤
፬) ሠራተኛና አሰሪን አስመልክቶ የወጡ ህጎች ላይ ለሚመለከተው አካል የግንዛቤ ማዳበሪያ ስልጠና አዘጋጅቶ ይሠጣል፣ አስፈላጊውን ድጋፍና ምክር ይሠጣል፤
፭) የሠራተኛና አሠሪ ማህበራትን ይመዘግባል፣ ይከታተላል፣ ሙያዊ ድጋፍ ይሠጣል፤ የህግ ሰውነት ማረጋገጫ የምስክር ውቀት ይሠጠል፤ ያድሣል፣እንዲሰረዝም ያደርጋል፤
፮) የህብረት ሥምምነትን ውል ይመዘግባል፤ ሥራ ላይ መዋሉን ይቆጣጠራል፣ የሙያ ድጋፍ ይሠጣል፤
፯) የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ አሰሪና ሰራተኞች በብዛት በሚገኙበት አካባቢ ያቋቁማል፣ አስፈላጊውን የሰው ሀይል ይመድባል፤ ያስተዳድራል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤
፰) በመንግስትና በግል የልማት ድርጅቶች ውስጥ በመገኘት የስራ ሁኔታ ቁጥጥር ያካሄዳል፣ የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፣ እንዲወሰድ ያደርጋል፤
፱) በሥራ መሠረታዊ ሁኔታ፤ ጤንነት፤ ደህንነት፤ ሙያና የሥራ አከባቢ ላይ ጥናት ያካሄዳል፤ የተገኘውን ውጤት ሥራ ላይ ያውላል፤ በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤
፲) የአሠሪና ሠራተኛ ኢንዱስትሪ መረጃዎችን ይሠበስባል፤ ያቀናጃል፣ ይገመግማል ለተቋማት ግብረ መልስ ይሠጣል፤ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ያደርጋል፤
፲፩) የሥራ ሁኔታ አስመልክቶ የወጣ ደረጃ ተግባር ላይ መዋሉን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ የማስተካከያ እርምጃ ይወስደል፤
፲፪) የክልሉን የሰው ሀይል ሀብት ሁኔታ ያጠናል፣ በሥራ ላይ የተሰማራውንና ያልተሰማራውን በመለየት ይመዘግባል፣ ይገመግማል፣ ያቀናጃል፣ ማስረጃና እስታቲስቲክስ ያዘጋጃል፣ ለሚመለከተው አካል ይሠጣል፤

2) Work for the peaceful settlement of the disputes which arise between the employee and employer for ensuring industrial peace;
3) Encourage and provide support for the employer and employee to exercise their rights to be organized in associations and collective agreements;
4) Prepare and provide awareness raising trainings to the concerned bodies about the newly issued laws regarding the employee and employer; provide necessary support and advices;
5) Register employee-employer associations; follow up; provide professional support; issue legal personality certificate; renew; cause to be cancelled;
6) Register collective agreements; supervise its implementation; and provide professional support;
7) Establish labor relations board of employer and employees affairs where there are greater number of organizations; assign the necessary human force; administer; follow up; control same;
8) Conduct work situation supervision appearing in the public and private enterprises; take corrective measures; cause such measures to be taken;
9) Undertake studies on work condition, health, peace, profession and work environments; implements the findings; cause its implementation;
10) Collect industrial evidences of employer employee affairs; Organize; reviews; provide feedback for the organizations, report to the concerned body;
11) Follow-up the implementation of work standards; supervise; and take corrective measures;
12) Undertake studies about the human resource situation of the region; identify and register the employed and unemployed ones; reviews; analyses; prepare evidences and statistics and submit to the concerned body;

13) Ragaa humna namaa gabaan barbaadu, ogummaa barbaadamu, fedhii fi iddoo hojii duwwaa jiru walitti ni qaba; adda ni baasa; ragaa fi odeeffannoo qindeessuun ni tamsaasa; hojii fi hojjataan akka walqunnaman ni taasisa;
14) Hojii barbaaddota naannicha keessatti qaxaramanii hojjachuu barbaadaniif bobba'iinsa hojii fi aadaa hojii irratti hubannoo ni kenna; ni gorsa; deeggarsa barbaachiisu ni taasisa;
15) Ejensii dhuunfaa hojii fi hojjataa naannicha keessatti walqunnamsiisuu barbaadaniif hayyama hojii ni kenna; ni haaromsa; ni hordofa; ni too'ata; ni ittisa; ni haqa;
16) Ejensii dhuunfaa hojii fi hojjataa walqunnamsiisuuf mootummaa Federaalaa irraa hayyama fudhatanii fi naannichatti hojjatan galmeessuun ni hordofa; ni too'ata; hayyama isaanii ni ittisa; bakka seeraan ala hojjatanii argamanitti qaama dhimmi ilaaluuf ni gabaasa;
17) Waliigaltee qaxarrii hojjataa fi hojjachiisaa gidduutti taasifamu ni mirkaneessa; ni galmeessa;
18) Waldhabiinsa hojjataa fi Ejensii dhuunfaa hojii fi hojjataa walqunnamsiisu gidduutti uumamu qaamolee lamaan walitti fiduun waltaasisa; deeggrsa ogummaa ni kenna;
19) Lammiilee gara biyya alaa deemanii hojjachuuf fedhii qabaniif haala biyya isaan simatuu, haala hojii irratti bobba'anii fi ogummaa qabaachuu qaban, haala mirgaa, itti gaafatamummaa fi dhimmoota kanaan wal fakkaatan irratti hubannoo bobba'iinsa duraa fi imala duraa idileedhaan ni kenna;
20) Gocha seeraan ala namoota naanneessuu fi ceesisuu, too'achuu fi ittisuuf leenjii hubannoo cimsu ni kenna; ni hordofa; ni too'ata; qaama dhimmi ilaalu waliin tarkaanfii sirreeffamaa ni fudhata; akka fudhatamu ni taasisa;
21) Maddoota godaansa seeraan alaa irratti qo'annoo ni gaggeessa; bu'aa qo'annichaa irratti hundaa'uudhaan tarsiimoo kallattii rakkoowwan muudatan ittiin hiikkaman akka bahu ni hojjata; qaama dhimmi ilaalu waliin hojiirra ni oolcha; akka hojiirra oolu ni taasisa;

፲፫) ገበያው የሚፈልገው የሰው ሀይል ማረጃ፣ የሚፈለገው ሙያ፣ ፍላጎትና ያለውን ክፍት የሥራ ቦታ ይሰበስባል፤ ይለያል፤ ማስረጃና መረጃ በማቀናጀት ያሰራጫል፤ ሥራና ሰራተኛ እንዲገናኝ ያደርጋል፤

፲፬) በክልሉ ውስጥ ተቀጥረው መስራት ለሚፈልጉ ሥራ ፈላጊዎች የሥራ ስምሪትና የሥራ ባህልን አስመልክቶ ግንዛቤ ይሠጣል፤ ይመክራል፣ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፤

፲፭) በክልሉ ውስጥ ለስራና ሠራተኛን ማገናኘት የሚፈልግ የግል ኤጀንሲ የሥራ ፍቃድ ይሰጣል፤ ያድሣል፤ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤ ያግዳል፤ ይሠርዛል፤

፲፮) ሥራና ሰራተኛን ለማገናኘት ከፌዴራል መንግስት ፍቃድ የወሰዱና በክልሉ ውስጥ የሚሰሩ የግል ኤጀንሲዎችን በመመዝገብ ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤ ፍቃዳቸውን ያግዳል፤ ከህግ ውጪ ሰርተው በሚገኙበት ጊዜም ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ያደርጋል፤

፲፯) በአሰሪና ሰራተኛ መካከል የሚደረግ የቅጥር ውል ያረጋግጣል፤ ይመዘግባል፤

፲፰) በሠራተኛና ሥራና ሠራተኛን አገናኝ የግል አጀንሲ መካከል የሚፈጠር አለመግባባት ሁለቱን አካላት በማገናኘት ያስማማል፣ የሙያ ድጋፍ ይሠጣል፤

፲፱) ወደ ውጪ አገር ሄደው መስራት ለሚፈልጉ ዜጎች ስለሚቀበላቸው አገር ሁኔታ፤ ስለሚሰማሩበት ሥራ ሁኔታና ሊኖራቸው ስለሚገባው ሙያ፣ ስለ መብት ሁኔታ፣ ስለ ሐላፊነትና እነዚህን በመሣሠሉ ጉዳዮች ላይ የቅድመ ስምሪትና የቅድመ ጉዞ ግንዛቤ ማስጨበጫ በመደበኛነት ይሠጣል፤

፳) ህገወጥ የሰዎች ዝውውርና ድንበር ማሻገር ድርጊትን ለመቆጣጠርና ለመከላከል የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና ይሠጣል፤ ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፣ ከሚመለከተው አካል ጋር የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፤ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

፳፩) በህገውጥ የሰዎች ዝውውር ምንጮች ላይ ጥናት ያካሄዳል፤ በጥናቱ ውጤት ላይ በመመስረት የገጠሙት ችግሮች የሚፈቱበት ስትራተጂ እንዲወጣ ይሠራል፣ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን ሥራ ላይ ያውላል፣ ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

13) Collect evidences of human resource that the market demands, the demanded profession; the demand and vacant positions; identify; organize the evidences and information and distribute ; perform the bringing together of the work and workers ;
14) Provide awareness for those who want to be employed and work in the region about work engagements and work culture; consult; provide necessary supports;
15) Issue licenses for the private agencies which are interested to engage in bringing the work and worker together in the region; renew the license; follow up; control; prevent; cancel;
16) Register; follow up; supervise; suspend the license of the private agencies that acquire the license of bringing the work and worker from the federal government and are working in the region; report to the concerned body where they are found working illegally;
17) Approve the employment contract made between the employee and employer; register same;
18) Resolve the dispute which arise between the employee and the agency bringing the work and worker by negotiating the two parties together; provide professional support;
19) Provide regular pre journey and pre job awareness raising training for the citizens who want to go to abroad in search of jobs about the country hosting them; the job in which they engage; and the profession expected from them; about their rights and responsibilities and other similar issues;
20) Provide awareness raising training; follows up, supervise to overcome and prevent the illegal human trafficking ; take corrective measures and cause same to be taken in collaboration with the concerned body;
21) Undertake studies on the causes of illegal evacuation; work on the strategies and directions of resolving the problems encountered to be devised depending on the findings of the study; implement same in collaboration with the concerned body; cause its implementation;

22) Rakkoolee jireenya hawaasummaa irratti qo'annoo ni gaggeesssa; bu'aa qo'annichaa irratti hundaa'uun tarsiimoo ittisaa ni qopheessa; hojiirra ni oolcha; hojjiirra ooluu isaa ni hordofa;
23) Ragaa dhimma nageenya hawaasummaa ni qindeessa; hojiirra ni oolcha; ni tamsaasa;
24) Hawaasi gumii wal-gargaarsa hawaasaa tiin gurmaa'ee duudhaa fi aadaa walgargaarsaa qabu akka gabbifatu; akkasumas Waldaaleen hawaasummaa fi walgargaarsaa akka gurmaa'an ni jajjabeessa; kan gurmaa'aniif hayyama ni kenna; ni haaromsa; ni haqa; hojii hawaasummaa fi misoomaa irratti akka hirmaatan ni barsiisa;
25) Hojjattoota guddina hawaasaa ni leenjisa; hojiitti ni bobbaasa; ni too'ata; deeggarsa ni kenna;
26) Mirgoota qaama miidhamtootaa, ittisa farra jireenya hawaasummaa fi kunuunsa manguddootaa ilaalchisee hawaasaaf leenjii hubannoo cimsu ni kenna; bu'aa isaa ni madaala;
27) Mirgaa fi faayidaan qaama miidhamtootaa akka eegamu ni hojjata; sagantaa raawwii hojii fi seerota dhimma kana irratti bahan hojiirra ni oolcha; deeggarsa ni kenna;
28) Nageenyi maatii akka eegamu gorsa gaa'elaa ni kenna; walitti dhufeenyii fi aadaan walgargaarsa maatii akka cimu deeggarsa ogummaa ni kenna; maatiin rakkoo hawaasummaatiif akka hin saaxilamne ni hojjata; kanneen harka qalleeyyii ta'an deeggarsa akka argatan haala ni mijeessa;
29) Maanguddootaa fi qaama miidhamtoota hirkoo fi deeggarsa hin qabne hawaasa keessatti tajaajila kunuunsaa fi haaromsaa akka argataniif haala ni mijeessa; deeggarsa ogummaa ni kenna; warra hawaasa keessatti deeggarsa argachuu hin dandeenyeef buufata keessatti akka kunuunsaman ni taasisa; buufataalee haaromsaa fi kunuunsaa ni bulcha; ni hordofa; humna namaa barbaachisu ni ramada; ni too'ata; deeggarsa ni kenna;

፳፪) በማህበራዊ ኖሮ ችግሮች ላይ ጥናት ያካሄዳል፣ በጥናቱ ግኝት ላይ በመመስረት የመከላከያ ስትራተጂ ያዘጋጃል፣ ሥራ ላይ ያውላል፣ ሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፤
፳፫) የማህበራዊ ደህንነት ጉዳይ ማስረጃ ያቀናጃል፣ ተግባር ላይ ያውላል፣ ያሰራጫል ፤
፳፬) ህብረተሰቡ በመረዳጃ አደረጃጀቶች ተደራጅቶ የመረዳዳት ወግና ባህል እንዲያዳብር እንዲሁም ማህበራዊና የመረዳጃ ማህበራት እንዲደራጁ ያበረታታል፤ለተደራጁት ፍቃድ ይሠጣል፤ ያድሳል፣ ይሰርዛል፣ በማሕበራዊና ልማት ሥራ ላይ እንዲሣተፉ ያስተምራል፤
፳፭) የህብረተሰብ እድገት ሠራተኞች ያሰለጥናል፤ ወደ ሥራ ያሰማራል፣ ይቆጣጠራል፤ ድጋፍ ይሠጣል፤
፳፮) የአካል ጉዳተኞች መብቶች፤ የማህበራዊ ኑሮ ጠንቆች መከላከልና የአረጋዊያን እንክብካቤን አስመልክቶ ለህብረተሰቡ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና ይሠጣል፤ ውጤቱን ይገመግማል፤
፳፯) የአካል ጉዳተኞች መብትና ጥቅም እንዲጠበቅ ይሰራል፤ የሥራ አፈፃፀም ፕሮግራምና በዚህ ጉዳይ ላይ የወጡ ህጎችን ሥራ ላይ ያውላል፤ ድጋፍ ይሠጣል፤
፳፰) የቤተሰብ ደህንነት እንዲጠበቅ የጋብቻ ምክር ይሠጣል፣ የቤተሰብ ግንኙነትና የመረዳዳት በህል እንዲጠናከር ሙያዊ ድጋፍ ይሠጣል፤ ቤተሰብ ለማህበራዊ ችግር እንዳይጋለጥ ይሠራል፤ የገንዘብ እጥረት ያለባቸው እርዳታ እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤
፳፱) ድጋፍና እርዳታ የሌላቸው አረጋዊያንና የአካል ጉዳተኞች በህብረተሰቡ ውስጥ የእንክብካቤና ተሀድሶ አገልግሎት እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤ የሙያ ድጋፍ ይሠጣል፤ በማህበረሰቡ ውስጥ ድጋፍ ማግኘት ለማይችሉ በማዕከሎች ውስጥ እንክብካቤ እንዲያገኙ ያደርጋል፣ የተሐድሶና እንክብከቤ ማዕከላትን ያስተዳድራል፣ ይከታተላል፣ የሚያስፈልገውን የሰው ሐይል ይመድባል፣ ይቆጣጠራል፣ ድጋፍ ያደርጋል፤

22) Conduct studies on the problems of social life; prepare preventive strategies depending on the findings of the study ; implement same; follow- up its implementation;
23) Organize evidences of social security; implement; distribute them.
24) Encourage the society to be organized in self- help social associations to enable them develop their self -helping norms and cultures; and the social self- supportive associations to be organized; issue license for the organized ones; renew; cancel same; educate them to participate on social and developmental activities;
25) Train social development workers; assign them on works; supervise and provide them support.
26) Provide awareness raising training to the public about the rights of disabled persons, prevention of anti-social lives and nurturing of elders; evaluates its outcome;
27) Work for the protection of the rights and benefits of persons with disabilities; implement the work performance programs and the laws enacted on this issue; provide support;
28) Provide consultancy services about marriage for the protection of family welfare; provide professional supports to promote the culture of integration and supportiveness of one another; work for the protection of the family from becoming vulnerable for social problems; facilitate conditions for the needy ones to get assistances.
29) Facilitate enabling conditions for the elders and disabled persons having no reliance and assistances to get protection or nurturing and rehabilitation services in the society; provide professional support; cause those who are unable to obtain assistances in the society to be nurtured in the centers; administer rehabilitation and nurturing centers; follows up; assign the necessary work force; supervise; provide supports;

30) Manguddoonni giddugala deeggarsaa fi bashannanaa akka argatan haala ni mijeessa; beekumsa isaanii qindeessuun dhaloota itti aanuuf akka darbu ni taasisa;
31) Qaama hawaasaa rakkoo jireenya hawaasummaa keessa jiraniif tajaajila haaromsaa ni kenna; maatii isaanii yookiin hawaasatti makamanii jireenya isaanii akka fooyyeffatan haala ni mijeessa;
32) Tajaajilli eegumsa hawaasummaa haala mirga fayyadamtootaa eegsisuun raawwachuu isaa ni mirkaneessa; fayyadamtoota sagantaa wabii nyaataa kallattii ta'an baadiyyaa fi magaalaatti adda ni baasa; tajaajila deeggarsa maallaqaa, akkaakuunii fi kan biroo argachuu isaanii ni mirkaneessa;
33) Fandiin hawaasummaa akka hundaa'u ni taasisa; ni sassaaba; leecalloo eegumsa hawaasummaatiif oolu walitti ni qaba; yammuu hayyamamu hojiirra ni oolcha; ni hordofa; ni too'ata; deeggarsa ogummaa ni kenna;
34) Dhaabbileen miti mootummaa dhimma nageenya hawaasummaa irratti akka bobba'an ni jajjabeessa; ni qindeessa; deeggarsa ni kenna; qaama dhimmi ilaalu waliin raawwii hojii isaanii ni madaala;
35) Namoota lammii biyya alaa ta'anii fi jaarmiyaalee adda addaa naannicha keessa socho'uun hojii adda addaa irratti bobba'an hayyama hojii qabaachuu isaanii ni too'ata; kanneen hayyama malee socho'an irratti tarkaanfii sirreeffamaa ni fudhata; akka fudhatamu qaama dhimmi ilaalu waliin ni hojjata;
36) Raawwii sagantaa eegumsa hawaasummaa saffisaa fi bu'a qabeessaa taasisuuf ta'e ragaa dhimma nageenya hawaasummaa teeknoloojii ammayyaa'aatti fayyadamuun ni sassaaba; ni qindeessa; hojiirra ni oolcha; ni tamsaasa.

፴) አረጋዊያን የድጋፍና የመዝናኛ ማዕከላት እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤ እውቀታቸዉን በማቀናጀት ለሚቀጥለው ትውልድ እንዲተላለፍ ያደርጋል፤
፴፩) የማህበራዊ ኑሮ ችግር ዉስጥ ላሉ የህብረተሰብ ክፍል የተሀድሶ አገልግሎት ይሰጣል፤ ከቤተሰቦቻቸው ወይም ከህብረተሰቡ ጋር ተቀላቅለው ኑሮአቸውን እንዲያሻሽሉ ሁኔታዎችን መቻቻል፤
፴፪) የማህበራዊ ጥበቃ አገልግሎት የተጠቃሚዎችን መብት በሚያስጠብቅ መንገድ መፈፀሙን ያረጋግጣል፤ ቀጥተኛ የምግብ ዋስትና ተጠቃሚዎች የሆኑትን በገጠርና ከተማ ይለያል፣ የገንዘብ፣ የአይነትና የሌሎች ድጋፍ አገልግሎት ማግኘታቸውን ያረጋግጣል፤
፴፫) የማህበረሰብ ፈንድ እንዲቋቋም ያደርጋል፤ ይሰበስባል፤ ለህብረተሰብ ጥበቃ የሚውለውን ሀብት ያሰባስባል፣ ሲፈቀድም ሥራ ላይ ያውላል፤ ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል ሙያዊ ድጋፍ ይሠጣል፤
፴፬) መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በማህበራዊ ደህንነት ጉዳይ ላይ እንዲሰማሩ ያበረታታል፣ ያቀናጃል፣ ድጋፍ ይሰጣል፤ የሥራ አፈፃፀማቸውን ከሚመለከተው አካል ጋር ይገመግማል፤
፴፭) የውጭ አገር ዜጎች የሆኑና በክልሉ የተለያዩ ድርጅቶች ውስጥ በመንቀሳቀስ የተለያዩ ሥራዎች ላይ የተሰማሩ ሰዎች የሥራ ፍቃድ መኖራቸውን ይቆጣጠራል፣ ካለፍቃድ በሚንቀሳቀሱት ላይ የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፣ እንዲወሰድ ከሚመለከተው አካል ጋር ይሰራል፤
፴፮) የማህበረሰብ ጥበቃ ፕሮግራም አፈፃፀምን ፈጣንና ውጤታማ ለማድረግ የማህበራዊ ደህንነት ጉዳይ ማስረጃ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመጠቀም ይሰበስባል፤ ያቀናጃል፤ ሥራ ላይ ያውላል፤ ያሰራጫል፤

30) Facilitate conditions for the elders to get assistance and entertainment centers; cause their cumulated knowledge and experiences to be organized and transferred to the next generation;
31) Provide rehabilitation services for the segments of the society that are suffering from social problems; facilitate conditions for them to be re-integrated with their families or the society and improve their lives.
32) Ensure that the social protection service to be implemented in a way that protects the rights of beneficiaries; identify the beneficiaries of food security programs in the cities and rural areas; ensure that they have got the aids in cash; in kind and other services;
33) Cause the social security fund to be established; collect same; gather the properties to be used for the social protection; implement up on its approval; follow-up; supervise; provide professional support for same;
34) Encourage the non- governmental organizations to engage in the social security affairs; organize; provide support; evaluate their work performances in collaboration with concerned bodies;
35) Follow-up the foreigners and different organizations engaged in various activities in the region to have licenses; take corrective measures on those operating without licenses; work with concerned bodies for such measures to be taken;
36) Collect the social security evidences using modern technology so as to make the implementation of social protection program speedy and effective; organize; implement; distribute same.

**34. Biiroo Konistiraakshinii**

Biiroon kun aangoo fi hojii armaan gadiitti tarreefaman ni qabaata:

1) Imaammata, tarsiimoo fi seerotni dizaayinii fi ijaarsaa gamoowwanii, bishaan, jallisii, daandii fi ijaarsawwan kana fakkaataan ilaalchisee bahan hojiirra ooluu isaanii ni hordofa, ni too'ata;
2) Gatii yeroo meeshaa ijaarsaa fi humna namaa qindeessuun seektarootni akka beekan ni taasisa;
3) Damee ijaarsaa keessatti haala hirmaannaan hawaasaa itti babal'atu ni qorata; hojiirra ni oolcha;
4) Sadarkaa fi koodota ijaarsa gamoo, bishaanii, jallisii fi daandii naannichaa ni qopheessa; dizaayinii ijaarsaa naannicha keessatti gaggeeffaman sadarkaa fi koodii eeguu isaanii xiinxaluudhaan ni mirkaneessa; ol'aantummaan ni too'ata;
5) Dizaayiniin pirojektoota ijaarsa dhuunfaa yookiin investimentii gaggeeffaman sadarkaa fi koodii eeguu isaanii ni xiinxala; ni mirkaneessa; hayyama hojii ijaarsaa ni kenna;
6) Pirojektoota baajata mootummaatiin gaggeeffamaniif waliigalteewwan hojii fi dizaayinii ijaarsaa akka qophaa'u ni taasisa; ni mirkaneessa; raawwii isaa ni hordofa; ni too'ata;
7) Jijjiirama yookiin dabalata hojii ijaarsaa, gatii, waldiddaa pirojektoota ijaarsaa irratti uumamuu fi gaaffilee kanneen irratti dhiyaatan xiinxalee furmaata akka argatan haala ni mijeessa;
8) Ijaarsa pirojektoota gamoowwanii, daandii, bishaanii, jallisii fi ijaarsawwan kan kana fakkaataan kanneen mootummaan gaggeessu ni hordofa; kaffaltiin akka raawwatamu ni taasisa; raawwii isaas ni madaala; rakkoo muudatu qorachuun yaada furmaataa mootummaadhaaf ni dhiyeessa;
9) Fedhii hojiiwwanii fi dizaayinii konistraakshinii naannichaa ni qorata; hojiirra akka oolu ni taasisa;

**፴፬. የኮንስትራክሽን ቢሮ**

ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩) የህንፃዎች፣ የውሀ፣ የመስኖ፣ የመንገድ ዲዛይንና ግንባታ እና እነዚህን የመሳሰሉ ግንባታዎችን አስመልክቶ የወጡ ፖሊሲ፤ ስትራተጂና ህጎች ሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤
፪) የግንባታ መሣሪያዎችና የሰው ሀይል ወቅታዊ ዋጋ በማቀናጀት ሴክተሮች እንዲያውቁት ያደርጋል፤
፫) በግንባታው ዘርፍ ውስጥ የህብረተሠቡ ተሣትፎ የሚስፋፋበትን ሁኔታ ያጠናል፤ ሥራ ላይ ያውላል፤
፬) የክልሉ የህንፃ ፣ የውሀ፣ የመስኖና መንገድ ግንባታ ደረጃና ኮዶች ያዘጋጃል፣ በክልሉ ውስጥ የሚከሄዱት የግንባታ ዲዛይኖች ደረጃና ኮዱን የጠበቁ መሆናቸውን በመመርመር ያረጋግጣል፤ በበላይነት ይቆጣጠራል፤
፭) የግል የግንባታ ፕሮጀክቶች ዲዛይን ወይም የሚካሄዱት ኢንቨስትመንት ደረጃና ኮድ መጠበቃቸዉን ይመረምራል፣ ያረጋግጣል፣ የግንባታ ሥራ ፍቃድ ይሰጣል፤
፮) በመንግስት በጀት ለሚከሄዱ ፕሮጀክቶች የሥራና የግንባታ ዲዛይን ውሎች እንዲዘጋጁ ያደርጋል፤ ያረጋግጣል፤ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤
፯) በግንባታ ፕሮጀክቶች ላይ የሚከሰተውን ለውጥ ወይም የግንባታ ሥራ ዋጋ ጭማሪና ከግንባታ ፕሮጀክቶች ጋር ተያይዞ የሚከሠቱ አለመግባባቶችና በነዚሁ ላይ የሚነሱ ጥያቄዎችን በመመርመር መፍትሄ እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤
፰) መንግስት የሚያካሄዳቸውን የህንፃዎች፣ የመንገድ ፣የውሀ፣ የመስኖና እነዚህን የመሣሠሉ የግንባታ ፕሮጀክቶችን ይከታተላል፣ ክፍያ እንዲፈፀም ያደርጋል፣ አፈፃፀሙንም ይገመግማል፣ የሚገጥሙትን ችግሮች በመመርመር የመፍትሄ ሐሳብ ለመንግስት ያቀርባል፤
፱) የክልሉን የሥራዎች ፍላጎትና የኮንስትራክሽን ዲዛይን ያጠናል፤ ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

**34. Construction Bureau**

The Bureau shall have the following powers and duties:-

1) Follow- up and supervise the implementation of the policy, strategies and laws enacted regarding designs and construction of buildings, water, irrigation, roads and other similar constructions.
2) Organize the current prices of construction materials and manpower and notify to the sectors.
3) Undertake studies about the ways of increasing the participation of the society in the construction sector; implement same;
4) Prepare the levels and codes of buildings, water, irrigation and roads construction in the region; review that the construction designs undertaken in the region respect the levels and codes and approve same; regulate;
5) Review that the private construction projects designs or the investments undertaken are in due respect of the levels and codes; approve same; issue construction activity license;
6) Cause the preparation of work contracts and construction designs for the projects conducted by the government budget; approve same; follow-up its implementation; supervise same;
7) Facilitate enabling conditions for reviewing and resolving the claims related to the conversion or addition of construction activity, the prices, disputes which arise on the construction projects and the claims submitted on these issues;
8) Follow- up; cause the payments to be made; evaluate the implementation of the construction of buildings, roads, water, irrigation projects and other similar constructions conducted by the government; investigate the problems encountered and propose recommendation to the government.
9) Study about the demand of works and the construction designs of the region; cause its implementation;

10) Aangoon qaama birootiif kenname akkuma eegametti ta'ee, sadarkaawwan hojii konistiraakshinii ni baasa; akkaataa seeraatiin hojiirra ooluu isaanii ni mirkaneessa;
11) Sochii damee hojiiwwan konistiraakshinii ol'aantummaan ni gaggeessa; raawwii isaa ni hordofa; qaama dhimmi ilaalu waliin ni hojjata;
12) Ijaarsa pirojektoota mootummaan gaggeessu ilaalchisee madaallii yookiin bu'aa caalbaasii seektaraan dhiyaateef xiinxalee ni mirkaneessa; yookiin qaama birootiif bakka bu'iinsa ni kenna;
13) Sadarkaa caalbaasii, ijaarsaa fi walharkaa fuudhiinsa ijaarsa gamoo, bishaanii, jallisii daandii fi kan kana fakkaataan ilaalchisee too'annoo ni gaggeessa; tarkaanfii sirreeffamaa ni fudhata;
14) Ijaarsawwan naannicha keessatti gaggeeffaman meeshaalee ijaarsaa naannotti argamuun akka ijaaramanii fi gatiin ijaarsa pirojektoota madaalawaa akka ta'u sadarkaa adda addaa qopheessee hojiirra akka oolu ni taasisa;
15) Hojii ijaarsaa irratti hirmaachuuf gaaffiin hayyama kontiraaktarummaa fi gorsitootaa yammuu dhiyaatu xiinxaluudhaan hayyama ogummaa ni kenna; ni haaromsa; sadarkaa ni guddisa; ni galmeessa; hayyamni kenname seeraa fi naamusaan ala hojiirra ooluu isaa yoo mirkaneesse ni haqa; haala raawwii isaanii irratti hundaa'uun kontiraaktarootaa fi gorsitoota gareedhaan addaan baasee seektarootni akka beekan ni taasisa;
16) Sadarkaa gorsitootaa ni murteessa; gabaasa raawwii hojii gorsitootaa ni qorata; kaffaltii tajaajila isaanii ni mirkaneessa;
17) Dizaayinoota gorsitootaan yookiin qaama biraatiin hojjataman ni qorata; ni mirkaneessa; hordoffii fi too'annoo hojiiwwan ijaarsaa ni raawwata; kaffaltiiwwan ni mirkaneessa;

፲) ለሌሎች አካላት የተሰጠው ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ የኮንስትራክሽን ሥራ ደረጃዎች ያወጣል፣ በህጉ መሰረት ሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤
፲፩) የኮንስትራክሽን ዘርፍ ሥራዎች እንቅስቃሴን በበላይነት ያካሄዳል፤ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣ ከሚመለከተው አካል ጋር ይሠራል፤
፲፪) መንግስት የሚያካሄዳቸውን የግንባታ ፕሮጀክቶች አስመልክቶ ግምገማ ወይም በሴክተሮች የሚቀርብለትን የጨረታ ውጤት በመመርመር ያረጋግጣል፣ ወይም ለሌላ አካል በውክልና ይሠጣል፤
፲፫) የህንፃዎች ፣ የውሀ፣ የመስኖ፣ የመንገድና እነዚህን የመሣሰሉ ግንባታዎችን የጨረታ ደረጃ፣ ግንባታና ርክክብን በተመለከተ ቁጥጥር ያካሄዳል፤ የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፤
፲፬) በክልሉ ውስጥ የሚካሄዱ ግንባታዎች በአከባቢው በሚገኙ የግንባታ ግብአቶች እንዲገነቡና የፕሮጀክቶች የግንባታ ዋጋ ተመጣጣኝ እንዲሆን የተለያዩ ደረጃዎችን በማዘጋጀት ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤
፲፭) በግንባታ ሥራ ላይ ለመሣተፍ የኮንትራክተርነትና የአማከሪነት ፍቃድ ጥያቄ ሲቀርብ በመመርመር የሙያ ፍቃድ ይሠጣል፣ ያዲሳል፤ ደረጃን ያሳድጋል፤ ይመዘግባል፤ የተሰጠዉ ፍቃድ ከህግና ሥነምግባር ውጪ ሥራ ላይ መዋሉን ካረጋገጠ ይሠርዛል፣ ኮንትራክተሮችንና አማካሪዎችን በሥራ አፈፃፀማቸው ላይ በመመስረት በቡድን በመለየት ሴክተሮች እንዲያውቋቸው ያደርጋል፤
፲፮) የአማካሪዎችን ደረጃ ይወስናል፣ አማካሪዎችን የሥራ አፈፃፀም ሪፖርት ይመረምራል፣ የአገልግሎት ክፍያቸውን ያረጋግጣል፤
፲፯) በአማካሪዎች ወይም በሌላ አካል የተሠሩ ዲዛይኖችን ይመረምራል፣ ያረጋግጣል፣ የግንባታ ሥራዎችን ክትትልና ቁጥጥር ይፈፅማል፣ ክፍያዎችን ያረጋግጣል፤

10) Without prejudice to the powers vested in other bodies, it sets the standards of construction works; ensure their implementation in accordance with the law;
11) Leads the overall activities of the construction branch; follow-up its implementation; work in collaboration with the concerned body;
12) Review and approve the evaluation or bid results submitted to it by a sector regarding the construction projects conducted by the government; or delegate it to other body;
13) Conduct supervision and take rectifying measures regarding bid standards, construction and taking over of buildings, water, irrigation, roads constructions and other similar projects;
14) Set various standards and make to be implemented for the constructions undertaken in the region to be constructed using local construction materials and to make the construction costs fair.
15) Examine the requests to be a contractor and consultant submitted with a view to engage in construction activity and issue professional licenses; renew; upgrade its level; register; cancel where such license is proved to be used illegally and unethically; classify the contractors and consultants in groups depending on their performances and notify same to the sectors;
16) Decide the level of consultants, evaluate their performance reports; approve their service payments;
17) Examine and approve the designs of consultants or those prepared by other bodies; perform monitoring and supervision of construction activities; approve payments;

18) Tajaajilootni bu'uura misooma adda addaa kan akka ibsaa, bishaanii, bilbila, daandii, sarara dhangala'aa fi kan kana fakkaatu magaalota keessatti dizaayinii fi sadarkaa ijaarsaa eeggatanii ijaaramuu isaanii ni hordofa; ni too'ata; tarkaanfii sirreeffamaa ni fudhata; akka fudhatamu ni taasisa;
19) Hojiiwwan misoomaa fi too'annoo industirii konistiraakshinii ni raawwata;
20) Bu'uura seera gamootiin hojiiwwan qulqulleessa pilaanii magaalotaa ni raawwata; dizaayinii ni gamaaggama; hayyama ijaarsaa fi itti fayyadamaa ni kenna;
21) Waajjira shuumii gamoo ni gurmeessa; ni hooggana; ni too'ata; galteewwan ijaarsaa irratti qo'annoo fi qorannoo ni gaggeessa; dhaabbileen barnoota ol'aanoo hojii qo'annoo fi qorannoo irratti akka hirmaatan ni qindeessa;
22) Naannicha keessatti kontiraaktaroota biyya keessaa keessumattuu waldaalee maayikiroo fi xixiqqaa hojii gorsaa fi konistiraakshinii irratti bobba'an dandeettiin isaanii cimee qulqullina qabaatanii gabaa irratti dorgomaa akka ta'an ni jajjabeessa; deeggarsa barbaachisaa ni kenna;
23) Hojii ijaarsaa keessatti carraan hojii humna namaatiin raawwatamu akka babal'atu ni jajjabeessa;
24) Sadarkaa dizaayinii bulchiinsa kontiraataa, ijaarsaa fi gatii pirojektoota ijaarsaa akka qophaa'u ni taasisa; kan qophaa'ee dhiyaate ni mirkaneessa; mootummaaf gorsa ni kenna;
25) Laboratorii meeshaalee konistiraakshinii naannichaa ol'aantummaan ni bulcha; galteewwan konistiraakshinii laboratoriidhaan qoratamanii tajaajila ijaarsaatiif ooluu isaanii ni mirkaneessa;
26) Hayyama maashinarii konistiraakshinii fi dhiyeessa meeshaalee ijaarsaa ni kenna; ni haaromsa; hanqinni yoo jiraate sirreeffama barbaachisu ni fudhata; akka fudhatamu ni taasisa;

፲፰) የተለያዩ የመሠረተ ልማት አገልግሎቶች እንደ መብራት፣ ውሀ፣ ሥልክ ፣ መንገድ፣የፍሣሽ ማስወገጃ መስመሮችና የመሣሰሉት በከተሞች ውስጥ ዲዛይንና የግንባደታ ደረጃን በመጠበቅ መገንባታቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፣ እንዲወሰድ ያደርጋል፤
፲፱) የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማትና ቁጥጥር ሥራዎችን ይፈፅማል፤
፳) በህንፃዎች ህግ መሰረት የከተሞች ፕላን ማጣራት ሥራዎችን ይሰራል፣ ዲዛይን ይገመግማል፣ የግንባታና አጠቃቀም ፍቃድ ይሰጣል፤
፳፩) የህንፃዎች ሹም ፅህፈት ቤት ያደራጃል፤ ይመራል፣ ይቆጣጠራል፣ በግንባታ ግብአቶች ላይ ጥናትና ምርምር ያካሄዳል፤ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በጥናትና ምርምር ላይ እንዲሳተፉ ያቀናጃል፤
፳፪) በክልሉ ውስጥ የአገር ውስጥ ኮንትራክተሮች በተለይም በአማካሪነትና ኮንስትራክሽን ሥራ ላይ የተሠማሩ የማይክሮና ጥቃቅን ማህበራት ችሎታቸው ዳብሮና ጥራት ኖሯቸው በገባያ ላይ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ያበረታታል፣ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሠጣል፤
፳፫) በግንባታ ሥራ ውስጥ በሰው ጉልበት የሚሰራ የሥራ እድል እንዲስፋፋ ያበረታታ፤
፳፬) የኮንትራት አስተዳደር፤ የግንባታና የፕሮጀክቶች ግንባታ ዋጋ የዲዛይን ደረጃ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፣ ተዘጋጅቶ የቀረበውን ያረጋግጣል፣ ለመንግስት ምክር ይሰጣል፤
፳፭) የክልሉን የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች ላቦራቶሪ በበላይነት ያስተዳድራል፤ የኮንስትራክሽን ግብአቶች በላቦራቶሪ ተመርምረው ለግንባታ አገልግሎት መዋላቸውን ያረጋግጣል፤
፳፮) የኮንሥትራክሽን ማሽነሪና የግንባታ መሣሪያዎች አቅርቦት ፍቃድ ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ጉድለት ካለ አስፈላደጊውን የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፣ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

18) Follow- up that the various infrastructure services such as electricity, water, telecommunication, roads, sewerage lines and the likes are constructed with due respect of the designs and construction standards in the cities; supervene; taken corrective measures or cause the measures to be taken;
19) perform development and control activities of the construction industry;
20) Perform examination the cities' plan in accordance with the laws of buildings; evaluate the designs; issue the construction and utilization license;
21) Organize buildings office; direct and supervise same; undertake research and study on the construction imputes; coordinate the higher education institutions to take part on research and studies;
22) Encourage the contractors and consultants in the region specially the micro and small scale enterprises engaged in the consultancy and construction activities to build and promote their capacities and possess better qualities to be competent on the market; provide necessary support;
23) Encourage the expansion of job opportunities performed manually;
24) Cause the preparation of the levels of designs, contract administration, construction and prices of construction projects; approve the prepared and submitted ones; give advice for the government;
25) Administer the construction materials laboratory of the region; ensure that the construction imputes shall be tested by laboratories to be used for construction services;
26) Issue licenses for construction machineries and supply of construction materials; renew; take the necessary corrective measure where there exist limitation; cause such measure to be taken;

27) Bittaawwan konistiraakshinii ni too'ata; akka too'atamus ni taasisa;
28) Madaallii gahumsa ogummaa ogeeyyii konistiraakshinii qaama dhimmi ilaalu waliin akka gaggeeffamu ni taasisa.

**35. Biiroo Barnoota Leenjii Teeknikaa fi Ogummaa**

Biiroon kun aangoo fi hojii armaan gadiitti tarreefaman ni qabaata:

1) Imaammataa fi tarsiimoo barnoota leenjii teeknikaa fi ogummaa naannicha keessatti hojiirra ni oolcha; hojiirra ooluu isaa ni hordofa;
2) Kaawunsilii fi Boordiin dhaabbata, kollejjii fi kollejjii pooliiteeknikaa akka hundeeffamu haala ni mijeessa;
3) Ulaagaa leenjifamtootni itti simataman ni qopheessa; qaama hojiirra oolchuuf ni dabarsa; hojiirra oolmaa isaa ni hordofa; dhaabbilee, kollejjoota fi kollejjii pooliiteeknikaa qindeessuun hojii misooma intarpiraayizii maayikiroo fi xixiqqaa akka deeggaran ni taasisa;
4) Barnootni dhaabbata, kollejjii fi kollejjii pooliiteeknikaa haala guddina hawaas-diinagdee fi fedhii humna namaa leenji'ee naannichi barbaaduun akka walsimu qo'annoo fedhii gabaa hojii ni gaggeessa; leenjiin kennamus fedhii gabaa irratti akka hundaa'u ni taasisa; ni hordofa;
5) Qorannoo irratti hundaa'uun dhaabbileen, kollejjoota fi kollejjii pooliiteeknikaa fedhii gabaa hojii irratti hundaa'uun akka hundeeffaman ni taasisa; ni bulcha; gurmaa'insaa fi bulchiinsa isaanii ni fooyyessa;
6) Baajataa fi qabeenyi dhaabbata, kollejjii fi kollejjii pooliiteeknikaaf barbaachisu baajata Aanaalee fi Bulchiinsa Magaalotaa irratti qabamee hojiirra akka oolu ni taasisa; raawwiin isaa qajeelfama bahuun kan murtaa'u ta'a;
7) dhaabbata, kollejjii fi kollejjii pooliiteeknikaa hunda keessatti qorannoo fedhii gabaa hojii gaggeeffamu irratti hundaa'ee kennamuusaa ni hordofa; ni too'ata;

፳፯) የኮንስትራክሽን ግዢዎችን ይቆጣጠራል፣ እንዲቆጣጠሩም ያደርጋል፤
፳፰) ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን የኮንስትራክሽን ባለሙያዎች የሙያ ብቃት ምዘና እንዲካሄድ ያደርጋል፤

**፴፭. የቴክኒክ እና ሙያ ሥልጠና ትምህርት ቢሮ**

ቢሮው የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩) የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ትምህርት ፖሊሲና ስትራተጂ በክልሉ ውስጥ ተግባር ላይ ያውላል፣ ተግባር ላይ መዋለሉን ይከታተላል፤
፪) የተቋም፣ ኮሌጅና የፖሊቴክኒክ ኮሌጅ ካውንስልና ቦርድ እንዲቋቋም ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤
፫) የሠልጣኞች ቅበላ መስፈርት ያዘጋጃል፣ ሥራ ላይ ለሚያውል አካል ያስተላልፋል፣ ሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፣ የተቋማትን፣ ኮሌጆችንና የፖሊቴክኒክ ኮሌጆችን በማቀናጀት የማይክሮና ጥቃቅን ኢንተርፐራይዝ የልማት ሥራን እንዲደግፉ ያደርጋል፤
፬) የተቋማት፣ ኮሌጅና የፖሊቴክኒክ ኮሌጅ ትምህርት በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ሁኔታና ክልሉ ከሚፈልገው የሰለጠነ የሰው ሀይል ጋር እንዲጣጣም የሥራ ፍላጎት ገበያ ጥናት ያካሂዳል፣ የሚሰጠው ሥልጠናም በገበያው ፍላጎት ላይ እንዲመሰረት ያደርጋል፣ ይከታተላል፤
፭) በጥናት ላይ በመመስረት ተቋማት፣ ኮሌጆችና የፖሊቴክኒክ ኮሌጆች በገበያው ፍላጎት ላይ በመንተራስ እንዲቋቋሙ ያደርጋል፣ ያስተዳድራል፣ አደረጃጀትና አስተዳደራቸውን ያሻሽላል፤
፮) ለተቋም ፣ኮሌጅና ፖሊቴኪኒክ ኮሌጅ ያሚያስፈልገው በጀትና ሀብት በወረዳዎችና በከተማ መስተዳድሮች በጀት ላይ ተይዞ ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፣ አፈፃፀሙ በሚወጣው መመሪያ የሚወሰን ይሆናል፤
፯) በሁሉም ተቋም ኮሌጅና ፖሊቴክኒክ ኮሌጅ ውስጥ በሚካሔደው የገበያ የሥራ ፍላጎት ጥናት ላይ በመመስረት መሰጠቱን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

27) supervise the construction procurements; cause same to be supervised;
28) Cause the competency evaluation of construction professionals to be conducted in collaboration with the concerned body.

**35. Technical and Vocational Training Education Bureau.**

The Bureau shall have the following powers and duties:

1) Implement; follow-up the implementation of the policy and strategy of the Technical and Vocational Training Education in the region;
2) Facilitate enabling condition for the establishment of the Council and Board of the institute, college and polytechnic college;
3) Set admission criteria of the trainees and refer to the implementing body; follow- up its implementation ; Coordinate the institutes, colleges and polytechnic colleges and make them support the micro and small scale enterprises development activities;
4) Undertake work market demand study for the courses provided in the institutes, colleges and polytechnic colleges to be compatible with the socio economic development and the trained man power that the region demands; and cause the trainings provided to depend on the demand of the market; follow-up same;
5) Depending on research, cause the institutes, colleges and polytechnic colleges to be established depending on the market demand; administer same; improve their organization and administration;
6) Cause the budget and resources needed for the institutes, colleges and polytechnic colleges to be allocated on the budgets of districts and city administrations and be implemented accordingly; Its implementation shall be decided by the directive to be issued;
7) Follow-up and control that all the training in the institutes, colleges and polytechnic colleges to be provided depending on work market demands;

8) Sagantaaleen dhaabbata, kollejjii fi kollejjii pooliiteeknikaa naannichaa sadarkaa gahumsaa fi qulqullinaa biyyoolessaa eeggachuun gaggeeffamaa jiraachuu isaanii ni mirkaneessa; gahumsaa fi qulqullina barbaachisuun gaditti hojjatame jedhee yoo itti amane tarkaanfii sirreeffamaa ni fudhata;
9) Yaada maamiltootaa fi ogeessota dhaabbata, kollejjii fi kollejjii pooliiteeknikaa akkasumas, qorannoo irratti hundaa'uun sagantaalee leenjii haaraa ni bana; kanneen hin barbaachisne ni cufa;
10) Qorannoo leenjiin boodaa ni gaggeessaa; akka gaggeeffamu ni taasisa; bu'aa qorannichaa irratti hundaa'uun sirreeffama ni taasisa;
11) Sirna dhaabbata, kollejjii fi kollejjii pooliiteeknikaa ogummaalee leenjii kennan wiirtuu kalaqqii fi oomishaa hundeeffachuun galii keessaa maddisiisuun itti fayyadamuu danda'an ilaalchisee ni diriirsa; yammuu hayyamamu hojiirra akka oolu ni taasisa;
12) Abbootiin qabeenyaa dhuunfaa, hawaasni, dhaabbileen mootummaa fi miti mootummaa dhaabbata, kollejjii fi kollejjii pooliiteeknikaa keessatti hirmaachuu akka danda'an haala ni mijeessa; tooftaa ni qopheessa;
13) Dhaabbatni, kollejjii fi kollejjiin pooliiteeknikaa dhuunfaa fi miti mootummaa, istaandardii eeguu isaanii ni madaala; gorsa ogummaa ni kenna; yeroo yeroon too'annoo ni gaggeessa; tarkaanfii sirreeffamaa ni fudhata;
14) Tooftaa hirmaannaan dubartootaa fi qaama miidhamtootaa dhaabbata, kollejjii fi kollejjii pooliiteeknikaa keessatti itti dabalu ni baasa; hojiirra ni oolcha;
15) Qaama miidhamtootni haala dhaabbata, kollejjii fi kollejjii pooliiteeknikaa argachuu itti danda'an ni mijeessa; hojiirra ni oolcha; hojiirra ooluu isaa ni hordofa;

፰) የክልሉ የተቋም፣ ኮሌጅና ፖሊቴክኒክ ኮሌጅ ፕሮግራሞች ብሔራዊ የብቃትና ጥራት ደረጃቸውን በመጠበቅ እየተካሄዱ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤ ከተገቢው ብቃትና ጥራት ደረጃ በታች ተሰርቷል ብሎ ሲያምን የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፤
፱) የተቋም፣ ኮሌጅና ፣ፖሊቴክኒክ ኮሌጅ የደንበኞችና ባለሙያዎች አስተያየት እንዲሁም በጥናት ላይ በመመስረት አዳዲስ የሥልጠና ፕሮግራሞች ይከፍታል፣ የማያስፈልጉትን ይዘጋል፤
፲) የድህረ ሥልጠና ግምገማ ያካሄዳል፤ እንዲካሄድ ያደርጋል፣ በሥልጠናው ውጤት ላይ በመመስረት ማስተካከያ ያደርጋል፤
፲፩) የሙያ ሥልጠና የሚሰጡ ተቋም ኮሌጅና ፖሊቴክኒክ ኮሌጅ የፈጠራና ማምረቻ ማዕከል በመመስረት የውስጥ ገቢያቸውን በማመንጨት መጠቀም የሚችሉበትን ሥርዐት ይዘረጋል፣ ሲፀድቅም በተግባር ላይ እንዲዉል ያደርጋል፤
፲፪) የግል ባለሐብቶች፣ ህብረተሰቡ፣ የመንግስትና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ውስጥ እንዲሣተፉ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ ሥልቶችንም ይነድፋል፤
፲፫) የግልና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ኮሌጆችና ፖሊቴክኒክ ኮሌጆች ስታንዳርድ የጠበቁ መሆናቸውን ይመዝናል፣ ሙያዊ ምክር ይሠጣል፣ በየጊዜው ቁጥጥር ያካሄዳል፣ የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፤
፲፬) የሴቶችና አካል ጉዳተኞች በተቋም፤ ኮሌጅና ፖሊቴክኒክ ኮሌጅ ውስጥ ተሳትፎዋቸዉ የሚጨምርበትን ሥልት ያወጣል፣ ተግባር ላይ ያውላል፤
፲፭) የአካል ጉዳተኞች ተቋም፤ ኮሌጅና ፖሊቴክኒክ ኮሌጅ ማግኘት የሚችሉበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ በተግባር ላይ ያውላል፣ ተግባር ላይ መዋሉን ይከታተላል፤

8) Ensure that the programs of the institutes, colleges and polytechnic colleges in the region are being conducted in conformity with the national competency and quality standards; take corrective measure where it believes to be performed below the necessary competency and quality standard.
9) Offer new training programs depending on the recommendations of customers and professionals of the institutes, colleges and polytechnic colleges and close the unnecessary ones;
10) Undertake post training assessment; cause same to be undertaken ; make corrections depending on the findings of the assessment;
11) Establish a system whereby the institutes, colleges and polytechnic colleges providing vocational trainings generate and use their internal income by establishing innovation and production centers; cause its implementation up on approval.
12) Facilitate enabling conditions and devise mechanisms to enable the private investors, the society, the governmental and nongovernmental organizations to take part in the institutes, colleges and polytechnic colleges;
13) Evaluate that the private and non-governmental institutes, colleges and polytechnic colleges respect the standard set forth; provide professional advice; conduct supervision from time to time; take corrective measures;
14) Devise mechanisms of increasing the participation of women and disabled persons in the institutes, colleges and polytechnic colleges; implement same;
15) Facilitate enabling conditions for the disabled persons to join the institutes, colleges and polytechnic colleges; implement same; follow-up its implementation;

16) Industirii fi dhaabbilee tajaajilaa qindeessuun dhaabbatni, kollejjii fi kollejjiin pooliiteeknikaa gocha irratti akka xiyyeeffatee kennamu ni taasisa; hojiirra oolmaa isaa ni hordofa;
17) Leenjifamtootni gahumsaa fi dandeettii gahaa qaban haala hojii leenjisuutti galuu itti danda'an ni mijeessa; hojiirra ni oolcha; yeroo yeroon dandeettiin isaanii akka fooyya'u ni taasisa;
18) Tarsiimoo intarpiraayizii maayikiroo fi xixiqqaa hojiirra oolchuuf hojiin tajaajila ekisteenshinii industirii fi intarpiraayizii maayikiroo fi xixiqqaa abbummaan ni hojjata; gurmaa'ina kanaaf barbaachisu sadarkaa naannootii kaasee hanga dhaabbata, kollejjii fi kollejjii pooliiteeknikaatti ni qabaata;
19) Waldaalee intarpiraayizii maayikiroo fi xixiqqaatiif leenjii fi deeggarsa ogummaa dandeettii isaanii cimsu ni kenna;
20) Hubannoon hawaasni dhaabbata, kollejjii fi kollejjii pooliiteeknikaa irratti qabu akka cimu ni hojjata;
21) Dandeettiin leenjistootaa akka cimu hanqina jiru addaan baasuun leenjii ni kenna; akka kennamu qaama dhimmi ilaalu waliin ni hojjata; gahumsa isaanii madaaluun deeggarsa barbaachisaa ta'e ni kenna;
22) Pirojektoota adda addaa dhaabbata, kollejjii fi kollejjii pooliiteeknikaa deeggaran ni qopheessa; hojiirra ni oolcha; hojiirra akka oolu ni taasisa
23) Nagahee galiin keessoo ittiin funaanamu Biiroo Maallaqaa fi Walta'iinsa Diinagdee hayyamsiisuun ni maxxansiisa; dhaabbileen, kollejjootaa fi kollejjii pooliiteeknikaa akka itti fayyadaman ni taasisa.

፲፮) ኢንዱስትሪዎችንና የአገልግሎት ሰጪ ድርጅቶችን በማቀናጀት ተቋም፤ ኮሌጅና ፖሊቴክኒክ ኮሌጅ ሥልጠና በተግባር ላይ አተኩሮ እንዲሰጥ ያደርጋል፤ ሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፤
፲፯) ብቃትና ችሎታ ያላቸው ሠልጣኞች ወደ አሰልጣኝነት ሥራ የሚገቡበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ ሥራ ላይ ያውላል፣ በየጊዜው ችሎታቸው እየተሻሻለ እንዲሄድ ያደርጋል፤
፲፰) የማይክሮና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች ስትራተጂን ተግባር ላይ ለማዋል የኢንዱስቱሪና የማይክሮና ጥቃቅን ኤክስቴንሽን ሥራን በባለቤትነት ይሰራል፣ ለዚሁ የሚያስፈልገው አደረጃጀትም ከክልል እስከ ተቋም ኮሌጅና ፖሊቴክኒክ ኮሌጅ ድረስ ይኖረዋል፤
፲፱) ለማይክሮና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች ማህበራት አቅም የሚገነባ ሥልጠናና የሙያ ድጋፍ ይሠጣል፤
፳) ህብረተሰቡ በተቋም፤ ኮሌጅና ፖሊቴክኒክ ኮሌጅ ላይ ያለው ግንዛቤ እንዲዳብር ይሠራል፤
፳፩) የአሰልጣኞች ችሎታ እነዲዳብር ያለውን ውሱንነት በመለየት ሥልጠና ይሠጣል፣ እንዲሰጥም ከሚመለከተው አካል ጋር ይሰራል፣ ብቃታቸውን በመመዘን አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤
፳፪) ተቋም፤ ኮሌጅና ፖሊቴክኒክ ኮሌጅ የሚረዱ የተለያዩ ፕሮጀክቶችን ያዘጋጃል፣ ሥራ ላይ ያውላል፣ ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤
፳፫) የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ልማት ቢሮን በማስፈቀድ የውስጥ ገቢ የሚሰበሰብበትን ደረሰኝ ያሳትማል፣ ተቋማት ፣ ኮሌጆችና የፖሊቴክኒክ ኮሌጆች እንዲጠቀሙበት ያደርጋል፤

16) Ensure that the lesson provided in the institutes, colleges and polytechnic colleges to be practice oriented through coordinating the industry and service rendering institutions; follow- up its implementation;
17) Facilitate conditions which enable the trainees having greater efficiencies and sufficient abilities to be promoted to the trainer ship status and engage in such activity; implement same; and make their abilities be promoted from time to time;
18) Perform industrial and the micro and small enterprises extension services activities so as to successfully implement the micro and small scale enterprises strategy; shall have structural organization necessary for such purpose extended from the regional level up to the institutes, colleges and polytechnic colleges;
19) Provide the capacity building trainings and professional support for the micro and small scale enterprises associations;
20) Work for the promotion of the understanding of the society towards the institutes, colleges and polytechnic colleges;
21) Provide trainings; work with the concerned body for the provision of same through identifying the existing limitations so as to build up the abilities of the trainers; give the required support by evaluating their efficiencies;
22) Prepare different projects that help the institutes, colleges and polytechnic colleges; implement and cause its implementation;
23) Cause the publication of receipts which help to collect internal incomes up on the permission of Finance and Economic Cooperation Bureau; and make the institutes, colleges and polytechnic colleges to use it;

## 36. Abbaa Taayitaa Daandiiwwanii

Abbaan Taayitichaa aangoo fi hojii armaan gadii ni qabaata:

1) Imaammata, tarsiimoo, sagantaalee fi seerota daandiiwwan babal'isuuf gargaaraan ni burqisiisa; ni qorata; mootummaaf ni dhiyeessa; yammuu mirkanaa'u hojiirra ni oolcha; hojiirra akka oolu ni taasisa;
2) Daandiiwwan Naanniichaa abbummaan ni bulcha ni too'ata; ni kunuunsa; ni supha; ni suphisiisa; sadarkaa isaanii ni fooyyessa;
3) Karooraa fi sagantaa daandiiwwan babal'isuu, suphuu fi sadarkaa ol guddisuuf gargaaru ni qopheessa;
4) Sadarkaa tajaajila daandii fi sadarkaa diizaayinii daandii fedhii fi guddina diinagdee irratti hundaa'e ni qopheessa; qaama dhimmi ilaaluun yammuu mirkanaa'u hojiirra ni oolcha; hojiirra akka oolu ni taasisa;
5) Daandii fi riqichi akkaataa sadarkaa fi barbaachisummaa isaatti kontiraaktaraan yookiin ummataan akka ijaaramu, suphamu, sadarkaan isaa akka fooyya'u, akkasumas akka kunuunfamu ni taasisa;
6) Qorannoo fi qo'annoo daandii fi daandiin walqabate ni gaggeessa; akka gaggeeffamu ni taasisa; ragaalee fi istaatistiksii adda addaa walitti ni qaba; ni qindeessa; ni tamsaasa; ni gabaasa;
7) Tooftaa daandii fi riqichi ittiin qoratamu, diizaayiniin ittiin qophaa'u, akkasumas ijaarsii fi suphaan ittiin raawwatamu ni diriirsa; hojiirra ni oolcha; hojiirra oolmaa isaas ni hordofa;
8) Teeknolojiiwwan gatii xiqqaan daandii babal'isuu, suphuu fi sadarkaa ol guddisuuf gargaaru yeroo yeroon qoratee hojiirra ni oolcha;
9) Hawaasni sadarkaa adda addaatti gurmaa'ee humnaa fi qabeenya isaa qindeessuudhaan daandii hawaasaa fi daandiiwwan kan biroo akka ijaaru, suphuu fi kunuunsu ni taasisa; deeggarsa ogummaa fi meeshaalee ijaarsaa ni kenna;
10) Qulqullina raawwii ijaarsaa fi suphaa daandii ni too'ata; qaama birootiniis akka too'atamu ni taasisa;

## ፴፮. የመንገዶች ባለስልጣን

ባለስልጣኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩) መንገዶችን ለማስፋፋት የሚረዱ ፖሊሲዎች፣ ስትራተጂዎች፣ ፕሮግራሞችና ህጎች ያመነጫል፤ ያጠናል፤ ለመንግስት ያቀርባል፤ ሲፀድቅም ተግባር ላይ ያውላል፤ ተግባር ላይ እንዲውል ያደርጋል፤
፪) የክልሉን መንገዶች በባለቤትነት ያስተዳድራል፣ ይቆጣጠራል፣ ይንከባከባል፣ ይጠግናል፤ያስጠግናል፤ ደረጃቸውን ያሻሽላል፤
፫) መንገዶችን ለማስፋፋት፤ ለመጠገን እና ደረጃቸውን ለማሳደግ የሚረዳ ዕቅድና ፕሮግራም ያዘጋጃል፤
፬) በፍላጎትና የኢኮኖሚ ዕድገት ላይ የተመሠረተ የመንገድ አገልግሎት ደረጃና የዲዛይን ደረጃ ያዘጋጃል፤ በሚመለከተው አካል ሲፀድቅም ሥራ ላይ ያውላል፣ ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤
፭) መንገድና ድልድይ እንደ ደረጃቸውና እንደ አስፈላጊነታቸው በኮንትራክተር ወይም በህብረተሰቡ እንዲሰሩ፣ እንዲጠገኑ፣ ደረጃቸው እንዲሻሻልና እንክብካቤ እንዲደረግላቸው ያደርጋል፤
፮) የመንገድና ከመንገድ ጋር የተያያዘ ጥናትና ምርምር ያካሄዳል፤ እንዲካሄድም ያደርጋል፤ የተለያዩ መረጃዎችና ስታቲክስን ይሰበስባል፤ ያቀናጃል ፣ ያሰራጫል፣ ሪፖርት ያደርጋል፤
፯) መንገድና ድልድይ የሚጠናበትን፣ ዲዛይን የሚዘጋጅበትን እንዲሁም ግንባታና ጥገና የሚፈፀምበትን ሥልት ይዘረጋል፣ ሥራ ላይ ያውላል፣ ሥራ ላይ መዋሉንም ይከታተላል፤
፰) በዝቅተኛ ወጪ መንገድ ለማስፋፋት ለመጠገንና ደረጀውን ለማሻሻል የሚረዱ ቴክኖሎጂዎችን በየጊዜው በማጥናት ሥራ ላይ ያውላል፤
፱) ህብረተሰቡ በተለያዩ ደረጃዎች ተደራጅቶ ጉልበቱንና ንብረቱን በማቀናጀት የህብረተሰብ መንደገድና ሌሎች መንገዶች እንዲሰራ፣ እንዲጠግንና እንዲንከባከብ ያደርጋል፣ የሙያና የግንባታ መሣሪያዎች ድጋፍ ይሰጣል፤
፲) የመንገድ ግንባታና ጥገና ሥራ አፈፃፀም ጥራትን ይቆጣጠራል፣ በሌሎች አካላትም ቁጥጥር እንዲደረግበት ያደርጋል፤

## 36. Roads Authority

The Authority shall have the following powers and duties:

1) Initiate; investigate and submit to the government the polices, strategies and laws that help for the expansion of roads; implement; cause its implementation up on approval;
2) Administer the roads of the region; supervise; protect; maintain; or make them to be maintained; upgrade their standard;
3) Prepare a plan and program that help to expand; maintain and upgrade the standards of roads;
4) Prepare the standards of service and standards of design of roads depending on the demand and economic growth ; implement same up on approval by concerned body; cause its implementation;
5) Cause the roads and bridges to be constructed; maintained; upgraded and conserved by the contractors or the people on the basis of its standard and significance;
6) Undertake research and study of roads and road related activities; cause it to be undertaken; collect various evidences and statistical data; analyze, disseminate and report;
7) Establish a mechanism whereby the roads and bridges shall be investigated; designs be prepared; and construction and maintenance be performed; implement and follow-up its implementation;
8) Study and implement periodically the technologies which help to expand, maintain and upgrade the roads in low costs;
9) Make the public to organize at different levels and construct, maintain and nurture public roads and other roads by coordinating its manpower and resources; provide professional and construction materials support;
10) Supervise; cause to be supervised by the other body the performance quality of construction and maintenance of roads;

11) Daandiin akka hin mancaanee fi tajaajilaan ala akka hin taane seerootni bahan hojiirra ooluu isaanii ni hordofa;
12) Waldaalee, Intarpiraayizii Maayikiroo fi xixiqqaa fi kontraaktaroonni xixiqqaan ijaarsaa fi suphaa daandii irratti bobba'an hojii isaaniif kenname gahumsaan raawwachuu akka danda'an dandeettii isaanii cimsuuf qaama dhimmi ilaalu waliin ni hojjata;
13) Bal'ina daandii ni murteessa; ni too'ata;
14) Akkaataa itti fayyadama daandii keessumattuu, daandiin akka hin mancaane hanga ulfaatinaa fi fe'iinsa konkoolaataa ni murteessa; ni too'ata;
15) Sadarkaa fi qulqullina meeshaalee hojii ijaarsa daandii irra oolan kan akka dhagaa, biyyoo paavimantii, biyyoo filatamaa, cirrachaa fi kan biroo ni qorata; ni qorachiisa; kan sadarkaa fi qulqullina isaa eeggate qofti hojiirra akka oolu ni taasisa;
16) Ijaarsa daandiitiif kan oolan kan akka dhagaa, biyyoo paavimantii, biyyoo filatamaa, cirrachaa fi kan biroo hayyama qaama dhimmi ilaallatuun kaffaltii malee itti fayyadamuu ni danda'a;
17) Daandiin faayidaa yaadame qofaaf hojiirra akka ooluu fi gochi seeraan alaa daandii irratti akka hin raawwatamne ni too'ata; tarkaanfii sirreeffamaa ni fudhata; akka fudhatamus ni taasisa;
18) Qabeenya daandii irratti argamu qaama dhimmi ilaalu waliin ta'uun ni kaasa; ni kaasisa;
19) Ijaarsi daandii qabeenya uumamaa fi naannoo irratti dhiibbaa akka hin dhaqqabsiifne eegumsa gahaa ni taasisa; qaama dhimmi ilaalu waliin ni hojjata;
20) Qabeenya lafa ijaarsa daandiitiif oolu irratti argamaniif bu'uura seeraatiin beenyaan akka kaffalamu ni taasisa; akkaataa barbaachisummaa isaatti ni kaffala;
21) Dandeettiin raawwachiisummaa seektara daandii akka cimu ni hojjata; leenjii gaggabaaboo ni kenna; akka kennamu ni taasisa;

፲፩) መንገዶች እንዳይበላሹና ከአገልግሎት ውጪ እንዳይሆኑ የወጡ ህጎች ተግባር ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፤
፲፪) በመንገድ ግንባታና ጥገና ላይ የተሰማሩ ማህበራት፤ የማይክሮና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዝና አነስተኛ ኮንትራክተሮች የተሰጣቸውን ሥራ በብቃት መፈፀም እንዲችሉ አቅማቸውን ለማጠናከር ከሚመለከተው አካል ጋር ይሠራል፤
፲፫) የመንገድን ሥፋት ይወስናል፤ ይቆጣጠራል፤
፲፬) የመንገድ አጠቃቀም ሁኔታ በተለይም መንገድ አንዳይበላሽ የመኪኖችን የክብደትና የጭነት መጠን ይወስናል፤ ይቆጣጠራል፤
፲፭) የመንገድ ግንባታ ሥራ ላይ የሚውሉ መሣሪያዎች እንደ ድንጋይ ፣ የፔቭመንት አፈር፣ የተመረጠ አፈር፣ ጠጠርና ሌሎችን ደረጃና ጥራት ያጠናል፤ ያስጠናል፣ ደረጃና ጥራቱን የጠበቀው ብቻ ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤
፲፮) ለመንገድ ግንባታ የሚውሉ እንደ ድንጋይ፣ የፔቭመንት አፈር፣ የተመረጠ አፈር፣ ጠጠርና ሌሎች በሚመለከተው አካል ፍቃድ ያለክፍያ መጠቀም ይችላል፤
፲፯) መንገዶች ለታለመላቸው አገልግሎት ብቻ ሥራ ላይ እንዲውሉና በመንገዶች ላይ ህገወጥ ድርጊት እንዳይፈፀም ይቆጣጠራል፣ የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፣ እንዲወሰድም ያደርጋል፤
፲፰) በመንገዶች ላይ የሚገኝ ንብረትን ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን ያነሣል፣ያስናሳል፤
፲፱) የመንገድ ግንባታ በተፈጥሮ ሐብትና በአከባቢ ላይ ጉዳት ተጽኖ እንዳያደርስ በቂ ጥበቃ ያደርጋል፣ ከሚመለከተው አካል ጋር ይሠራል፤
፳) ለመንገድ ግንባታ የሚውል መሬት ላይ ለሚገኝ ንብረት በህጉ መሰረት ካሣ እንዲከፈል ያደርጋል፣ እንደ አስፈላጊነቱ ይከፍላል፤
፳፩) የመንገድ ሴክተር የአፈፃፀም አቅም እንዲጠናከር ይሠራል፤ አጫጭር ሥልጠናዎችን ይሠጣል፤ እንዲሰጥ ያደርጋል፤

11) Follows-up the implementation of the laws enacted to protect the roads from destruction and becoming out of use.
12) Work in collaboration with concerned body to build the capacities of associations, the micro and small scale enterprises and smaller contractors engaged in the construction and maintenance of roads so as to enable them undertake their activities effectively;
13) Determine the width of roads and supervise same;
14) Decide and supervise the ways of utilization of roads, specially the weight and load of the vehicle it can carry so as to protect the road from destruction;
15) Test; cause to be tested the standard and quality of construction materials required for the construction of roads like stones, pavement soil, selected soil, sand and others; cause only the standardized and quality ones to be used for construction purposes;
16) May use the materials used for road construction like the stones, pavement soil, selected soil, sands and others without payment under the authorization of concerned body;
17) Control that the road to be used only for the purpose it is intended and no illegal act be committed on the roads; take corrective measures; cause such measures to be taken;
18) Remove the property found on the road in collaboration with the concerned body; cause its removal;
19) Make the required protection for the construction of roads not to cause adverse impact on the natural resources and the environment; work with the concerned body;
20) Make compensation to be paid in accordance with the law for the properties found on the land to be used for construction of roads; pay such compensation as deemed necessary;
21) Work for building the performance capacity of the roads sector; provide short term trainings; cause it to be provided;

22) Hojjattoota haala addaatiin iskeeliin mindaa isaanii murtaa'uu qabu qoratee Mana Maree Bulchiinsa Mootummaa Naannichaatiif ni dhiyeessa; yammuu hayyamamu hojiirra ni oolcha;

23) Dhimmichi adeemsa Mana Murtiin ilaalamuun isaa akkuma eegametti ta'ee, Ijaarsa daandiin walqabatee wal dhabiinsa Abbaa Taayitichaa fi kontiraaktara, waldaalee, Intarpiraayizii Maayikiroo fi Xixiqqaa yookiin gorsaa gidduutti uumamu fedhii Abbaa Taayitaa fi qaama Abbaa Taayitichaa waliin waliigaltee seene irratti hundaa'uun akkaataa barbaachiisummaa isaatti Mana Murtiitiin alatti akka xumuramu ni taasisa; raawwiin isaa Dambii bahuun kan murtaa'u ta'a.

**37. Abbaa Taayitaa Too'annoo Dhaabbilee Misoomaa Mootummaa**

Abbaan Taaytichaa aangoo fi hojii armaan gadii ni qabaata:

1) Karooraa fi raawwii hojii dhaabbilee misoomaa ni hordofa; ni gamaaggama; kallattii ni kaa'a;
2) Dhaabbilee misoomaa ilaalchisee yaada imaammataa fi tarsiimoo ni maddisiisa; yammuu mirkanaa'u hojiirra ni oolcha; kallattii tarsiima'aa ni kenna;
3) Dhaabbileen misoomaa akka hundeeffaman qorannoo pirojektootaa ni gaggeessa; yammuu mirkanaa'u hojiira olmaa isaa ni hordofa;
4) Dandeettii dhaabbilee misoomaa mootummaa cimsuuf qorannoo fi qo'annoo ni gaggeessa; kallattii waliigalaa ni kenna;
5) Galmawwan waliigalaa fi karoora investimentii dhaabbilee misoomaa ni mirkaneessa;
6) Kaappitaalli ka'umsaa dhaabbilee misoomaatiif mootummaan akka ramadu ni taasisa;
7) Dhaabbilee misoomaa haarawaa hundeeffamaniif kaappitaalli ka'umsaaf hayyamame waggaa shan keessatti kaffalamee akka xumuramu, herregni baajata ofeeggannoo akka qabamu yookiin waggaa waggaan baajanni akka qabamu mootummaaf ni dhiheessa; raawwii isaa ni hordofa;

፳፪) የደሞዝ እስኬላቸው በተለየ ሁኔታ ሊወሰን የሚገባው ሠራተኞችን በማጥናት ለክልሉ የመንግስት መስተዳድር ምክር ቤት ያቀርባል፤ ሲፈቀድም ሥራ ላይ ያውላል፤

፳፫) ጉዳዩ በፍርድ ቤት አካሄድ የሚታይ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ከመንገድ ግንባታ ጋር ተያይዞ በባለስልጣኑና በኮንትራክተር፤ በማህበራት፣ በማይክሮና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ ወይም አማካሪ መካከል የሚከሰተውን አለመግባባት በባለስልጣኑና ከባለስልጣኑ ጋር ውል የገባ አካል ፍላጎት ላይ በመመስረት እንደአስፈላጊነቱ ከፍርድ ቤት ውጪ መፍትሄ እንዲያገኝ ያደርጋል፤ አፈፃፀሙ በሚወጣው ደንብ የሚወሰን ይሆናል፡፡

**፴፯. የመንግስት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ባለስልጣን**

ባለስልጣኑ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩) የልማት ድርጅቶችን የሥራ ዕቅድና አፈፃፀም ይከታተላል፣ ይገመግማል፤ አቅጣጫ ያስቀምጣል፤
፪) የልማት ድርጅቶችን አስመልክቶ የፖሊሲና ስትራተጂ ሀሳብ ያመነጫል፣ ሲፀድቅም ሥራ ላይ ያውላል፣ ስትራተጂካዊ አቅጣጫ ይሠጣል፤
፫) የልማት ድርጅቶች እንዲቋቋሙ የፕሮጀክቶች ጥናት ያካሄዳል፤ ሲፀድቅም ሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፤
፬) የልማት ድርጅቶችን አቅም ለማጠናከር ጥናትና ምርምር ያካሄዳል፣ አጠቃላይ አቅጣጫ ይሰጣል፤
፭) የልማት ድርጅቶችን አጠቃላይ ግብና የኢንቨስትመንት ዕቅድ ያፀድቃል፤
፮) ለልማት ድርጅቶች መነሻ ከፒታል መንግስት እንዲመድብ ያደርጋል፤
፯) አዲስ ለተቋቋሙ የልማት ድርጅቶች የተፈቀደው መነሻ ካፒታል በአምስት አመት ውስጥ ተከፍሎ እንዲፈፀም፣ የመጠባበቂያ በጀት ሒሣብ እንዲያዝ ወይም በየአመቱ በጀት እንዲያዝ ለመንግስት ያቀርባል፤ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

22) Study the employees whose salary scales shall be determined differently and submit to the Regional Administration council; implement same up on approval;

23) Without prejudice for the issue to be tried by the court proceedings, it may cause the disputes which arise between the Authority and the Contractor, Associations, the micro and small scale enterprises or the consultants in connection with road construction to be resolved through extra court mechanisms as deemed necessary depending on the consent of the Authority and the body which conclude contractual agreement with the Authority; Its implementation shall be decided by the regulation to be issued;

**37. Public Enterprises Regulatory Authority**

The Authority shall have the following powers and duties;

1) Follow up and evaluate the work plan and performances of public enterprises; and set directions;
2) Initiate policy and strategy concerning public enterprises; implement up on approval; provide strategic direction;
3) Undertake project study with a view to establish public enterprises; follow-up its implementation upon its approval;
4) Undertake research and study for building the capacities of public enterprises; give general direction;
5) Approve the general goals and investment plans of the public enterprises;
6) Cause the allocation of running capital for public enterprises by the government;
7) Propose recommendation for the government that the initial capital allocated for newly established public enterprises to be paid and completed within five years; the reserve budget to be allocated or the budget to be allocated annually; follow up its implementation;

8) Walitti qabaa fi miseensota Boordii dhaabbilee misoomaa Pirezidaantii Mootummaa Naannichaatiif dhiyeessuun akka ramadaman ni taasisa; raawwii hojii isaanii ni hordofa;
9) Durgoo miseensota Boordii fi sirna onnachiistuu bu'aa irratti xiyyeeffate miseensoota boordii fi hojii gaggeessitoota dhaabbilee misoomaaf oolu qoratee hojiira akka oolu ni taasisa; raawwii isaa ni hordofa;
10) Ramaddii odiitaroota alaa dhaabbilee misoomaa ni mirkaneessa;
11) Gabaasa herregaa dhaabbilee misoomaa mootummaa odiitara alaatiin qoratamanni mirkaneessa;
12) Bu'aa qulqulluu dhaabbilee misoomaa mootummaa irraa dhibbeentaan mootummaaf yeroo yerootti dhangala'uu qabu qoratee hojiirra akka oolu ni taasiisa;
13) Fandii misoomaa fi industirii dhaabbilee misoomaa mootummaa akka hundeeffamu ni taasisa; yammuu hayyamamu hojiirra ni oolcha;
14) Bu'aa waldaalee aksiyoonaa mootummaan qooda keessaa qabu yeroo yerootiin fandii misoomaa fi industiriitti dhangala'uu isaa ni hordofa; ni raawwachiisa;
15) Dhaabbileen misoomaa kaayyoo fi eergama isaanii galmaan ga'uu akka danda'aniif humni raawwachiisummaa isaanii haala itti cimu ni qorata; bu'aa qorannichaa mootummaaf ni dhiyeessa; yammuu murtaa'u hojiirra oolmaa isaa ni hordofa;
16) Kaappitaala qabanii fi haala uumama isaanii irratti hundaa'uun sadarkaa dhaabbilee misoomaa ni murteessa;
17) Investimentiiwwan kaayyoo hundeeffama dhaabbilee galmaan gahuu fi ce'umsa industiriif galtee ta'uu danda'an qoratee akka irratti hirmaatan ni taasiisa;
18) Aksiyoonota bu'aa qabeeyyii fi guddina diinagdee biyyaa fi naannoo keenyaa keessatti tarsiimo'aa ta'an qoratee mootummaa bakka bu'uun bittaa aksiiyoonaa ni gaggeessa; dhaabbileen misoomaa akka irratti hirmaatan ni taasisa; hojiirra oolmaa isaa ni hordofa;

፰) የልማት ድርጅቶች የቦርድ ሰብሣቢና አባላትን ለክልሉ ፕሬዝዳንት በማቅረብ እንዲመደቡ ያደርጋል፣ የሥራ አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፤
፱) የቦርድ አባላት አበልና ለቦርድ አባላትና ለልማት ድርጅቶች ሐላፊዎች የሚውል ውጤት ተኮር የማትጊያ ሥርዐት በማጥናት ሥራ ላይ ያውላል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤
፲) የልማት ድርጅቶች የውጭ ኦዲተሮች ምደባ ያፀድቃል፤
፲፩) በውጭ ኦዲተሮች የተመረመሩትን የልማት ድርጅቶች የሂሣብ ሪፖርት ያፀድቃል፤
፲፪) ከመንግስት የልማት ድርጅቶች በየጊዜው ለመንግስት ፈሠስ ሊደረግ የሚገባውን የተጣራ ትርፍ በመቶኛ አስልቶ ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤
፲፫) የመንግስት የልማት ድርጅቶች የልማትና ኢንዱስትሪ ፈንድ እንዲቋቋም ያደርጋል፣ ሲፈቀድም ሥራ ላይ ያውላል፤
፲፬) የመንግስት ድርሻ ያላቸው የአክሲዮን ማህበራት ትርፍና በየጊዜው ወደ ልማትና ኢንዱስትሪ ፈንድ ፈሠስ መሆኑን ይከታተላል፣ ያስፈፅማል፤
፲፭) የልማት ደርጅቶች አላማና ተልዕኮዋቸውን ከግብ ማድረስ እንዲችሉ የማስፈፀም አቅማቸው የሚጠናከርበትን ሁኔታ ያጠናል፣ የጥናቱን ውጤት ለመንግስት ያቀርባል፣ ሲወሰንም ሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፤
፲፮) ባላቸው ካፒታልና አመሰራረታቸው ላይ በመመስረት የልማት ድርጅቶችን ደረጃ ይወስናል፤
፲፯) ድርጅቶች የተመሰረቱበትን አላማ ከግብ ለማድረስና ለኢንዱስትሪ ሽግግር ግብዓት ሊሆኑ የሚችሉ ኢንቨስትመንቶችን በማጥናት እንዲሣተፉባቸው ያደርጋል፤
፲፰) ውጤታማና በአገራችንና ክልላችን የኢኮኖሚ ዕድገት ውስጥ ስትራተጂካዊ የሆኑ አክሲዮኖችን በማጥናት መንግስትን በመወከል የአክሲዮን ግዢ ያካሄዳል፣ የልማት ድርጅቶች እንዲሣተፉበትም ያደርጋል፤ ሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል

8) Propose the chairperson and board members of the public enterprises to the president of the region for assignment ; fallow-up their work performances;
9) Study and cause the implementation of the allowance payments of board members and the effect based incentive system of the board members and heads of public enterprises; follow- up its execution;
10) Approve the assignment of external auditors of public enterprises;
11) Approve the financial reports of public enterprises made by external auditors;
12) Study and implement the net profit in percentage to be flowed periodically to the government treasury form the public enterprises;
13) Cause the establishment of the development and industry fund of public enterprises and implement up on its approval;
14) Follow up that the profit of the ax ion associations in which the government has shares to be periodically funded in to the development and industry fund; cause its execution;
15) Undertake study about the ways of building the performance capacities of public enterprises so as to enable them achieve their objectives and missions; submit the findings of the study to the government; follow-up its implementation up on approval;
16) Decide the standard of public enterprises depending on the capital they own and nature of their creation;
17) Study investments which may be imputes for the achievements of objectives of enterprises and for transition of industry and make them take part on it;
18) Identify and conduct purchase of ax ions which are effective and strategic in the economic developments of the country and our region on behalf the government; cause the public enterprise to participate on same; follow- up its implementation;

19) Abbootii qabeeyaa mootummaa waliin hojii Investimentii gaggeessuuf yaada pirojektii dhiyeessan qoratee qaama dhimmi ilaaluuf ni dhiyeessa; yammuu mirkanaa'uu hojiirra akka oolu ni taasiisa; hojiirra oolmaa isaa ni hordofa; ni too'ata;
20) Yaa'ii waldaalee abbootii aksiyoonaa mootummaan qooda keessaa qabu irratti mootummaa bakka bu'ee ni hirmaata;
21) Karoora bittaa qabeenya dhaabbii gurguddoo hojii dhaabbatichaaf murteessaa ta'an akka mirkanaa'u mootummaaf ni dhiyeessa; yoo mirkanaa'e ni raawwachiisa; Tarreeffamni isaa Dambii bahuun kan murtaa'u ta'a;
22) Herregni dhaabbilee misoomaa mootummaa galmeerraa haala itti haqamuu danda'u irratti qaama dhimmi ilaalu waliin ni hojjata; raawwii isaa ni hordofa;
23) Qabeenya dulloomanii fi tajaajilaan ala ta'an, kanneen bitamanii hojii malee jiranii fi hojii dhaabbilee misoomaa mootummaatiif barbaachisaa hin taane qaama dhimmi ilaaluuf dhiyaatanii akka maqfaman yookiin akka gurguraman ni taasiisa; raawwii isaa ni hordofa;
24) Gaaffii hojjattootaa fi miseensota manajimantii dhaabbilee misoomaa daangaa umurii sooramaa ol tajaajiluuf gaafatamu irratti bu'uura seeraatiin murtee ni kenna;
25) Dhaabilee misoomaa mootummaa walitti makuun yookiin gargar baasuun yookiin diiguun barbaachisaa ta'ee yoo argame qorannoo gad-fageenya qabu gaggeessuun yaada murtii mootummaaf ni dhiyeessa; yammuu hayyamamu hojiirra ni oolcha;
26) Hojiiwwan mirga abbaa qabeenyummaa mootummaa kabachiisan biroo ni raawwata.

**38. Abbaa Taayitaa Geejjibaa**

Abbaan Taayitichaa aangoo fi hojii armaan gadii ni qabaata:

1) Hojiin tajaajila geejjibaa bu'uura imaammataa, tarsiimoo fi seeraatiin qajeelfamuu isaa ni too'ata; deeggarsa barbaachisaa ni kenna;

፲፱) ከመንግስት ጋር የኢንቨስትመንት ሥራ ለማከሄድ የፕሮጀክት ሀሳብ ያቀረቡ ባለሐብቶችን በማጥናት ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፣ ሲፀድቅም ሥራ ላይ እንዲዉል ያደርጋል፤ ሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

፳) የመንግስት ድርሻ ያለባቸው የአክሲዮን ማህበራት ስብሰባ ላይ መንግስትን በመወከል ይሣተፋል፤

፳፩) ለድርጅቱ ሥራ ወሣኝ የሆኑ የግዙፍ ቋሚ ንብረቶች ግገር ዕቅድ እንዲፀድቅ ለመንግስት ያቀርባል፣ ሲፀድቅም ያስፈፅማል፤ ዝርዝሩ በሚወጣው ደንብ የሚወሰን ይሆናል፤

፳፪) የመንግስት ልማት ድርጅቶች ሒሳብ ከመዝገብ ላይ የሚሠረዝበትን ሁኔታ ላይ ከሚመለከተው አካል ጋር ይሠራል፤ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

፳፫) ያረጁና ከአገልግሎት ውጪ የሆኑ፤ ተገዝተው ያለስራ የተቀመጡና ለመንግስት የልማት ድርጅቶች አስፈላጊ ያልሆኑ ንብረቶች ለሚመለከተው አካል ቀርበዉ እንዲወገዱ ወይም እንዲሸጡ ያደርጋል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

፳፬) ከጡረታ ዕድሜ ገደብ በላይ ለማገልገል በልማት ድርጅቶች ሠራተኞችና የማኔጅመንት አባላት የሚቀርብ ጥያቄን አስመልክቶ በህጉ መሠረት ውሣኔ ይሠጣል፤

፳፭) የልማት ድርጅቶችን ማቀላቀል ወይም ማለያየት ወይም ማፍረስ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ጥልቀት ያለው ጥናት በማካሄድ የውሳኔ ሐሳብ ለመንግስት ያቀርባል፤ ሲፈቀድም ሥራ ላይ ያውላል፤

፳፮) የመንግስት የባለቤትነት መብት የሚያስከብሩ ሌሎች ሥራዎችን ያከናውናል፤

**፴፰. የትራንስፖርት ባለስልጣን**

ባለስልጣኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩) የትራንስፖርት አገልግሎት ሥራ በፖሊሲው፣ ስትራተጂውና በህጉ መሰረት መመራቱን ይቆጣጠራል፤ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሠጣል፤

19) Identify the private investors which have submitted project proposal for conducting investment activities with the government and submit to the concerned body; cause its implementation up on approval; follow-up and supervise its implementation;
20) Take part on the meetings of shareholders of ax ions associations in which the government has shares by representing the government;
21) Submit procurement plan of permanent and huge properties which are decisive for the activities of the enterprises to the government for approval; cause its implementation where approved; Its particulars shall be decided by the directive to be issued;
22) Work with the concerned body regarding the cancellation of the public enterprises' debts from the books of accounts;
23) Cause the properties which are old and un operational, purchased and remain without use and are not necessary for the activities of public enterprises to be delivered to the concerned body and be disposed or sold; follow -up its implementation;
24) Provide decision in accordance with the law on the requests for the authorization of retention of employees and members of the management of public enterprises in service beyond retirement age;
25) Carry out a thorough study and propose recommendation to the government where it is found necessary to amalgamate or divide or dissolve the public enterprises; implement same up on its approval;
26) Perform other activities which help to protect ownership rights of the government.

**38. Transport Authority**

The Authority shall have the following powers and duties:

1) Supervise that the transport service delivering activity to be directed in accordance with the policy, strategy and the laws; give the required support;

2) Hojiin tajaajila geejjibaa seeraan alaa akka hin raawwatamne ni too'ata; tarkaanfii seeraas ni fudhata; akka fudhatamu ni taasisa;
3) Sirni tajaajila geejjiba naannicha keessatti diriire haala waldeeggaree fi qindoomina qabuun akka hojiirra oolu ni taasisa;
4) Abbootii qabeenyaa tajaajila geejjiba deddeebisa ummataa fi fe'iinsaa irratti bobba'aniif hayyama tajaajila geejjibaa ni kenna; ni haaromsa; ni haqa; waldaan ni gurmeessa; hayyama waldaa ni kenna; ni haaromsa; ni haqa; ni deeggara; ni too'ata;
5) Teeknolojiiwwan tajaajila geejjibaaf oolan ni qorata; istaandardii ni baasa; ni gamaaggama; sirnaan akka hojiirra oolu ni taasisa;
6) Tajaajilli geejjibaa naannolee biroo waliin taasifamu akkaataa itti waldeeggaru, babal'atuu fi cimu irratti haala mijaa'aa ni uuma;
7) Konkolaattota abbaa motoraa, motora dhabeeyyii fi humna beeyiladaatiin harkifaman akkasumas bidiruuwwan naannicha keessatti argaman ni galmeessa; ragaa abbaa qabeenyummaa ni kenna; ni too'ata;
8) Gahumsa konkolaachistootaa, kaapiteenotaa, konkolaattotaa fi bidiruuwwanii ni mirkanneessa; akkaataa barbaachiisummaa isaattis qaama gahumsa kana akka mirkanneessaniif dhaabbilee yookiin jaarmiyaalee hayyama qabanii fi gahumsa mirkanneessuu danda'aniif bakka bu'iinsa ni kenna; ni hordofa;
9) Tajaajila tilmaama gatii konkolaataa fi jijjiirraa maqaa abbaa qabeenyaa ni raawwata; waliigaltee bittaa fi gurgurtaa yookiin kennaa konkolaataa, waliigaltee kiraa konkolaataa, konkolaattota wabiin qabaman ni galmeessa; ni eega;
10) Hojimaata tajaajilli geejjibaa ittiin hoogganamu ni diriirsa; haala ni mijeessa; hojimaata dorgommii bobbii bilisaa akka hojiirra oolu ni taasisa; ni hordofa; qorannoo taarifaa gaggeessuun ka'umsaa fi fiixee taarifa tajaajila geejjibaa ni murteessa; raawwii isaa ni hordofa;

፪) ህገወጥ የትራንስፖርት አገልግሎት እንዳይፈፀም ይቆጣጠራል፤ ህጋዊ እርምጃም ይወስዳል፤ እንዲወሰድ ያደርጋል፤
፫) በክልሉ ውስጥ የተዘረጋው የትራንስፖርት አገልግሎት ሥርዓት በተደጋገፈና በተቀናጀ ሁኔታ ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤
፬) በህዝብ ማመላለሻና በጭነት ትራንስፖርት አገልግሎት ላይ ለተሰማሩ ባለሀብቶች የትራንስፖርት አገልግሎት ፍቃድ ይሰጣል፣ ያድሣል፣ ይሰርዛል፣ በማህበር ያደረጃል፣ የማህበሩ ፍቃድ ይሠጣል፤ ያድሣል፤ ይሰርዛል፤ ይደግፋል፣ ይቆጣጠራል፤
፭) ለትራንስፖርት አገልግሎት የሚውሉ ቴክኖሎጂዎችን ያጠናል፤ ስታንዳርድ ያወጣል፤ ይገመግማል፣ በአግባቡ ተግባር ላይ እንዲውል ያደርጋል፤
፮) ከሌሎች ክልሎች ጋር የሚደረገው የትራንስፖርት አገልግሎት የሚደጋገፍበትን፣ የሚስፋፋበትንና የሚጠናከርበትን ላይ አመቺ ሁኔታን ይፈጥራል፤
፯) ባለሞተር ፣ ሞተር የሌላቸውና በእንስሳት የሚጎተቱ ተሽከርካሪዎች እንዲሁም በክልሉ የሚገኙ ጀልባዎችን ይመዘግባል፤ የባለቤትነት ማስረጃ ይሰጣል፤ ይቆጣጠራል፤
፰) የአሽከርካሪዎችን፣ የካፒቴኖችን፣ የተሽከርካሪዎችን እና የጀልባዎችን ብቃት ያረጋግጣል፣ እንዳስፈላጊነቱም ይህን ተቋም እንዲያረጋግጡ ፍቃድ ላላቸውና ብቃት ማረጋገጥ ለሚችሉ ተቋማት ወይም ድርጅቶች ውክልና ይሠጣል፣ ይከታተላል፤
፱) የመኪና ዋጋ መገመትና የንብረት ባለቤትነት ሥም ማዘዋወር አገልግሎት ይፈፅማል፣ የግዢና ሽያጭ ወይም የመኪና ስጦታ ዉል፣ የመኪና ኪራይ ዉል፣ በዋስትና የተያዙ መኪናዎችን ይመዘግባል፣ ይጠብቃል፤
፲) የትራንስፖርት አገልግሎት የሚመራበትን አሠራር ይዘረጋል፣ ሁኔታን ያመቻቻል፤ የነፃ ሥምሪት ውድድር ሥርዓት ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤ ይከታተላል፤ የታሪፍ ጥናት በማካሄድ የትራንስፖርት አገልግሎት የመነሻና ከፍተኛ ታሪፍ ይወስናል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

2) Control the illegal transport service activity; take or cause to be taken lawful measures;
3) Cause the transport service system extended in the region to be implemented in an integrated and coordinated manner;
4) Issue transport service license for the private investors engaged in transport of people and goods services; renew; cancel; set standards; organize in associations, issue license for the association; renew; cancel; support and supervise;
5) Study the technologies used for transport purposes; set standards, evaluate; make it to be implemented properly;
6) Create conducive atmosphere of the ways that the transport service made with other regions be cooperative, expanded, and strengthened;
7) Register the motor vehicles, non-motor vehicles, those pulled by animals, as well as the boats in the region; provide ownership evidence; and supervise them;
8) Approve the competency of the drivers, captains, vehicles and boats; or give delegation to other bodies to perform such approval to the institutes or organizations having licenses and competencies as deemed necessary; perform following up activity;
9) Perform price valuation of vehicles and transfer of title deed services; register contracts of purchase and sale or donation of vehicles; and contracts of rents of vehicles as well as vehicles attached in surety, protect them;
10) Establish a system whereby the transport service be directed or guided; facilitate enabling conditions; cause the free deployment competition to be implemented; follow- up; undertake study about tariff and determine the baseline and ceiling tariff price of transportation service; follows-up its implementation;

11) Hojii too'annoo sochii tiraafika geejjiba daandii ni raawwata; raawwii isaa ni hordofa; hojiilee too'annoo nageenya tiraafikaa naannicha keessatti gaggeeffaman qaama dhimmi ilaalu waliin ni hojjeta; ni hooggana; balaa tiraafikaa ilaalchisee qo'annoo ni gaggeessa;

12) Fandii sochii nageenya tiraafikaa fi hojii geejjibaa ilaallatu kamiiyyuu naannicha keessaa fi qaama adda addaa irraa haala itti argamu ni uuma; kan argames kaayyoo barbaadameef hojiirra akka oolu ni taasisa;

13) Naannicha keessatti uwwisni tajaajila geejjibaa gahaa fi bobbiin akka jiraatu ni taasisa; sagantaa bobbii waldaalee geejjibaa fi namoota dhuunfaa tajaajila geejjiba ummataa fi fe'iinsaa irratti bobba'anii qoratee ni mirkaneessa; ni fooyyessa; hojiirra oolmaa isaas ni hordofa; bakka hanqinni argamettis tarkaanfii sirreeffamaa ni fudhata;

14) Gahumsa oppireetaroota geejjibaa ni mirkanneessa; hayyama ni kenna; waliigaltee oppireetaroota gidduutti taasifamu ni galmeessa; tarkaanfii sirreeffamaa ni fudhata;

15) Dhaabbilee meeshaalee tajaajila geejjibaaf oolan oomishan, suphanii fi haaromsan, akkasumas qulqulleessa konkolaataa irratti bobba'anii fi leenjii ogummaa konkolaachisummaa kennaniif waraqaa gahumsa ogummaa mirkanneessu ni kenna; ni haaromsa; ni too'ata; ni haqa;

16) Dhaabbilee leenjii ogummaa konkolaachisummaa kennaniif ulaagaa leenjiin ittiin kennamu ni qopheessa; hojiirra ooluu isaa ni hordofa; bakka hanqinni jirutti tarkaanfii sirreeffamaa ni fudhata;

17) Leenjifamtoota dhaabbilee leenjii konkolaachisummaa irraa leenji'anii bahaniif qormaata gahumsaa ni kenna; kanneen qormaata darbaniif hayyama konkolaachisummaa sadarkaa adda addaa ni kenna; ni haaromsa; ni too'ata; ni haqa;

፲፩) የመንገድ የትራንስፖርት ትራፊክ እንቅስቃሴ ቁጥጥር ሥራ ይፈፅማል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን በክልሉ ውስጥ የሚካሄዱትን የትራፊክ ደህንነት ቁጥጥር ሥራዎችን ይሠራል፤ ይመራል፤ የትራፊክ አደጋን በተመለከተ ጥናት ያካሄደል፤

፲፪) የትራፊክ ደህንነት እንቅስቃሴና የትራንስፖርት ሥራን የሚመለከት ማንኛውም ፈንድ ከክልሉ ውስጥና ከተለያየ አካላት ላይ የሚገኝበትን ሁኔታ ይፈጥራል፤ የተገኘውንም ለተፈለገዉ አላማ እንዲውል ያደርጋል፤

፲፫) በክልሉ ውስጥ በቂ የትራንስፖርት አገልግሎት ሽፋንና ሥምሪት እንዲኖር ያደርጋል፣ በህዝብ ትራንስፖርትና ጭነት አገልግሎት ላይ የተሰማሩ የትራንስፖርት ማህበራትና ግለሰቦች ሥምሪት ፕሮግራም በማጥናት ያረጋግጣል፤ ያሻሽላል፣ ሥራ ላይ መዋሉንም ይከታተላል፤ ውሱንነት በተገኘበት ቦታም የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፤

፲፬) የትራንስፖርት ኦፕሬተሮች ብቃትን ያረጋግጣል፣ ፍቃድ ይሰጣል፣ በኦፕሬተሮች መካከል የሚደረገውን ውል ይመዘግባል፤ የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፤

፲፭) ለትራንስፖርት አገልግሎት የሚውሉ መሣሪያዎችን ለሚያመርቱ፣ ለሚጠግኑና ለሚያድሱ እንዲሁም በመኪና ፅዳት ላይ ለተሰማሩና የአሽከርካሪነት ሙያ ስልጠና ለሚሰጡ ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ይቆጣጠራል፣ ይሰርዛል፤

፲፮) የአሽከርካሪነት ሙያ ስልጠና ለሚሰጡት ተቋማት ሥልጠና የሚሰጥበትን መስፈርት ያዘጋጃል፤ ሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፤ ግድፈት ባለበት ቦታ የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፤

፲፯) ከአሽከርካሪነት ሙያ ማሰልጠኛ ተቋማት ሰልጥነው ለሚወጡ ሠልጠኞች የብቃት ማረጋገጫ ፈተና ይሠጣል፤ ፈተናውን ላለፉት የተለያየ ደረጃ የአሽከርካሪነት ፍቃድ ይሠጣል፤ ያድሣል፤ ይቆጣጠራል፤ይሰርዛል፤

11) Perform the road transport traffic controlling activity; follows-up its implementation; perform the supervision of transport traffic peace activities carried out in the region in collaboration with other bodies; directs same; undertake studies regarding traffic accidents;

12) Create mechanisms of obtaining funds for traffic peace ensuring activities and for any activity related to transport from within the region and from various bodies; cause the acquired one to be used for the objective it is required;

13) Cause the prevalence of adequate transport service coverage and deployment in the region; study and approve the deployment program of transport associations and private persons engaged in public and goods transport service; amends; follows-up its implementation; and take rectifying measures where there occurs limitation;

14) Approve the competency of transport operators; issue license, register the contracts concluded amongst the operators; take rectifying measures;

15) Provide professional competency certificate for the institutions engaged in the production, maintenance and renewal of materials used for transport services as well as those engaged in car wash activities and those who provide driving profession trainings; renew; supervise and cancel such license;

16) Prepare training criteria for the institutions which provide drivers profession trainings; follow-up its implementation, take rectifying measures where there is limitation;

17) Provide competency examination for the graduates from the driving skill training institutions; provide driving licenses of different levels for those who pass the examination; renew; supervise and cancel same;

18) Buufata konkolaataa fi bidiruu, tarminaala fe'umsaa, paarkiingii, giddugala leenjii fi qormaataa istaandaardii ni baasa; qaama dhimmi ilaallatu waliin ni ijaara; akka ijaaraman ni taasisa; kenniinsa tajaajila isaanii ol'aantummaan ni hooggana; ni too'ata;
19) Bittaa konkolaataa mootummaa fi jaarmiyaalee ummataa ilaalchisee deeggarsa ogummaa ni kenna;
20) Haalli dirqisiisaan yoo muudate iddoo fi sarara barbaadame irratti waldaalee yookiin jaarmiyaalee geejjibaaf bobbii ni kenna; haalli raawwii isaa dambii bahuun kan murtaa'u ta'a;
21) Dhaabbilee gahumsa konkolaataa sakatta'aniif hayyama ni kenna; ni haaromsa; ni too'ata; ni haqa;
22) Ragaalee istaastiksii fi odeeffannoo kan biroo geejjiba naannichaa ilaallatan kamiyyuu dhaabbiidhaan ni sassaaba; ni qindeessa;
23) Geejjibni naannichaa akka hammayyaa'uu fi babal'atu qo'annoo fi qorannoo ni gaggeessa; akka gaggeeffamu ni taasisa; bu'aan qorannichaa yammuu mirkanaa'u hojiirra akka oolu ni taasisa;
24) Konkolaattota, bidiruuwwanii fi kanneen biroo tajaajila geejjibaan walqabatan keessaa aara, gaazii, hurkaa fi wantootni biroo naannoo faalan xiqqeessuuf qaama dhimmi ilaalu waliin ni hojjata;
25) Sirna konkolaattotnii fi bidiruwwaan irra deebiidhaan itti hojjataman ni diriirsa; hojiirra akka oolu ni taasisa.

## 39 Abbaa Taayitaa Misooma Jallisii

Abbaan Taayitichaa aangoo fi hojii armaan gadii ni qabaata:

1) Imaammata, tarsiimoo, sagantaalee fi seerota misooma jallisii ilaallatan qopheessuun mootummaaf ni dhiyeessa; yammuu hayyamamu hojiirra ni oolcha;
2) Dizaayinii ijaarsa iskiimota jallisii kamiyyuu ni qopheessa; akka qophaa'u ni taasisa; qaama dhimmi ilaallatuun yammuu mirkanaa'u hojiirra ni oolcha; qo'annoo ijaarsa iskiimota jallisii ni gaggeessa; akka gaggeeffamu ni taasisa;

፲፰) የተሽከርካሪና የጀልባ ጣቢያ፣ የጭነት ተርሚናል፣ ፓርኪንግ፣ የሥልጠና ማዕከልና ፈተና ስታንዳርድ ያወጣል፤ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን ይገነባል፤ እንዲገነቡ ያደርጋል፤ የአገልግሎት አሰጣጣቸውን በበላይነት ይመራል፣ ይቆጣጣራል፤
፲፱) የመንግስትና የህዝባዊ ድርጅቶች ተሽከርካሪዎች ግዢን በተመለከተ የሙያ ድጋፍ ይሰጣል፤
፳) አስገዳጅ ሁኔታ ካጋጠመ፣ በሚፈለገው ቦታና መስመር ላይ ለትራንስፖርት ማህበራት ወይም ድርጅቶች ስምሪት ይሰጣል፤ አፈፃፀሙ በሚወጣው ደንብ የሚወሰን ይሆናል፤
፳፩) የተሽከርካሪዎችን ብቃት ለሚመረምሩ ተቋማት ፍቃድ ይሠጣል፤ ያድሳል፤ ይቆጣጠራል፤ ይሰርዛል፤
፳፪) የክልሉን ትራንስፖርት የሚመለከቱ ማንኛውም ስታትስቲካዊ ማስረጃዎችና ሌሎች መረጃዎችን በመደበኛነት ይሰበስባል፤ ያቀናጃል፤
፳፫) የክልሉ ትራንስፖርት እንዲዘምንና እንዲስፋፋ ጥናትና ምርምር ያካሄዳል፤ እንዲካሄድ ያደርጋል፤ የጥናቱ ውጤት ሲፀድቅም ስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤
፳፬) ከተሽከርካሪዎች፣ ጀልባዎች እና ሌሎች ከትራንስፖርት አገልግሎት ጋር ተያየዥነት ካላቸው ነገሮች የሚወጣ ጢስ፣ ጋዝ፣ ትነትና ሌሎች አካባቢን የሚበክሉ ነገሮችን ለመቀነስ ከሚመለከተው አካል ጋር ይሠራል፤
፳፭) ተሽከርካሪዎችና ጀልባዎች እንደገና የሚሰሩበትን ሥርዓት ይዘረጋል፣ ስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል።

## ፴፱. የመስኖ ልማት ባለስልጣን

ባለሥልጣኑ የሚከተሉትን ሥልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩) የመስኖ ልማትን የሚመለከቱ ፖሊሲዎች፣ እስትራቴጂዎች፤ ፕሮግራሞችንና ህጎችን በማዘጋጀት ለመንግሥት ያቀርባል፤ ሲፈቀድም ሥራ ላይ ያውላል።
፪) የመስኖ አዉታር ግንባታ ዲዛይን ያዘጋጃል፤ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፣ በሚመለከተዉ አካል ስፀድቅ ሥራ ላይ ያዉላል፤ የመስኖ አውታር ግንባታ ጥናት ያካሄዳል፣ እንዲካሄድ ያደርጋል፤

18) Prepare standards for vehicles and boats stations; loading terminals, parking areas training and examination centers; construct; cause them to be constructed with the concerned body; leads and supervises their service delivery activities;
19) Provide professional support regarding procurement of government and public organizations' vehicles;
20) Give transport deployment for transport associations or organizations towards the intended places and routes where there encountered force majeure; Its particulars shall be decided by the regulation to be issued;
21) Issue license for vehicles competency examining institutions; renew; supervise; cancel same;
22) Collect and analyze any statistical evidences and other information related to transportation service of the region permanently;
23) Undertake; cause to be undertaken research and study for the modernization and promotion of transport of the region; cause the implementation of the findings of the study up on its approval;
24) Work with the concerned body for the minimization of smokes, gases, steams and other environmental pollutants released out of the vehicles, boats and others related to transport services;
25) Establish a system whereby the vehicles and boats be re-manufactured; cause it to be implemented.

## 39. Irrigation Development Authority

The Authority shall have the following power and duties:

1) Prepare and submit policies, strategies, programs and laws related to irrigation to the government and implement same upon approval;
2) Undertake and cause to be undertaken any irrigation schemes construction design; implement same upon approval by concerned body, undertake or cause to be undertaken study of irrigation schemes construction;

3) Jallisii giddugaleessaa fi gurguddaa ijaarsi isaanii xumurame hanga itti fayyadamtoonni of danda'anii bulchanitti guutummaa guutuutti ni bulcha; ni hordofa; hojii teeknikaa ni raawwata; suphaa humna fayyadamtoota jallisii ol ta'e ni raawwata; ni raawwachiisa; yeroo itti fayyadamtootni of danda'an dabarsee ni kenna;
4) Bu'a qabeessummaa iskiimoota jallisii guddisuuf fayyadamtootni hubannoo baasii, kunuunsa, bulchiinsaa fi suphaa qabaatanii maallaqa akka qusatan ni gorsa; ni hordofa; akkasumas deeggarsa barbaachisaa ni kenna;
5) Qabeenya bishaanii naannicha keessatti argaman haala itti fufiinsa qabuun misooma jallisiitiif akka ooluu danda'an qaama dhimmi ilaalu waliin kunuunsa isaanii irratti ni hojjata;
6) Hojii qoorsa lafa naannicha keessatti iddoo barbaachisaa ta'etti ni hojjata;
7) Hojii bishaan cimmisuu misooma jallisiif oolu irratti ni hojjata;
8) Rakkoolee misooma jallisii fi qoorsa lafaa, akkasumas teeknolojii misooma jallisii irratti qo'annoo ni gaggeessa; akka gaggeeffamu ni taasisa; ni qindeessa; bu'aa qo'annoo fi teeknolojiiwwan fooyya'aa naannicha keessatti ni balbal'isa; iddoo hojjatanii itti agarsiisan ni qopheessa;
9) Jallisii maayikiroo fi jallisii bonee ummataan akka hojjataman abbummaadhaan ni hordofa; ni deeggara; ni jajjabeessa;
10) Qaamolee guddinaa fi itti fufiinsa misooma jallisiif bu'aa buusuu danda'an waliin ni hojjata;
11) Fandii arjoomtota irraa misooma jallisiitiif gargaarsaan yookiin liqiidhaan argamu dhimma barbaadameef akka oolu ni hordofa; ni bulcha; raawwii isaa qaama ilaallatuuf ni gabaasa;
12) Jallisiiwwan xixiqqaa ijaarsi isaanii xumurame itti fayyadamtootaatti dabarsee ni kenna; bulchiinsaa fi itti fayyadama irratti deeggarsa teeknikaa ni taasisa; ni hordofa; suphaa humna fayyadamtoota jallisii ol ta'e ni raawwata; ni raawwachiisa;

፫) ግንባታቸው የተጠናቀቀ መካከለኛና ትላልቅ የመስኖ አዉታሮችን ተጠቃሚዎች ራሳቸው ማስተዳድር እስከሚችሉ ድረስ ሙሉ በሙሉ ያስተዳድራል፤ ይከታተላል፣ የቴክኒክ ሥራ ይሰራል፤ ከተጠቃሚዎች አቅም በላይ የሆነ ጥገናን ያከናውናል፤ እንዲከናወን ያደርጋል፤ ተጠቃሚዎች ራሳቸውን ሲችሉ ወደነርሱ ያስተላልፋል፤
፬) የመስኖ አውታሩን ዉጤታማነት ለማሳደግ ተጠቃሚዎች ስለ ወጪ፣ እንክብካቤ፣ አስተዳደርና ጥገና ግንዛቤ ኖሯቸው ገንዘብ እንዲቆጥቡ ይመክራል፤ ይከታተላል፤ እነዱሁም አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤
፭) በክልሉ ውስጥ የሚገኙትን የውሀ ሀብት ቀጣይነት ላለው የመሥኖ ልማት ሊውል እንዲችል ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን በእንክብካቤያቸዉ ልይ ይሰራል፤
፮) በክልሉ ውስጥ የመሬት ማንጣፈፍ ሥራ በሚያስፈልግበት ቦታ ላይ ይሰራል፤
፯) ለመስኖ ልማት የሚውል የውሀ ማቆር ሥራ ላይ ይሰራል፤
፰) ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን በክልሉ የመስኖ ልማትና መሬት ማንጣፈፍ ችግሮች ላይ እንደዚሁም በመስኖ ልማት ቴክኖሎጂ ላይ ጥናት ያካሄዳል፤ እንድካሄድ ያረጋል፤ ያቀናጃል፤ የጥናትና የተሻሻሉ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን በክልሉ ውስጥ ያስፋፋል፤ የሰርቶ ማሳያ ቦታዎችን ያዘጋጃል፤
፱) የጥቃቅን መስኖና እርጥበት አዘል መስኖ ልማት በህብረተሰቡ እንዲሰራ በባለቤትነት ይከታተላል፤ ያግዛል፤ ያበረታታል ፤
፲) ለመስኖ ልማት እድገትና ቀጣይነት ሥራ አስተዋፅዖ ማድረግ ከሚችሉ አካላት ጋር ይሰራል፡፡
፲፩) ለመስኖ ልማት የሚውል በእርዳታ ወይም በብድር የሚገኝ ፈንድ ለታሰበለት አላማ መዋሉን ይከታተላል፤ ያስተዳድራል፤ አፈፃፀሙንም ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ያደርጋል፤
፲፪) ግንባታቸው የተጠናቀቁ አነስተኛ መስኖዎችን ለተጠቃሚዎች አሳልፎ ይሰጣል፤ አስተዳደርና አጠቃቀም ላይ የቴክኒክ ድጋፍ ያደርጋል፣ ይከታተላል፣ ከተጠቃሚዎች አቅም በላይ የሆነ ጥገናን ያከናውናል፣ እንዲከናወን ያደርጋል፡፡

3) Fully administer, follow up, execute technical work of medium and large scale irrigations whose construction is completed until the users are self-sufficient to administer; conduct or cause the conduct of maintenance work which is beyond the capacity of the users, and turn the administration over to them when they are self-sufficient;
4) Advise; follow up and provide necessary support for the beneficiaries in order to create their awareness on expenditure, preservation, administration and maintenance for the effectiveness of irrigation schemes; and thereby save money; follow up and give necessary support;
5) Work in collaboration with concerned body on the conservation of water resources in the region with a view to enable them be used for sustainable irrigation development purposes;
6) Undertake drainage work where it is necessary in the region;
7) Undertake water harvesting activity for irrigation development;
8) Undertake a study with the concerned body on problems related with areas of irrigation development, drainage, and on irrigation technology; coordinate; disseminate research findings and improved technology; prepare demonstration plots;
9) Take the responsibility of following up, supporting, motivating for the micro and moisture irrigations to be undertaken by people;
10) Work in collaboration with the bodies who contribute to the growth and sustainability of irrigation development;
11) Follow up, administer, irrigation development funds obtained from different funding agencies as a grant to be utilized for the intended purpose and report its implementation to concerned bodies;
12) Handover small scale irrigation projects whose construction is completed to users, provide technical support, follow up, conduct, cause to be conducted maintenance where is beyond the capacity of the users;

13) Uwwisa misooma qonna jallisii fi qoorsa lafaa guddisuudhaaf akka danda'amu maddi baajataa karaa ittiin argamuu danda'u tooftaa adda addaa fayyadamuudhaan ni barbaada;
14) Baasii ijaarsa pirojektii jallisiif bahe itti fayyadamtootaan akka bakka bu'u ni taasisa; Mootummaa hayyamsiisee pirojektii jallisii birootiif ni oolcha; kaffaltii tajaajila adda addaatiif suphaa ni sassaaba; deebisee hojiirra ni oolcha;
15) Teeknolojiiwwan misooma qonna jallisii saffisiisuu danda'an ni filata; kanneen dhiyaatan irratti qulqullina isaanii ilaalchisee qaama dhimmi ilaalu waliin ni hojjata;
16) Hojii ekisteenshinii fi tajaajila gorsa misooma qonna jallisii ni babal'isa;
17) Hojiilee muuxannoo gaarii misooma qonna jallisii sadarkaa hundatti raawwataman addaan ni baasa; ni galmeessa; akka babal'atu ni hojjata;
18) Hirmaannaa ummataa misooma qonna jallisii irratti qabu ni jajjabeessa;
19) Waldaalee itti fayyadamtoota bishaan jallisii ni gurmeessa; ni leenjisa; dambii ittiin bulmaataa akka qopheeffatan ni gargaara; ni hordofa; akkaasumas qaama seerummaa akka argatan qaama dhimmi ilaalu waliin ni hojjata;
20) Dubartootnii fi dargaggootni hojii misooma qonna jallisii keessatti qooda fudhattootaa fi fayyadamtoota akka ta'an ni hojjata; haala ni mijeessa;
21) Qaamolee misooma qonna jallisii irratti bobba'aniif hordoffii fi deeggarsa ogummaa barbaachisu ni kenna;
22) Miidhaa pirojektootni misooma qonna jallisii naannoo fi fayyaa namaa irratti fiduu danda'an xiqqeessuudhaaf qaama dhimmi ilaalu waliin ni hojjata;
23) Hojii misooma qonna jallisii fi qoorsa lafaa sadarkaa hundaa irratti raawwatamu bu'aa fi rakkoo isaa ni xiinxala;

፲፫) የመስኖ እርሻ ልማት እና የመሬት ማንጣፈፍ ሽፋን ለማሳደግ እንዲቻል የተለያየ ዘዴ በመጠቀም የበጀት ምንጭ የሚገኝበትን መንገድ ያፈላልጋል፤
፲፬) ለመስኖ ግንባታ ፕሮጀክት የወጣ ወጪ በተጠቃሚዎች እንድተካ ያደርጋል፤ መንግስትን በማስፈቀድ ለሌላ የመስኖ ፕሮጀክት ያዉላል፤ ለተለያዩ አገልግሎትና ጥገና ክፍያ ይሰበስባል፤ መልሶ ሥራ ላይ ያዉላል፤
9) Karoora itti fayyadama lafaa irratti hundaa'uun akaakuu pirojektoota investimentii naannicha keessatti gaggeeffamuu danda'an qoratee qaama dhimmi ilaaluuf ni dhiyeessa; yammuu hayyamamu hojiirra akka oolu ni taasisa;
10) Gaaffii jijjiirraa gosa pirojektootaa investimentii lafa baadiyyaa irratti dhiyaatu ni raawwata;
11) Waliigaltee pirojektoota investimentii gurguddaa Boordii Investimentii yookiin Mana Maree Bulchiinsa Mootummaa Naannichaatiin murtaa'an ni mallateessa; ni galmeessa; ni hordofa; haalli raawwii isaa Dambii bahuun kan murtaa'u ta'a;
12) Gaaffii pirojektoota investimentii naannichaaf faayidaa ol'aanaa qaban simachuun Boordii Investimentii Naannichaatiif ni dhiyeessa; yammuu murtaa'u hojiirra akka oolu ni taasiisa; hojiirra oolmaa isaa ni hordofa; akkaataa waliigalteetiin yoo hojiirra hin oolle tarkaanfii sirreeffamaa ni fudhata; akka fudhatamu ni taasiisa;

፭) በኢንቨስትመንት ሥራ ላይ መሰማራት ለሚፈልጉ ሰዎች የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ከክልሉ ገቢዎች ባለስልጣን መስጠቱን በማረጋገጥ የኢንቨስትመንት ፍቃድ ይሰጣል፤ያድሳል፤ ይሰርዛል፤ በሕገ ወጥ እንቅስቃሴ ላይ የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፤ እንዲወሰድ ያደርጋል፤
፮) ለኢንቨስትመንት የተሰጠ መሬት በኢንቨስትመንት ሕግና በተፈፀመዉ ውል መሠረት መከናወኑን ከሚመለከተዉ አካል ጋር በመሆን ይከታተላል፤ ያቀናጃል፤ ኢንቨስተሮችን የሚያጋጥሙ ችግሮች መፍትሄ የሚያገኙበት አግባብ ላይ ከሚመለከተዉ አካል ጋር ይሠራል፤
፯) ጉዳዩ በሚመለከተው አካል የተዘጋጀ የኢንቨስትመንት መሬት መረጃ አጠናቅሮ ይይዛል፣ መሠረተ ልማት መሟቱን በማረጋገጥ የማስታወቂያ ሥራ ይሠራል፤
፰) ኢንቨስተሮች በፍጥነት መሬትን በሚያገኙበት ሁኔታን አስመልክቶ ጉዳዩ ከሚመለከተው አካል ጋር ይሰራል፤
፱) በመሬት አጠቃቀም ዕቅድ ላይ በመመስረት በክልሉ ዉስጥ ሊካሄዱ የሚችሉ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ዓይነትን አጥንቶ ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤
፲) በገጠር መሬት ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ዓይነት ለውጥ ላይ የሚቀርብ ጥያቄን ይፈጽማል፤
፲፩) በክልሉ ኢንቨስትመንት ቦርድ ወይም በክልሉ መንግስት መስተዳደር ምክር ቤት የሚወሰኑትን ትላልቅ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን ስምምነት ይፈርማል፣ ይመዘግባል፣ ይከታተላል፤ የአፈፃፀሙ ሁኔታ በሚያወጣው ደንብ የሚወሰን ይሆናል፤
፲፪) ለክልሉ ከፍተኛ ጥቅም ያላቸዉን የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ጥያቄን በማስተናገድ ለክልሉ ኢንቨስትመንት ቦርድ ያቀርባል፤ ሲወሰን ሥራ ላይ እንዲዉል ያደርጋል፤ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤ በውሉ መሠረት ሥራ ላይ ካልዋለ የእርምት እርምጃ ይወስዳል፤ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

5) Give, renew and cancel investment license for those persons who intend to engage in investment activities by ensuring that they obtained tax payers special number from regional revenue authority, take corrective measures or cause to be taken on illegal activities;
6) Organize and follow up with concerned body that the land given for investment activities are implemented based on investment law and agreement entered; work with concerned body on the condition by which problems encountered investors get solution;
7) Organize and keep data regarding land prepared for investment activities and submitted to it by concerned body; work promotion activity by ensuring the fulfillment of infrastructure;
8) Works with concerned body regarding conditions through which investors get land expeditiously;
9) study and submit to concerned body the type of investment projects that can be undertaken in the region based on land use plan, cause to be implemented based when approved;
10) implement request for change of investment project type with concerned body;
11) Sign, register, and follow up investment contract agreements regarding huge investment projects decided by investment board of the region. Its implementation shall be determined by regulation issued by the regional administration council;
12) Accept and submit to investment board or regional administration council the request for investment project that have special importance for the region; cause to be implemented when decided; follow up its implementation; take or cause to be taken corrective measure when it is not performed according to the agreement;

13) Abbootii qabeenyaa akkaataa seeraatiin lafa baadiyyaa hojii investimentiitiif fudhatan bulchiinsa Godinaalee yookiin Aanaalee waliin waliigaltee akka mallatteessan ni taasiisa; waliigaltee mallattaa'e ni galmeessa; haalli raawwii isaa Dambii bahuun kan murtaa'u ta'a;

14) Lafa investimentii magaalaa fi baadiyyaa qaamolee dhimmi ilaaluun qophaa'an bulchiinsa sadarkaa sadarkaan jiran waliin hojii beeksisaa ni raawwata;

15) Bal'ina lafa investimentii investeronni fudhatan akkaataa waliigalteetiin ta'uu isaa qaamolee dhimmi ilaalu waliin ni hordofa; bakka hanqinni jirutti qaama dhimmi ilaallatu waliin tarkaanfii sirreeffamaa ni fudhata; akka fudhatamu ni taasisa;

16) Hayyama investimentii kennuun dura pirojektootni investimentii qophaa'anii dhiyaatan naannoo fi fayyaa namaa irratti dhiibbaa kan hin dhaqqabsiifne ta'uu isaanii sakatta'iinsi dhiibbaa naannoo qaama dhimmi ilaallatuun gaggeeffamuu isaa ni mirkaneeffata; kan fudhatama argataniif hayyama ni kenna;

17) Dizaayinii ijaarsa pirojektoota investimentii mirkanaa'an ni galmeessa; qaama dhimmi ilaalu waliin raawwii isaanii ni hordofa;

18) Investerootni hayyama investimentii argatan bu'uura waliigalteetiin yeroo daangeffame keessatti akkaataa hayyama kennameefiin hojjachuu isaanii qaama dhimmi ilaalu waliin ni hordofa; ni deeggara; akkaataa waliigalteetiin kan hin hojjanne irratti qaama dhimmi ilaalu waliin tarkaanfiin sirreeffamaa akka fudhatamu ni taasisa;

19) Investaroota lafa baadiyyaa irratti hojii investimentii gaggeessaniif jajjabeessituuwwan hayyamaman akkaataa seeraatiin ni raawwata.

፲፫) በህጉ መሠረት ለኢንቨስትመንት ሥራ የገጠር መሬትን የወሰዱ ባለሃብቶች ከዞን ወይም ከወረዳ መስተዳደር ጋር ዉል እንዲፈርሙ ያደርጋል፤ የተፈረመዉን ዉል ይመዘግባል፤ የአፈፃፀሙ ሁኔታ በሚወጣዉ ደንብ የሚወሰን ይሆናል፤

፲፬) ጉዳዩ በሚመለከታቸው አካላት የተዘጋጁ የከተማና የገጠር የኢንቨስትመንት መሬትን በየደረጃዉ ከሚገኙ የመስተዳድር አካላት ጋር በመሆን የማስተዋወቅ ሥራን ይሰራል፤

፲፭) በኢንቨስተሮች የሚወሰዱት የኢንቨስትመንት መሬት ስፋት በስምምነቱ መሠረት መሆኑን ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ይከታተላል፣ ጉድለት ባለበት የማስተካከያ ዕርምጃ ጉዳዩ ከሚመለከተዉ አካል ጋር ይወስዳል፣ እንዲወስድ ያደርጋል፤

፲፮) የኢንቨስትመንት ፈቃድን ከመስጠቱ በፊት ተዘጋጅተዉ የቀረቡ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች በአካባቢና በሰዎች ጤና ላይ ተፅዕኖ የማያደርሱ መሆኑን የአከባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ጉዳዩ በሚመለከተው አካል መከናወኑን ያረጋግጣል፤ ተቀባይነት ላገኙ ፍቃድ ይሰጣል፤

፲፯) የጸደቁትን የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ዲዛይን ይመዘግባል፣ ከሚመለከተዉ አካል ጋር አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፣

፲፰) የኢንቨስትመንት ፈቃድ ያገኙ ኢንቨስተሮች በስምምነቱ መሠረት በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ በተሰጣቸው ፍቃድ መሠረት መሥራታቸውን ከሚመለከተዉ አካል ጋር ይከታተላል፣ ይደግፋል፣ በስምምነቱ መሠረት በማይሰሩት ላይ ከሚመለከተዉ አካል ጋር የማስተካከያ ዕርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

፲፱) በገጠር መሬት ላይ የኢንቨስትመንት ሥራ ለሚያከናውኑ ኢንቨስተሮች የተፈቀዱ ማበረታቻዎችን በሕጉ መሰረት ይፈጽማል፤

13) Cause investors who obtained rural land for investment activities according to law to sign investment contract agreement with zonal or urban administration; register agreements signed. Its implementation shall be determined by regulation issued;

14) Undertake promotion works on urban and rural investment land prepared by concerned bodies in collaboration with administrative organs at all level;

15) Follow up whether the size of investment land delivered to investors is in line with investment contract agreement in collaboration with concerned body, take or cause to be taken corrective measures where there is defect;

16) Ensure whether environmental impact assessment undertaken by concerned body before issuing investment license so that investment projects have no impact on environment and human health; give license for those who get acceptance;

17) Register approved investment projects design, follow up their implementation with concerned body;

18) Support and follow up whether investors who have construction license are working with the specified time stipulated in the contractual agreement and in accordance with the investment license issued, take legal measures on investors who act against the investment contractual agreement;

19) Implement incentives allowed for investors undertaking investment activities on rural land according to the law.

**44. Komishinii Poolisii**

Komishinichi aangoo fi hojii armaan gadii ni qabaata:

1) Gochaa fi sochiiwwan sirna Heera Mootummaa faallessanii fi balaa irra buusuu danda'an kamiyyuu ni ittisa;
2) Gocha yakkaa fi balaan tiraafikii akka hin uumamne fi hin raawwatamne ni ittisa;
3) Qorannaan yakkaa, mirga namoota yakkaan shakkamanii qabamanii Heeraa fi seeraan kabajame eeggatee akka gaggeeffamu ni taasisa;
4) Faayidaa fi dhaabbilee mootummaa naannichaa irratti yakki akka hin raawwatamne ni ittisa;
5) Ka'umsa yakkaa xiinxalee tooftaalee ittisaa ni baasa; ummannis yakka irraa akka of eegu ni barsiisa; bu'aawwan qorannoo yakkaa filataman hawaasaaf akka dhiyaatan ni taasisa;
6) Ummanni nageenya naannoosaa kabachiisuu fi yakka ittisuu irratti akka hirmaatu boordii kominitii poolisingii fi nageenyaa ni gurmeessa; ni barsiisa; qaama dhimmi ilaalu waliin ni hojjata; ni qindeessa;
7) Nageenya naannichaa amansiisaa taasisuuf qaamolee nageenya mootummaa Federaalaa fi Naannoo dhimmi ilaalu waliin odeeffannoo waljijjiira; qindoominaan ni hojjata;
8) Eegumsa daandiiwwan gurguddoo naannicha keessa qaxxaamuranii, dhaabbilee mootummaa, riqicha, warshaalee fi iddoowwan sochiin investimentii gurguddoon itti adeemsifaman, walgahii ummataa, ayyaana gurguddoo fi eegumsa abbootii taayitaa fi kan kana fakkaatu ni raawwata; sirnaa fi nageenyi eegamuu isaa ni mirkaneessa;
9) Qaama hawaasaa deeggarsa addaa barbaadan kan akka daa'immanii, dubartoota, manguddootaa fi qaama miidhamtootaaf xiyyeeffannaa addaa kennuun ni hojjata;
10) Hojiiwwan ittisaa fi qorannaa yakkaa cimsuuf gahumsa ogummaaf tajaajilli poolisii sadarkaa isaa kan eeggate akka ta'u qo'annoo ni gaggeessa;

**፵፬. የፖሊስ ኮሚሽን**

ኮሚሽኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩) ህገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን የሚቃረኑና አደጋ ላይ ሊጥሉ የሚችሉትን ማናቸውንም ድርጊቶችና እንቅስቃሴዎችን ይከላከላል፤
፪) የወንጀል ድርጊት እንዳይፈጸምና የትራፊክ አደጋ እንዳይከሰት ይከላከላል፤
፫) የወንጀል ምርመራ በህገ መንግሥቱና በሌሎች ህጎች በወንጀል ተጠርጥረው ለተያዙ ሰዎች መብት ጠብቆ እንዲካሄድ ያደርጋል፤
፬) በክልሉ መንግሥት ጥቅምና ተቋማት ላይ ወንጀል እንዳይፈጸም ይከላከላል፤
፭) የወንጀል መንስዔዎችን አጥንቶ የመከላከል ስልቶችን ያወጣል፣ህብረተሰቡ ከወንጀል ራሱን እንዲጠብቅ ያስተምራል፣ የተመረጡ የወንጀል ምርመራ ውጤቶች ለህዝብ እንዲቀርቡ ያደርጋል፤
፮) ህብረተሰቡ የአካባቢውን ሰላም ማስከበርና ወንጀል መከላከል ሥራ ላይ እንዲሳተፍ የሰላምና የኮሚኒቲ ፖሊሲንግ ቦርድን ያደራጃል፣ያስተምራል፣ ጉዳዩ ከሚመለከተው አካል ጋር ይሰራል፣ ያቀናጃል፤
፯) የክልሉን ሠላም አስተማማኝ ለማድረግ ከፌደራል የፀጥታ አካላትና ጉዳዩ ከሚመለከተው ክልል ጋር መረጃን ይለዋወጣል፣ በቅንጅት ይሰራል፤
፰) ክልሉን አቋርጦ የሚያልፉ ትላልቅ መንገዶችን፣ የመንግሥት ተቋማትን፤ ድልድዮች፤ ፋብሪካዎችንና ትላልቅ የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ የሚካሄድባቸው ቦታዎችን፣ የሕዝብ ስብሰባን፣ ትላልቅ በዓላትንና የባለሥልጣናት ጥበቃንና የመሳሰሉትን ጥበቃን ይፈጽማል፤ ሥርዓትና ደኅንነት መጠበቁን ያረጋግጣል፤
፱) ልዩ ዕርዳታ ለሚያስፈልጋቸው የህብረተሰቡ ክፍሎች እንደ ህፃናት፤ ሴቶች፤ አዛውንቶችና አካል ጉዳተኞች ላሉ ልዩ ትኩረት በመስጠት ይሰራል፤
፲) የወንጀል መከለከልና ምርመራ ሥራን ለማጠናከር የፖሊስ የሙያ ብቃትና አገልግሎት ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን ጥናት ያካሄዳል፤

**44. Police Commission**

The Commission shall have the following power and duties:

1) Prevent any activities and movements that contravene and endanger the constitutional system;
2) Prevent occurrences of criminal acts and traffic accidents;
3) cause criminal investigation to be conducted in accordance with the constitutional and legal rights of the suspected and detained persons;
4) prevent criminal acts against the interest of government and its organizations;
5) Analyze the causes of crime and devise means of prevention; educate the community to protect themselves from criminal acts; make selected criminal investigation case results public;
6) Organize community policing and security board to make the community participate in ensuring peace, educate, organize, and work with concerned body;
7) exchange information and work in collaboration with federal and regional concerned security organs with a view to ensure peace and security in the region;
8) undertake security activities to protect high ways which pass through the region, government organizations, bridge, factories, and areas where huge investment activities being undertaken, public gatherings, public holidays and government higher officials and other similar activities, ensure the respect of order and security;
9) work by giving particular attention to part of the society that needs special protection such as children, women, elders and persons with disability;
10) Undertake study to strengthen crime prevention and investigation activities and to make police service delivery compatible with the standard;

11) Gurmaa'ina, tajaajilaa fi raawwii hojii poolisii naannichaa irratti hojii xiinxalaa fi insipeekshinii ni gaggeessa; karoora tarsimoo ni baasa; tooftaalee raawwii hojii bifa wal fakkaatuun akka hojiirra oolu ni taasisa;
12) Meeshaalee waraanaa naannicha keessatti argaman ni galmeessa; hayyama ni kenna, ni haaromsa; ni too'ata; seera irratti hundaa'uun hidhannoo ni hiikkachiisa;
13) Ragaa baatota seeraa Abbaa Alangaa waliin ta'uun ni dhiyeessa;
14) Yakkoota aangoo Mana Murtii naannichaa ta'an Abbaa Alangaa waliin ni qorata;
15) Qorannoo teeknikii Abbaa Alangaa waliin ta'uun ni gaggeessa; ragaa ni baha; ragaa yakka irraa bilisa ta'uu ni kenna;
16) Meeshaalee ciraa akka ragaatti qabaman of eeggannoon ni eega; hanga qorannaan xumuramutti qabiinsaa fi haala abbaa qabeenyaatiif itti deebi'u irratti Abbaa Alangaa waliin ni hojjata; yammuu qorannaan xumuramu kanneen akka ragaatti barbaachisan Mana Murtiitti ni dhiyeessa; akkasumas qabeenya namoota yakkaan shakkamanii qabamanii imaanaan ni qaba; yeroo barbaachisaa ta'e ni deebisa;
17) Ajaja yookiin murtee Mana Murtii irraa kennamu ni raawwata;
18) Galmeewwan qorannaa yakkaa fi balaa tiraafikii, akkasumas ragaalee adda addaa Abbaa Alangaa fi qaama dhimmi ilaalu waliin sirnaan akka eegaman ni taasisa;
19) Balaan tasaa yammuu uumamu akkaataa haala balaa uumameetiin gargaarsaa fi deeggarsa ni kenna; qaama dhimmi ilaalu waliin qindoominaan ni hojjata;
20) Poolisii naannichaaf humna namaa barbaachisaa ta'e filatee ni leenjisa; ni barsiisa; iddoo barbachisaa ta'etti ramadee ni hojjachiisa; leenjii hojiirraa ni kenna; akka kennamus ni taasisa;
21) Humna kora bittinneessaa fi yakkamtoota gurumaa'an too'atu ni gurmeessa; ni leenjisa; ni bobbaasa;

፲፩) በክልሉ የፖሊስ አደረጃጀት፣ አገልግሎትና የሥራ አፈፃፀም ላይ የምርመራና ኢንስፔክሽን ሥራን ያካሄዳል፣ የስትራቴጂክ ዕቅድ ያወጣል፣ ሥራ አፈፃፀም ስልቶች በተመሣሣይ መልኩ ሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤
፲፪) በክልሉ ውስጥ የሚገኙትን የጦር መሣሪዎች ይመዘግባል፣ ፈቃድ ይሰጣል፣ ያድሳል፤ ይቆጣጠራል፣ በህግ መሰረት ትጥቅ ያስፈታል፤
፲፫) ከአቃቤ ህግ ጋር በመሆን የህግ ምስክሮች ያቀርባል፤
፲፬) የክልሉ ፍርድ ቤቶች ሥልጣን የሆኑትን ወንጀሎች ከአቃቤ ህግ ጋር በመሆን ይመረምራል፤
፲፭) ከአቃቤ ህግ ጋር በመሆን የቴክኒክ ምርመራን ያካሄዳል፣ ምስክር ይሆናል፣ ከወንጀል ነፃ የመሆን ማስረጃን ይሰጣል፤
፲፮) በማስረጃነት የተያዙ ኤግዚቢቶችን በጥንቃቄ ይይዛል፣ ምርመራ እስኪጠናቀቅ ድረስ ስለጥበቃውና ለባለቤቱ መመለስ በሚችልበት ሁኔታ ላይ ከአቃቤ ህግ ጋር ይሰራል፣ ምርመራው ሲጠናቀቅ በማስረጃነት የሚያገለግሉትን ለፍርድ ቤት ያቀርባል፣ እንደሁም በወንጀል ተጠርጥረው የተያዙ ሰዎችን ንብረት በአደራ ይይዛል፤ አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ይመልሳል፤
፲፯) ከፍርድ ቤት የሚሰጠውን ትዕዛዝ ወይም ውሳኔን ይፈጽማል፤
፲፰) የወንጀል ምርመራንና የትራፊክ አደጋ መዝገቦችን እንዲሁም የተለያዩ ማስረጃዎችን ከአቃቤ ህግና ጉዳዩ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን በሥርዓቱ እንዲጠበቁ ያደርጋል፤
፲፱) ድንገተኛ አደጋ ሲከሰት እንደደረሰው የአደጋ ሁኔታ ዕርዳታና ድጋፍ ይሰጣል፤ ከሚመለከተዉ አካል ጋር በቅንጅት ይሰራል፤
፳) ለክልሉ ፖሊስ አስፈላጊ የሆነውን የሰው ኃይል መልምሎ ያሰለጥናል፣ ያስተምራል፣ አስፈላጊ በሆነበት ቦታ መድቦ ያሰራል፤ የሥራ ላይ ሥልጠና ይሰጣል፤ እንዲሰጥም ያደርጋል፤
፳፩) የአድማ በታኝና የተደራጁ ወንጀለኞችን የሚቆጣጠር ኃይልን ያደራጃል፣ ያሰለጥናል፣ ያሰማራል፤

11) Undertake evaluation and inspection on organizational structure, service delivery and performance of police; issue strategic plan; cause implementation strategy of the work to be implemented uniformly;
12) Register weapons found in the region, issue and renew license, supervise, disarm in accordance with the law;
13) Cause appearance of legal witnesses in collaboration with public prosecutor;
14) investigate crimes which fall under the jurisdiction of the regional courts in collaboration with public prosecutor;
15) Undertake technical investigation in collaboration with public prosecutor, give professional evidence and testimony, issue certification document that proves a person to be free from crime;
16) keep exhibits with due care; work in collaboration with public prosecutor on its handling and return to the owner until investigation is completed, transfer exhibits to the court that are relevant as evidence upon completion of investigation; keep properties of suspects honestly; return when necessary;
17) execute order or decisions given by the court;
18) Cause proper handling of criminal investigation, and traffic accident files and various documents in collaboration with public prosecutor and concerned bodies;
19) Give necessary support when disaster occurs, work in collaboration with concerned bodies;
20) Recruit, train, educate and assign police members of the region, give or cause to be given on job training for them;
21) Organize, train and deploy police forces that control organized criminals;

22) Dandeettii raawwachiisummaa poolisii guddisuuf yeroo yeroon carraa barumsaatiif haala ni mijeessa;
23) Odeeffannoo fi istaastikisii yakkaa walitti ni qaba; ni qorata; akkaataa barbaachisummaa isaatti qaama dhimmi ilaaluuf ni dabarsa;
24) Dhaabbata leenjii poolsii naannichaa akka hundeeffamu ni taasisa; meeshaalee fi humna namaatiin ni guuta; ni gurmeessa; ni bulcha.

## 45. Komishinii Bulchiinsa Manneen Sirreessaa

Koomishinichi aangoo fi hojii armaan gadii ni qabaata:

1) Sirreeffamtootni seeraa yammuu too'annaa jala jiran mirgi isaanii bifa garaagarummaa hin qabneen akka kabajamu ni taasisa;
2) Poolisii mana hojichaatiif humna namaa barbaachisaa ta'e filatee ni leenjisa; ni barsiisa; iddoo barbachisaa ta'etti ramadee ni hojjachiisa; leenjii hojiirraa ni kenna; akka kennamus ni taasisa;
3) Sirreeffamaan seeraa gara mana sirreessaatti ergamu ajaja Mana Murtiitiin ta'ee waaraantiin kan itti kenname qofa ta'uu isaa ni mirkaneeffata;
4) Sirreeffamaan seeraa yeroo turmaata isaa keessatti jijjiirama amalaa fi ilaalchaa agarsiise gara jireenya hawaasaatti deebisuuf hojiiwwan dandeessisan ni raawwata;
5) Manneen sirreessaa keessatti wiirtuu leenjii ogummaa adda addaa ni hundeessa; sirreeffamtootni seeraa barumsa bu'uuraa, idilee fi ogummaa, akkasumas hubannoo adda addaa akka argatan ni taasisa; yeroo turmaata isaanii keessatti lammii oomishaawaa ta'anii jireenyi hawaasummaa isaanii akka fooyya'u ni taasisa;
6) Sirreeffamtootni seeraa fayya qabeessa akka ta'an, akkasumas haamilee fi qaamaan akka ciman iddoo ispoortii fi bashannanaa adda addaa ni qopheessa;
7) Sirreeffamtoota seeraa sababa umurii isaaniitiin haala addaatiin akka qabaman seeraan murtaa'e ilaalchisee addatti qabamanii murtii isaanii akka raawwatan haala ni mijeessa;

፳፪) የፖሊስ የማስፈጸም አቅምን ለማጎልበት በየጊዜው ለትምህርት ዕድሎች ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤
፳፫) የወንጀል መረጃንና ስታቲስቲክስን ይሰበስባል፣ ይመረምራል፣ እንደአስፈላጊነቱ ለሚመለከተው አካል ያስተላልፋል፤
፳፬) የክልሉ የፖሊስ ማሰልጠኛ ተቋም እንዲቋቋም ያደርጋል፣ በሰው ኃይልና በሎጅስቲክስ ያሟላል፣ ያደራጃል፣ ያስተዳድራል፡፡

## ፵፭. የማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ኮሚሽን

ኮሚሽኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩) የሕግ ታራሚዎች በቁጥጥር ሥር በሚቆዩበት ጊዜ መብቶቻቸው ያለልዩነት እንዲከበሩ ያደርጋል፤
፪) ለመስርያ ቤቱ አስፈላጊ የሆነዉን የፖሊስ የሰው ኃይል መልምሎ ያሰለጥናል፣ ያስተምራል፣ አስፈላጊ በሆነበት ቦታ መድቦ ያሰራል፤ የሥራ ላይ ሥልጠና ይሰጣል፤ እንዲሰጥም ያደርጋል፤
፫) ወደ ማረሚያ ቤቱ የሚላኩ የህግ ታራሚዎች በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሆኖ ዋራንቲ የተሰጠባቸዉ ብቻ መሆናቸዉን ያረጋግጣል፤
፬) በቆይታ ጊዜው የባህርይና የአመለካከት ለውጥ ያሳየን የህግ ታራሚ ወደ ማህበረሰቡ ኑሮ ለመመለስ የሚያስችሉ ሥራዎችን ይፈጽማል፤
፭) በማረሚ ቤቶች ውስጥ የተለያዩ የሙያ ማሠልጠኛ ማዕከላትን ይመሰርታል፣ የህግ ታራሚዎች መሠረታዊ መደበኛና ሙያዊ ትምህርቶችን እንዲሁም የተለያዩ ግንዛቤዎችን እንዲያገኙ ያደርጋል፣ በቆይታ ጊዜያቸው ምርታማ ዜጎች ሆነው ማህበራዊ ኑሮአቸውን እንዲያሻሽሉ ያደርጋል፡፡
፮) የህግ ታራሚዎች ጤናማ እንዲሆኑ እንዲሁም በሞራልና በአካል እንዲጠነክሩ የተለያዩ የስፖርትና መዝናኛ ቦታዎችን ያዘጋጃል፤
፯) በእድሜያቸዉ ምክንያት በልዩ ሁኔታ እንዲያዙ በህግ የተወሰነ የህግ ታራሚዎችን አስመልክቶ በልዩ ሁኔታ ተይዘዉ ፍርዳቸዉን እንዲፈጽሙ ሁኔታን ያመቻቻል፤

22) facilitate education opportunities to build performance capacity of police;
23) Collect and examine information and statistics regarding crime, transfer to concerned body as it is necessary;
24) Cause the establishment of regional police training institution, fill and organize with necessary man power and materials; organize and administer same.

## 45. Prison Administration Commission

The Commission shall have the following power and duties:

1) cause the rights of prisoners to be protected without discrimination while they are in prison;
2) Recruit, train, educate and assign police man power necessary for the commission; give or cause to be given on job training for them;
3) Ensure that prisoners who are sent to prison administration only be with court order and warrant;
4) Perform works which enable to return prisoners who have acquired behavioral and psychological change to their previous social life;
5) Establish training centers in prison administration, cause prisoners to get basic, regular and vocational education as well as awareness on different matters, cause them to be productive citizen and improve their social life;
6) Prepare different sport and recreation places that helps prisoners to be healthy as well as mentally and physically strong;
7) Facilitate condition to provide special treatment to prisoners whose special treatment is decided by law due to their age;

8) Sirreeffamtoonni seeraa qulqullina dhuunfaa fi naannoo isaanii akka eeggatan, kanneen dhibaman addatti bahanii akka qabamanii fi yaalaman ni taasia;
9) Baajata ramadamuun sirreeffamtoota seeraatiif nyaata gahaa ta'e ni dhiyeessa; dubartoota ulfaa fi daa'imman haadha waliin mana sirreessaa akka turan taasisamaniif kunuunsa addaa ni taasisa;
10) Sirreeffamoota seeraa yeroo turmaata isaanii keessatti fooyya'iinsa jijjiirama amalaa agarsiisan hordofuudhaan gorsaan (amakkiroodhaan) akka gadi lakkiffaman Mana Murtiitti ni dhiyeessa;
11) Gaaffii ol'iyyannoo fi iyyata sirreeffamtootni seeraa qaama adda addaatti akka ergamuuf dhiyeeffatan qaama dhimmi ilaalutti ni dabarsaaf; bu'aa isaas ni hordofa;
12) Sirreeffamtootni seeraa maatii isaanii, ogeeyyii fayyaa, abukaatoo isaanii fi k.k.f waliin akka wal qunnaman ni taasisa;
13) Manneen sirreessaa fi jireenya hawaasummaa sirreeffamtoota seeraa fooyyessuuf galii sochii hojii misoomaa adda addaa manneen sirreessaa, akkasumas qaamolee mootummaa, miti mootummaa fi dhaabbilee gargaarsaa irraa argamu qaama dhimmi ilaalutti dhiyeessuun yammuu hayyamamu hojiirra ni oolcha;
14) Nageenyaa fi tasgabbii manneen sirreessaa ni kabachiisa; sirreeffamtootni seeraa akka hin badne yookiin akka hin milqine ni eega; naamusa akka kabajanis ni taasisa;
15) Galmee fi seenaa sirreeffamtoota seeraa sirnaan ni qaba; jijjiirama jiru guyyaa guyyaan ni hordofa;
16) Jireenya hawaasummaa sirreeffamtoota seeraa fooyyessuuf sirreeffamtootni seeraa gurmaa'anii galii akka argatan deeggarsa ni kenna; galiin argamus dhimma fooyya'iinsa jireenya hawaasummaa isaaniitiif akka oolu ni taasisa;

፰) የህግ ታራሚዎች የግልና አካባቢያቸውን ፅዳት እንዲጠብቁ፣ የታመሙትም ለብቻ ተለይተው እንዲያዙና እንዲታከሙ ያደርጋል፤
፱) በሚመደበው በጀት ለህግ ታራሚዎች በቂ ምግብን ያቀርባል፣ ለነፍሰጡር ሴቶችና ከእናቶቻቸው ጋር ማረሚያ ቤት እንዲቆዩ ለተደረጉ ሕጻናት ልዩ እንክብካቤ ያደርጋል፤
፲) በቆይታ ጊዜያቸው የባህሪይ ለውጥ መሻሻል ያሳዩ የህግ ታራሚዎችን በመከታተል በአመክሮ እንዲፈቱ ለፍርድ ቤት ያቀርባል፤
፲፩) የህግ ታራሚዎች ለተለያዩ አካላት የሚያቀርቧቸውን ይግባኞችና ማመልከቻዎችን ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት ያስተላልፍላቸዋል፣ ውጤቱንም ይከታተላል፤
፲፪) የህግ ታራሚዎች ከቤተሰቦቻቸው፣ ከሐኪሞቻቸው፣ ከጠበቆቻቸውና ወዘተ ጋር እንዲገናኙ ያደርጋል፤
፲፫) ማረሚያ ቤቶችንና የህግ ታራሚዎችን ማህበራዊ ኑሮ ለማሻሻል የተለያዩ የማረሚያ ቤቶች የልማት ሥራዎች እንቅስቃሴ እንዲሁም ከመንግሥትና መንግሥታዊ ካልሆኑ አካላትና የዕርዳታ ድርጅቶች ላይ የሚገኘውን ገቢ ለሚመለከተው አካል በማቅረብ ሲፈቀድ ሥራ ላይ ያውላል፤
፲፬) የማረሚያ ቤቶችን ሠላምና ፀጥታ ያስከብራል፣ የህግ ታራሚዎች እንዳያመልጡ ወይም እንዳይጠፉ ይጠብቃል፣ ሥነ-ሥርዓት እንዲያከብሩም ያደርጋል፤
፲፭) የህግ ታራሚዎችን መዝገብና ታሪክ በሥርዓት ይይዛል፣ ያሉትን ለውጦች ቀን በቀን ይከታተላል፤
፲፮) የህግ ታራሚዎች ማህበራዊ ኑሮን ለማሻሻል ተደራጅተው የራሳቸውን ገቢ እንዲያገኙ ድጋፍ ይሰጣል፣ የሚያገኙትም ገቢ ለማህበራዊ ኑሯቸው መሻሻል እንዲውል ያደርጋል፤

8) Cause prisoners to take care of their personal hygiene and sanitation, and those who are sick to be kept and treated separately;
9) provide sufficient food for the prisoners with the allocated budget; make special treatment for pregnant women and children made to be detained in the prison with their imprisoned mother;
10) present to the court prisoners who rehabilitated in their stay in the prison to be released from imprisonment;
11) Send appeals and petitions of prisoners to various concerned organs and follow up feed back;
12) cause prisoners to meet with their family, physicians, and legal counselor etc;
13) utilize income generated from different development activities of the prison administration, donation generated from governmental and non-governmental organizations as well as aid organizations upon approval of concerned body to improve prison administration and social life of prisoners;
14) Ensure peace and security of prison administration; keep prisoners not to escape, cause prisoners to observe disciplinary rules;
15) keep prisoners records properly, follow up the changes which occur daily;
16) Give support for prisoners to be organized and get income to improve their social life, cause the income to be utilized for the improvement of their social life;

17) Wiirtuuwwan misooma sirreeffamtoota seeraa hojii misoomaa irratti hirmaachisuuf gargaaran ni babal'isa; galii argamu irraa kaffaltii gatii humnaa akka argatanii fi galii argamettis haala itti fayyadamuu danda'an ni mijeessa;
18) Qaamolee mootummaa fi miti mootummaa adda addaa waliin walitti dhufeenya ni taasisa; qondoominaan ni hojjata;
19) Dhiifama sirreefamtoota seeraatiif taasifamu ilaalchisee qaama dhimmi ilaalu waliin ni hojjata.

**46. Komishinii Misooma Naannoo Horsiisee Bulaa**

Komishinichi aangoo fi hojii armaan gadii ni qabaata:

1) Misooma naannoo horsiisee bulaa ilaalchisee qu'annoo ni gaggeessa; akka gaggeeffamus ni taasisa; ragaa adda addaa walitti ni qaba; ni qindeessa; sagantaa misoomaa itti fufiinsa qabu ni qopheessa; yammuu hayyamamu hojii irra ni oolcha;
2) Tooftaa misoomaa jiruu fi jireenya hawaasa horsiisee bulaa fooyyessuuf naannicha keessatti gaggeeffamu haala qabatamaa ummata naannoo horsiisee bulaa waliin wal simuu danda'u irratti yaada ni burqisiisa; yammuu hayyamamu hojiirra ni oolcha;
3) Abbootiin qabeenyaa dhuunfaa, dhaabbilee miti mootummaa fi seektarootni mootummaa dhimmi ilaalu sochii hojii misooma naannoo horsiisee bulaa keessatti qooda akka fudhatan ni qindeessa; ni jajjabeessa;
4) Sagantaalee fi pirojektoota misooma naannoo horsiisee bulaatiif ta'an ni qopheessa; qaamolee dhimmi ilaalu waliin hojiirra ni oolcha; bu'a qabeessummaa isaas abbummaan ni hordofa;
5) Sagantaalee fi pirojektoota misooma naannoo horsiisee bulaa keessatti gaggeeffaman raawwachiisuuf fandii fi qabeenya ni barbaada; yammuu hayyamamu hojiirra ni oolcha; hojiirra oolmaa isaas ni hordofa;

፲፯) የህግ ታራሚዎችን በልማት ሥራ ለማሳተፍ የሚረዱ የልማት ማዕከላትን ያስፋፋል፤ ከሚገኘው ገቢ የጉልበታቸው ዋጋ እንዲያገኙና በተገኘዉ ገቢም ሊጠቀሙ የሚችሉበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤
፲፰) ከተለያዩ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላት ጋር ግንኙነት ያደርጋል፤ በመቀናጀት ይሰራል፤
፲፱) ለህግ ታራሚዎች የሚደረገውን ይቅርታ አስመልክቶ ጉዳዩ ከሚመለከተው አካል ጋር ይሰራል፡፡

**፵፮. የአርብቶ አደር አካባቢ ልማት ኮሚሽን**

ኮሚሽኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩) የአርብቶ አደር አካባቢ ልማትን አስመልክቶ ጥናት ያካሄዳል፣ እንዲካሄድም ያደርጋል፣ የተለያዩ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ያደራጃል፣ ቀጣይነት ያለው የልማት ፕሮግራም ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድ ሥራ ላይ ያውላል፤
፪) የአርብቶ አደሩን ህይወትና ኑሮ ለማሻሻል በክልሉ ውስጥ የሚካሄዱት የልማት ሥልቶች ከአርብቶ አደሩ አካባቢ ተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር ሊጣጣሙ የሚችሉበት ሁኔታ ላይ ሃሣብ ያመነጫል፣ ሲፈቀድ ሥራ ላይ ያውላል፤
፫) የግል ባለሐብቶች፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ጉዳዩ የሚመለከታቸው የመንግሥት ሴክተሮች በአርብቶ አደር አካባቢ የልማት እንቅስቃሴ ውስጥ እንዲሣተፉ ያቀናጃል፣ ያበረታታል፤
፬) ለአርብቶ አደሩ አካባቢ ልማት የሚሆኑ ፕሮግራሞችና ፕረጀክቶችን ያዘጋጃል፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ሥራ ላይ ያውላል፣ ውጤታማነቱን በባለቤትነት ይከታተላል፤
፭) በአርብቶ አደሩ አካባቢ የሚካሄዱትን የልማት ፕሮግራሞችንና ፕሮጀክቶችን ለማስፈፀም ፈንድና ንብረትን ያፈላልጋል፣ ሲፈቀድ ሥራ ላይ ያውላል፤ ሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፤

17) Expand various prisoners development centers that enables prisoners to participate in development activities; facilitate condition through which prisoners be paid and utilize from income generated;
18) Make relation with various governmental and non-governmental organizations;
19) Work with concerned body on pardon given to prisoners.

**46. Pastoralist Area Development Commission**

The commission shall have the following power and duties:

1) Undertake and cause to be undertaken study regarding pastoralist area development; collect and organize different data; prepare sustainable development programs and implement same upon approval;
2) Devise development means to be undertaken in the region and suitable to the particular situation of the pastoralists to improve the lives of pastoralist societies; implement same up on approval;
3) Coordinate and encourage private investors, non-governmental organizations and concerned governmental sectors to participate in development activities undertaken in pastoral areas;
4) Prepare development program and projects suitable for pastoral area and implement in collaboration with concerned bodies, follow up its effectiveness;
5) Explore funds and resource necessary for implementation of development programs and projects undertaken in pastoral area, implement and follow up its implementations;

6) Yaada furmaataa rakkoo gabaa horsiisee bulaa hiiku ni burqisiisa; qaama dhimmi ilaalu waliin misoomni bu'uura gabaa akka babal'atu ni hojjata; oomishni qulqullinaa fi baay'ina barbaadamun gabaa biyya keessaa fi alaatiif akka dhiyaatu ni taasisa;
7) Hanqina bishaanii naannoo horsiisee bulaa maqsuuf qorannoon akka gaggeeffamu haala ni mijeessa; tooftaa adda addaatiin cimmisa bishaanii ni raawwata; qaamolee adda addaa misooma bishaanii gaggeessan waliin qindoominaan ni hojjata;
8) Dhiyeessa tajaajila bu'uura hawaasummaa naannoo horsisee bulaa ni qorata; sagantaa fi pirojektoota qopheessuudhaan akka babal'atu ni taasisa; qaamolee dhimmi ilaalu waliin qindoominaan ni hojjata; haala ni mijeessa;
9) Ijaarsa jal'isii xixiqqaa sadarkaa hirmaannaa ummataatiin hojjataman qaama dhimmi ilaalu waliin ni raawwachiisa; waldaalee itti fayyadamtoota jal'isii bishaanii ni gurmeessa; ni deeggara, ni hordofa;
10) Tooftaa misoomaa fi eegumsa qabeenya sanyii beeyiladaa, lafa dheedumsaa fi qabeenya uumamaa naannoo horsiisee bulaa keessatti argamu kunuunsuu fi eegsisu ilaalchisee qaama dhimmi ilaalu waliin ni baasa; hojiirra ni oolcha; ni hordofa;
11) Paakeejii misooma naannoo horsiisee bulaa ni qopheessa; akka babal'atu ni taasisa; qaama dhimmi ilaalu waliin ni hojjata; deeggarsa barbaachisu ni kenna; hojiirra ooluu isaa ni hordofa;
12) Naannoo horsiise bulaa keessatti sirna akeekkachiisa duraa akka diriiru haala ni mijieessa; karoora qophii of-eeggannoo balaa ni qopheessa; qaama dhimmi ilaalu waliin qindoominaan ni hojjata;
13) Naannoo horsiisee bulaa keessatti dhukkuba beeyiladaa, biqiltuu fi ilbiisa weerartuu fi kan biroo irratti qaamolee dhimmi ilaalu waliin tarkaanfii ittisaa ni fudhata; tajaajilli kuwaaraantiinii akka babal'atu ni taasisa;

፮) የአርብቶ አደሩን የገበያ ችግር የሚፈታ የመፍትሔ ሃሣብን ያመነጫል፣ ጉዳዩ ከሚመለከተው አካል ጋር የገበያ መሰረተ ልማት እንዲስፋፋ ይሠራል፣ ምርቶች በሚፈለገው ጥራትና ብዛት ለአገር ውስጥና ለውጪ ገበያ እንዲቀርቡ ያደርጋል፤
፯) የአርብቶ አደሩን አካባቢ የውሃ እጥረት ችግርን ለማስወገድ ጥናት እንዲካሄድ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤ በተለያዩ ሥልቶች የውሃ ማጠራቀም ሥራን ይሰራል፣ የውሃ ልማትን ከሚያካሂዱ ከተለያዩ አካላት ጋር በቅንጅት ይሠራል፤
፰) የአርብቶ አደር አካባቢ መሰረታዊ የማህበራዊ አገልግሎት አቅርቦትን ያጠናል፣ ፕሮግራምና ፕሮጀክቶችን በማዘጋጀት እንዲስፋፋ ያደርጋል፣ ጉዳዩ ከሚመለከተው አካል ጋር በቅንጅት ይሠራል፣ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤
፱) በህዝብ ተሳትፎ ደረጃ የሚሰሩ ትናንሽ የመስኖ ግንባታዎችን ጉዳዩ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን ያስፈፅማል፣ የመሥኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማህበራትን ያደረጃል፣ ይደግፋል፣ ይከታተላል፤
፲) የእንስሳት ሐብት ዝርያ ልማትና ጥበቃ፣ የግጦሽ መሬትንና በአርብቶ አደር አካባቢ የሚገኙትን የተፈጥሮ ሐብቶችን ለመንከባከብና ለመጠበቅ የሚያስችል ሥልትን ከሚመለከተዉ አካል ጋር ይቀይሳል፣ ሥራ ላይ ያውላል፣ ይከታተላል፤
፲፩) የአርብቶ አደር አካባቢ የልማት ፓኬጅን ያዘጋጃል፣ እንዲስፋፋ ያደርጋል፣ ጉዳዩ ከሚመለከተው አካል ጋር ይሰራል አስፈላጊውን ድጋፍ ይሠጣል፣ ሥራ ላይ መዋሉንም ይከታተላል፤
፲፪) በአርብቶ አደር አካባቢ ውስጥ የቅድመ ማስጠንቀቂያ ሥርዓት እንዲዘረጋ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ የአደጋ የመጠባበቅያ ዝግጁነት ዕቅድ ያዘጋጃል፣ ጉዳዩ ከሚመለከተው አካል ጋር በቅንጅት ይሠራል፤
፲፫) በአርብቶ አደሩ አካባቢ የእንስሳትና ዕጽዋት በሽታዎችን እንዲሁም የወራሪ ነፍሣትና በሌሎችም ላይ ከሚመለከተው አካል ጋር የመከላከል እርምጃ ይወስዳል፤ የኲዋራንታይን አገልግሎት እንዲስፋፋ ያደርጋል፤

6) Propose solution for market problems of pastoralists; work in collaboration with concerned bodies to expand basic market development infrastructures, cause products to be supplied, with necessary quality and quantity for domestic and foreign markets;
7) Facilitate conditions in which study to be undertaken to avoid water shortage in pastoral areas; perform water collection using various strategies; work in coordination with concerned bodies who are engaged in water development works;
8) Study basic social service provisions of pastoral areas; cause to be expanded through preparing plan and projects, work in collaboration with concerned bodies, facilitate conditions;
9) Cause small irrigation construction to be undertaken by the participation of community, organize, support and follow up water irrigation beneficiary association;
10) Prepare development and protection strategies for livestock species, grazing land and natural resource found in pastoral area with concerned body, implement and follow up same;
11) Prepare development package for pastoral areas, cause to be expanded, work in coordination with concerned bodies, give necessary support and follow up its implementation;
12) Facilitate condition for the establishment of pre warning system in pastoral area, prepare disaster preparedness plan, work in collaboration with concerned organs;
13) Take preventive measures in collaboration with concerned body on livestock and plant disease, insecticides, and others, in pastoral area, cause quarantine service to be expanded;

14) Ijaarsaawwan bu'uura misooma baadiyyaa fi dhaabbilee tajaajila hawaasummaa naannoo horsiisee bulaatti gaggeeffamaniif istaandardii fi dizaayinii mijaa'aan akka qophaa'u qaama dhimmi iluulu waliin ni qorachiisa; qaamoleen hojii ijaarsa bu'uura misooma baadiyyaa naannoo horsiisee bulaa keessatti gaggeessan akka itti fayyadaman ni taasisa; hojiirra ooluu isaa ni hordofa; ni too'ata;
15) Naannoo horsiisee bulaatti tajaajilli hawaasummaa akkka babal'atu qaama dhimmi ilaalu waliin ni hojjata;
16) Callaa guddistuu fi teeknolojiiwwan gosa adda addaa oomishaa fi oomishtummaa horsiisee bulaa guddisuudhaaf gargaaran gara horsiisee bulaatti osoo hin darbin Inistiitiyuutii Qorannoo Qonnaa waliin fudhatamummaa isaanii ni mirkaneessa; qulqullina isaa eegee yeroodhaan horsiisee bulaaf akka dhiyaatu ni taasisa; haala ni mijeessa; ni hordofa;
17) Dandeettii ogeessota naannoo horsiisee bulaa cimsuuf qaamolee adda addaa waliin walqunnamuun ogeessootni ogummaa barbaadamun haala leenjii itti argatan ni qindeessa; ni mijeessa;
18) Hirmaannaa fi hubannoon horsiisee bulaa akka cimu leenjii adda addaa ni qopheessa; giddugaleessa leenjii horsiisee bulaa ni babal'isa; ni qindeessa; hojiirra ni oolcha;
19) Hojiiwwan misoomaa naannoo horsiisee bulaa keessatti gaggeeffaman irratti dubartootni qooda fudhattootaa fi itti fayyadamtoota akka ta'an ni hojjata; haala ni mijeessa;
20) Naannoo horsiisee bulaatti giddugaleessa sanyii beeyiladaa fooyyessu kilinkoonnii fi laaboraatoriiwwan tajaajila eegumsa fayyaa beeyiladaa qaama dhimi ilaalu waliin akka babal'atu ni taasisa;
21) Naannoo horsiisee bulaatti daldaltoota qoricha beeyiladaa fi farra ilbiisotaa irratti bobba'aniif haala ni mijeessa; tamsa'ina qoricha fayyaa horii fi ilbiisotaa seeraan alaa qaama dhimmi ilaalu waliin ni too'ata;

፲፬) በአርብቶ አደሩ አካባቢ ለሚካሄዱ የገጠር መሰረተ ልማት ግንባታዎችና የማህበራዊ አገልግሎት ተቋማት ምቹ ስታንዳርድና ዲዛይን እንዲዘጋጅ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ያስጠናል፣ በአርብቶ አደር አካባቢ የገጠር መሰረተ ልማት ግንባታ ሥራን የሚያካሂዱ አካላት እንዲጠቀሙበት ያደርጋል፣ ሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤
፲፭) በአርብቶ አደሩ አካባቢ የማህበራዊ አገልግሎት እንዲስፋፋ ጉዳዩ ከሚመለከተው አካል ጋር ይሠራል፤
፲፮) የአርብቶ አደሩን ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ የሚረዱ የተለያዩ የምርት ማሣደጊያ ግብዓቶችና ቴክኖሎጂዎች ወደ አርብቶ አደሩ ከመተላለፋቸው በፊት ከግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ጋር ተቀባይነታቸውን ያረጋግጣል፣ ጥራቱን ጠብቆ በጊዜ ለአርብቶ አደሩ እንዲቀርብ ያደርጋል፣ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ ይከታተላል፤
፲፯) የአርብቶ አደሩ አካባቢ ባለሙያዎችን ብቃት ለማጠናከር ከተለያዩ አካላት ጋር ግንኙነት በመፍጠር ባለሙያዎቹ በሚፈለገው ሙያ ሥልጠና የሚያገኙበትን ሁኔታ ያቀናጃል፣ ያመቻቻል፤
፲፰) የአርብቶ አደሩ ተሳትፎና ግንዛቤ እንዲጠናከር የተለያዩ ሥልጠናዎችን ያዘጋጃል፣ የአርብቶ አደሮችን የሥልጠና ማዕከላት ያስፋፋል፣ ያቀናጃል፣ ሥራ ላይ ያውላል፤
፲፱) ሴቶች በአርብቶ አደሩ አካባቢ በሚካሄዱ የልማት ሥራዎች ውስጥ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይሠራል፣ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤
፳) በአርብቶ አደሩ አካባቢ የእንስሳት ዝሪያን የሚያሻሽሉና የእንስሳት ጤና ጥበቃ አገልግሎትን የሚሰጡ ክሊኒኮችና ላብራቶሪዎች ጉዳዩ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን እንዲስፋፉ ያደርጋል፤
፳፩) በአርብቶ አደሩ አካባቢ በእንስሳትና ፀረ ተባይ መድሐኒት ንግድ ላይ ለተሰማሩ ነጋዴዎች ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ ህገ ወጥ የእንስሳትና ፀረ-ተባይ መድሐኒቶች ሥርጭትን ጉዳዩ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን ይቆጣጠራል፤

14) Cause study to be undertaken with concerned body to prepare suitable standards and design of rural development infrastructure and social service organizations that are undertaken in pastoral area; cause those organs who are engaged in basic rural development construction works and infrastructures undertaking in pastoral area to use it; follow up and supervise its implementations;
15) work with concerned bodies for the expansion of social services in pastoral area;
16) ensure effectiveness of different agricultural inputs and new technologies that help to enhance products and productivity of pastoralist in collaboration with Agricultural Research Institute before passing them to pastoralists, cause to be supplied for pastoralists with required quality and standards on time for pastoralists, facilitate conditions and follow up;
17) Organize and facilitate conditions whereby the professionals of pastoralist areas acquire trainings on the required profession in order to strengthen their awareness in collaboration with different bodies;
18) Prepare various training to strengthen the awareness and participation of pastoralists; expand pastoralist training centre, organize and implement same;
19) Work and facilitate condition to make women to be the participant and beneficiary of development activities undertaken in pastoral area;
20) Cause livestock species improvement center, clinics, and laboratories of livestock health service to be expanded in pastoral area with concerned body;
21) Facilitate conditions for traders engaged in trading of veterinary medicine and pesticide in pastoral areas, supervise illegal distribution of livestock medicine and pesticides in collaboration with concerned bodies;

22) Qalma horii fi kuwaaraantiinii ilaalchisee seerotni jiran hojiirra ooluu isaanii qaama dhimmi ilaalu waliin ni hordofa;
23) Hojii eegumsaa fi misooma sululaa, lafa dheedumsaa, biyyee fi bishaanii naannoo horsiisee bulaatiif qorannoo ni gaggeesa; tooftaa ni baasa; ni raawwata; ni hordofa; ni too'ata;
24) Naannoo horsiisee bulaatti bosona mootummaa, paarkii, dawoo bineensa bosonaa fi lafa biqiltuun mukaa itti dhaabbatu qaama dhimmi ilaalu waliin ni daangeessa; gosa mukaa, bineensota bosonaa, simbirroo badiif saaxila bahan ni kunuunsa; ummanni qabeenya kana irraa itti fayyadamaa akka ta'u ni taasisa;
25) Naannoo horsiisee bulaatti qaamolee daldala bu'aa bosonaa fi horsiisa bineensa bosonaa irratti hirmaataniif deeggarsa teeknikaa ni kenna; raawwii isaa ni hordofa;
26) Teeknolojiiwwan giddugaleessa qorannootii bahan mootummaa, horsiisee bultootaa fi waldaaleedhaan akka baay'atanii fi raabsaman deeggarsa barbaachisu ni kenna; qooda fudhattootas ni jajjabeessa;
27) Waldaalee hojii gamataa naannoo horsiisee bulaatti qaama dhimmi ilaalu waliin akka gurmaa'anii fi qaama seerummaa akka argatan haala ni mijeessa; ni deeggara;
28) Gareewwan misoomaa haala qabatamaa naannoo horsiisee bulaatiin ni gurmeessa; garee misoomaa irraa fayyadamaa ta'uu isaanii ni mirkaneessa.

## 47. Komishinii Hoogganssa Sodaa Balaa

Komishinichi aangoo fi hojii armaan gadii ni qabaata:

1) Imaammata, tarsiimoowwan, sagantaalee fi karoora misoomaa mootummaa fi dhaabbilee dhuunfaa bahan keessatti dhimmi hoogganssa sodaa balaa hammatamuu isaa ni mirkaneessa; raawwii isaa ni hordofa; sirna barnootaa keessatti akka hammatamu ni hojjata; akkaataa barbaachisummaa isaatti deeggarsa ni kenna;

፳፪) የእንስሳት ዕርድንና ኳዋራንቲንን አስመልክቶ የወጡ ህጎች ሥራ ላይ መዋላቸውን ጉዳዩ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን ይከታተላል፤
፳፫) ለአርብቶ አደሩ አካባቢ የተፋሰስ፤ የግጦሽ መሬት፤ የአፈርና ውሃ ልማትና ጥበቃ ሥራዎች ጥናት ያካሄዳል፣ ሥልት ይቀይሳል፣ ሥራ ላይ ያውላል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤
፳፬) በአርብቶ አደሩ አካባቢ የመንግስት ደንን፤ ፓርክን፣ የዱር እንስሳት መኖሪያንና ፣የችግኝ መትክያ መሬትን ጉዳዩ ከሚመለከተው አካል ጋር ይከልላል፣ ለመጥፋት የተጋለጡ የዕፀዋት ፣የዱር እንስሳትና የአእዋፍ ዝሪያን ይንከባከባል፣ ህረተሰቡ ከነዚህ ሐብቶች ተጠቃሚ እንዲሆን ያደርጋል፤
፳፭) በአርብቶ አደሩ አካባቢ በደን ተዋፅኦ ንግድና በዱር እንስሳት ዕርባታ ላይ ለተሣተፉ የንግድ አካላት የቴክኒክ ድጋፍ ይሠጣል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤
፳፮) ከምርምር ማዕካላት የሚወጡ ቴክኖሎጂዎች በመንግስት፤ በአርብቶ አደሮችና በማህበራት እንዲባዙና እንዲሠራጩ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሠጣል፣ ባለ ድርሻ አካላትንም ያበረታታል፤
፳፯) የህብረት ሥራ ማህበራት በአርብቶ አደሩ አካባቢ እንዲደራጁና ህጋዊ ሰውነት እንዲያገኙ ጉዳዩ ከሚመለከተው አካል ጋር ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ ይደግፋል፤
፳፰) እንደ አርብቶ አደሩ አካባቢ ተጨባጭ ሁኔታ የልማት ቡድኖችን ያደራጃል፣ ከልማት ቡድን ተጠቃሚ መሆናቸውንም ያረጋግጣል።

## ፵፯. የአደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን

ኮሚሽኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

፩) በወጡ የመንግስትና የግል ተቋማት የልማት ፖሊሲ፤ ስትራቴጂዎች ፤ፕሮግራሞችና እቅዶች ውስጥ የአደጋ ስጋት አመራር ጉዳይ መካተቱን ያረጋግጣል፤ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣በትምህርት ሥርዓት ውስጥ እንዲካተት ይሠራል፣እነደ አስፈላጊነቱ ድጋፍ ይሰጣል፤

22) Follow up implementation of laws relating to slaughters and quarantine;
23) Undertake study to perform conservation and development of valley, grazing land, soil and water activities in pastoralist area; devise mechanisms, implement, follow up, and supervise same;
24) Demarcate government forest, parks, willed shelter and land for planting trees with concerned bodies, conserve plant species, wild animals, birds exposed to extinction, causes society to be benefited from these resources;
25) Give technical support for organs who participate on forest product trade and rearing wild life in pastoralist area, follow up its implementation;
26) Give necessary support for the production and distribution of new technologies coming from research centers by Government, private investors, pastoralists and associations, encourage stakeholders;
27) Facilitate condition and support co-operative associations to be organized and acquire legal personality in collaboration with concerned body;
28) Organize development teams based on particular situation of pastoralists areas; ensure that they are benefited from such development;

## 47. Disaster Threat Management Commission

The commission shall have the following power and duties:

1) Ensure that the issue of disaster threat management be incorporated in the policies, strategies, programs and development plans of the government and private enterprises; follow up its implementation; work to enable it be included in the educational curriculum; provide support as deemed necessary;

2) Mana Maree hooggansa sodaa balaa naannichaa akka hundaa'u ni taasisa; barreessaa Mana Marichaa ta'ee ni tajaajila; raawwiin isaa Dambii bahuun kan murtaa'u ta'a;
3) Bu'uura immaammataa fi tarsiimoo baheen hooggansi sodaa balaa hojiirra ooluu isaa ni hordofa; raawwii isaas yeroo yeroon Mana Maree hooggansa sadaa balaa naannichaatiif ni dhiyeessa;
4) Sagantaalee sodaa balaa hir'isan, miidhaa dhaqqabeef deebii kennuu fi miidhamtoota deebisanii dhaabuu ni qindeessa; ni hordofa; ni gamaaggama;
5) Balaa tasaa humna seektarootaa ol ta'aniif hojii deebii kennuu ni raawwata; ni hooggana; ni qindeessa;
6) Fandii of-eeggannoo ni hundeessa; ni bulcha; haalli raawwii isaa Dambii baahuun kan murtaa'u ta'a;
7) Hojii qophii pirofaayilii saaxilamummaa balaa fi akkaataa barbaachisaa ta'etti pirofaayilicha irra deebiin haaromsuu qaama ilaallatu waliin ni gaggeessa; ni qindeessa.
8) Pirofaayilii saaxilamummaa balaa qophaa'e bu'uura godhachuun sirna akeekkachiisa duraa ni diriirsa; hojiirra ni oolcha; hojiirra akka oolu ni taasisa; haala wayitaawaa fi itti fufiinsa qabuun qaama dhimmi ilaallatau waliin odeeffannoo wal ni jijjiira;
9) Balaan dura, yeroo balaa fi balaan booda qorannoo fi gamaaggamni sadarkaa hundatti gaggeeffamu ni hooggana; ni qindeessa;
10) Sadarkaa naannootti giddugaleessa qindeessaa hojii akeekkachiisa duraa fi deebii teeknolojii ammayyaatiin akka deeggaramu ni taasisa; ni gaggeessa; ni bulcha; akkaataa barbaachiisummaa isaatti giddugaleessotni walfakkaatan sadarkaa Godinaa, Magaalotaa fi Aanaaleetti akka hundeeffaman deeggarsa ni taasisa;
11) Balaa qunname ilaalchisee murtii Mana Maree hooggansa sodaa balaatiin kennamu irratti hundaa'uun gargaarsa barbaachisu walitti ni qaba; miidhamtootaaf ni dhaqqabsiisa; akka dhaqqabu ni taasisa;
12) Dhaabbilee miti mootummaa naannicha keessatti gargaarsa fi wabii nyaataa irratti bobba'an waliin qindoominaan ni hojjata; ni hordofa.

፪) የክልሉ የአደጋ ስጋት አመራር ምክር ቤት እንዲቋቋም ያደርጋል፤ የምክር ቤቱ ፀሐፊ ሆኖ ያገለግላል፤አፈፃፀሙ በሚወጣው ደንብ የሚወሰን ይሆናል፤
፫) በወጣው ፖሊሲና ስትራቴጂ መሰረት የአደጋ ስጋት አመራር ሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፣አፈፃፀሙን በየግዜው ለክልሉ የአደጋ ስጋት አመራር ምክር ቤት ያቀረባል፤
፬) የአደጋ ስጋትን የሚቀንሱ ፤ለደረሰው ጉዳት ምላሽ መስጠትና ተጎጅዎችን መልሶ የማቋቋም ፕሮግራሞችን ያቀናጃል፤ ይከታተላል፣ ይገመግማል፤
፭) ከሴክተሮች አቅም በላይ ለሆኑ ድንገተኛ አደጋ ምላሽ የመስጠት ሥራ ያከናውናል፤ያስተዳድራል፤ ያቀናጃል፤
፮) የመጠባበቅያ ፈንድ ያቋቁማል፣ያስተዳድራል፣የአፈፃፀሙ ሁኔታ በሚወጣው ደንብ የሚወሰን ይሆናል፤
፯) የአደጋ ተጋላጭነት ፕሮፋይል ዝግጅት ሥራና እንደ አስፈላጊነቱ ፕሮፋይሉን መልሶ ማሳደስን ከሚመለከተው አካል ጋር ያካሄዳል፤ ያቀናጃል፤
፰) የተዘጋጀውን የአደጋ ተጋላጭነት ፕሮፋይል መሰረት በማድረግ የቅድመ ማስጠንቀቅያ ሥርዓትን ይዘረጋል፣ ሥራ ላይ ያውላል፣ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፣ ወቅታዊና ቀጣይነት ባለዉ ሁኔታ ጉዳዩ ከሚመለከተው አካል ጋር መረጃ ይለወዋወጣል፤
፱) ከአደጋ በፊት፣በአደጋ ጊዜና ከአደጋ በኊላ በሁሉም ደረጃ የሚካሄደውን ጥናትና ግምገማ ይመራል፣ያቀናጃል፤
፲) በክልል ደረጃ የቅድመ ማስጠንቀቂያ ሥራና ምላሽ ቅንጅት ማዕከል በዘመናዊ ተክኖሎጂ እንዲደገፍ ያደርጋል፤ ይመራል፤ያስተዳድራል፤እነደአስፈላግነቱ ተመሳሳይ ማዕከላት በዞን በከተማና በወረዳ ደረጃ እንዲመሰረቱ ድጋፍ ያደርጋል፤
፲፩) ያጋጠመውን አደጋ አስመልክቶ የአደጋ ስጋት አመራር ምክር ቤት በሚሰጠው ዉሳኔ ላይ ተመሰርቶ የሚያስፈልገዉን እርዳታ ይሰበስባል፤ ለተጎጅዎች ያደርሳል፤እንዲደርስ ያደርጋል፤
፲፪) በክልሉ ውስጥ በዕርዳታና በምግብ ዋስትና ላይ ከተሰማሩ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር በቅንጅት ይሰራል፤ይከታተላል፤

2) Cause the establishment of the disaster threat management council of the region; serve as a secretary of such council; its implementation shall be decided by the regulation to be issued;
3) Follow up that the disaster threat management to be implemented in accordance with the policy and strategy set forth; submit its implementation to the disaster threat management council of the region periodically;
4) Co-ordinate; follow-up; and evaluate the programs of disaster threat minimization, responding for the damage caused and rehabilitation of the victims;
5) Perform response provision activity for the accidents beyond the capacity of the sectors; direct; co-ordinate same;
6) Establish reserve fund; administer same; its implementation shall be decided by the regulation to be issued;
7) Conduct preparation of danger vulnerability profile and the renewal of such profile as deemed necessary in collaboration with the concerned body; coordinate same;
8) Extend a precautionary system depending on the prepared danger vulnerability profile; implement; cause its implementation; exchange information with the concerned body in a current and sustainable basis;
9) Leads the pre, during, and post danger investigation and evaluation conducted at all levels; coordinate same;
10) Cause the regional level precautionary and response activity coordinating center to be supported by the modern technology; direct; administer; provide support as deemed necessary for the establishment of similar centers at the zonal, city, and district levels;
11) Collect the necessary aids depending on the decision of disaster threat management council concerning the disaster occurred; supply to the victims; cause to be supplied;
12) Work in co-ordination with non-governmental organization engaged in aid and food security in the region; follow up same.

**48. Ejensii Carraa Hojii Uumuu fi Wabii Nyaataa Magaalotaa**

Ejensichi aangoo fi hojii armaan gadii ni qabaata:

1) Tarsiimoo carraa hojii uumuu fi wabii nyaataa magaalotaa bu'uura taasifachuun lammiilee hojii hojjachuu hin dandeenye yookiin sababa adda addaatiin hojjachuu osoo danda'anuu hojii warra hin qabnee fi lammiilee sarara hiyyummaatii gadii jiraniif deeggarsa seeftii neetii misoomawaa kennuudhaan jireenya isaanii ittii fufiinsaan akka fooyya'uu fi wabii nyaataa isaanii akka mirkanaa'u ni taasisa;
2) Tarsiimoo misooma intarpiraayizoota maayikiroo fi xixiqqaa galmaan gahuuf, hojii dhabeeyyii naannicha keessa jiran ni galmeessa; hubannoo ni uuma; carraa hojii jiru adda baasuun akkaataa fedhii isaaniitiin dhuunfaan yookiin gurmaa'anii akka hojjatan haala ni mijeessa;
3) Misooma intarpiraayizoota maayikiroo fi damee maanufakcharingii xixiqqaan ala jiran hundaa kan qonnaa, ijaarsaa, daldalaa fi damee tajaajilaa irratti kutaalee hawaasaa bobba'an deeggaruu fi guddisuudhaan dorgomaa akka ta'an taasisuun caarraa hojii naannichaa keessattii akkaa uumamuu, galiin jiraattotaa akka fooyya'uu fi qoodinsi galii haqaa qabeessaa ta'ee akka jiraatu ni taasiisa;
4) Hojii dhabdootni naannichaa keessumaayyuu dargaggootaa fi dubartootni hojii uumachuu irratti bal'inaan akka bobba'an hubannoo ni uuma; deeggarsa leenjii, iddoo hojii, liqii, walitti hidhamiinsa gabaa, gorsaa fi odeeffannoo akka argatan haala ni mijeessa;
5) Intarpiraayizoota maayikiroo fi damee maanufakcharingii xixiqqaan ala jiran dorgomaa, guddina ittiifuufinsaa qabuu fi misooma industiritiif bu'uraa cimaa akka buusu danda'an dhaabbilee deeggarsa kennan ni cimsa; ni qindeessa;

**፵፰. የከተሞች ሥራ እድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና ኤጀንሲ**

ኤጀንሲው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

፩) የከተሞች ሥራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ስትራቴጂን መሰረት በማድረግ ሥራ መስራት የማይችሉ ዜጎችን ወይም መስራት እየቻሉ በተለያየ ምክንያት ሥራ የሌላቸውና ከድህነት ወለል በታች ላሉ ዜጎች ልማታዊ የሴፍት ኔት ድጋፍ በመስጠት ኑሮዋቸው በቀጣይነት እንዲሻሻልና የምግብ ዋስትናቸው እንዲረጋገጥ ያደርጋል፤
፪) የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን የልማት ስትራቴጂ ከግብ ለማድረስ በክልሉ ውስጥ ያሉ ሥራ አጦችን ይመዘግባል፤ ግንዛቤ ይፈጥራል፤ ያለውን የሥራ ዕድል በመለየት እንደየፍላጎታቸው በግል ወይም በመደራጀት እንዲሰሩ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤
፫) በጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች ልማትና በአነስተኛ ማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ውጭ ባሉት በሁሉም የእርሻ፣ የኮንስትራክሽን፣ ንግድና አገልግሎት ዘርፍ ላይ የተሰማሩ የህብረተሰብ ክፍሎችን በመደገፍና በማሳደግ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ በማድረግ በክልሉ ውስጥ የሥራ ዕድል አንዲፈጠር፣ የነዋርዎች ገቢ እንዲሻሻልና ፍትሀዊ የገቢ ክፍፍል እንዲኖር ያደርጋል፤
፬) የክልሉ ሥራ አጦች በተለይም ወጣቶችና ሴቶች የራሣቸውን ሥራ መፍጠር ላይ በሰፊው እንዲሰማሩ ግንዛቤ ይፈጥራል፤የስልጠና ድጋፍ፣ የሥራ ቦታ፣ የብድር አገልግሎት፣ የገበያ ትስስር፣ ምክርና መረጃዎችን እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤
፭) በጥቃቅን ኢንተርፕራይዞችና በአነስተኛ ማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ውጭ ያሉ ተወዳዳሪ፣ ቀጣይነት ያለው እድገትና ለእንዱስትሪ ልማት ጠንካራ መሰረት መጣል እንዲችሉ ድጋፍ የሚሰጡ ድርጅቶችን ያጠናክራል፤ ያቀናጃል፤

**48. Urban Job Opportunity Creation and Food Security Agency**

The Agency shall have the following powers and duties:

1) On the basis of the urban job opportunity creation and food security strategy, make the citizens who are unable to work or who do not have work for various reasons though they can work and the citizens living below the poverty line that their lives be sustainably improved and their food security be ensured by providing them developmental safety net assistances;
2) Register the jobless persons in the region; create awareness; identify the existing job opportunity and facilitate conditions for them to work as per their own interests whether privately or by being organized so as to achieve the strategies of micro and small scale enterprises;
3) Ensure the creation of job in the region, the improvement of the income of residents, and prevalence of fair distribution of income through supporting and promoting segments of the society engaged on all activities like in agriculture, construction, trade and service branch excluding the micro and small scale manufacturing branch development enterprises;
4) Create awareness for the jobless persons in the region specially the youth and women to enable them widely engage on job creation activities; facilitate conditions for them to get training supports, place of work, loans, market integration, consultancy and information;
5) Strengthen and coordinate the organizations which provide supports for the micro and small scale enterprises which are out of manufacturing branches to enable them be competent, lay strong foundations for sustainable growth and industrial development;

6) Hojilee carraa hojii uumuu fi wabii nyaataa magaalotaa arii-fachiisuuf tarsiimoowwan fi sagantaalee qophaa'an bu'uura godhachuudhaan hojiirra akka oolan karoora yeroo dheeraa fi gabaabaa qopheessuun qaama dhimmi ilaaluuf ni dhiyeessaa; yammuu hayyamaamu hojiirra ni oolcha; raawwii isaa ni hordofaa;
7) Hojiilee seeftiineetii misoomawaa magaalotaa, foyya'insaa jireenyaa fi intarpiraayzoota maayikiroo fi xixiqqaa damee maanufakcharingii ala jiraniif paakeejii deeggarsaa ni qopheessa; ni qindeessaa; raawwii isaa ni hordofa;
8) Magaalota naannichaa keessatti wabii nyaataa magaalotaa mirkaneessuuf akkasumas carraa hojii uumuu fi xixiqqaa damee maanufakcharingiin ala jiran dabalatee dhimmoota misoomaa fi dorgomtummaa isaanii irratti hudhaa ta'an qo'annoon adda baasee furmaata ni kenna;
9) Naannicha keessatti qaamolee sadarkaan hojiilee carraa hojii uumuu fi wabii nyaataa magalotaa gargaaraanii fi qindeessan paakeejii deeggarsa dandeettiiraawwachistummaaisaanii cimsan ni qopheessa; ni ijaara;
10) Saxaxaa sona dabaluuf gargaaraan hordofuudhaan misooma intarpiraayzoota maaykiroo fi xixiqqaa damee maanufacharingiin ala jiraniif fedhii isaanii bu'uura godhachuudhaan dhaabbilee deeggarsaa leenjii, faayinaansii, teeknolojii fi tajaajila gorsaa dhiyeessan ni qindeessa;
11) Hawaasa keessatti ilaalcha dogoggoraa hojii uummachuu irratti jiru jijjiiruuf kan dandeessisan hojiilee barnootaa fi leenjii bal'inaan akka hojjataman kan gargaraan sosochiin ummataa akka uumamu deeggarsa ni taasisaa;
12) Qaamolee dhimmi ilaallatan waliin qindaa'uun magaalota keessatti dhimmoota rakkoolee hawaasummaa fi farra jireenyaa ta'an akkasumaas godaansa seeraan alaaf lammiilee saaxilamoo ta'an gochicha irraa ittisuu fi hojiiwwan haaromsaa akka hojjatamaan ni taasisa;

፮) የከተሞችን ሥራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትናን የሚያፋጥኑ ሥራዎች የተዘጋጁ ስትራቴጂዎችና ፕሮግራሞችን መሰረት በማድረግ ሥራ ላይ እንዲውሉ የአጭርና የረጂም ጊዜ እቅዶችን በማዘጋጀት ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ሥራ ላይ ያውላል፤ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፤
፯) የከተሞች ልማታዊ የሴፍት ኔት ፣ የኑሮ መሻሻልና ከማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ውጭ ላሉት የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የድጋፍ ፓኬጅ ያዘጋጃል፤ ያቀናጃል፤ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፤
፰) በክልሉ ከተሞች ውስጥ የከተሞችን ምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ እንዲሁም የሥራ ዕድል ፈጠራና ከማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ውጭ ያሉትን የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ጨምሮ በልማትና ተወዳዳሪነታቸው ጉዳይ ላይ ማነቆ የሆኑትን በጥናት ለይቶ መፍተሄ ይሰጣል፤
፱) በክልሉ ውስጥ የከተሞች ሥራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ሥራዎችን በየደረጃው የሚደግፉና የሚያቀናጁ አካላትን የማስፈፀም አቅም የሚያጠናክር የድጋፍ ፓኬጅ ያዘጋጃል፤ ይገነባል፣
፲) የእሴቶችን ትስስር ለመጨመር የሚረዱትን በመከታተል ከማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ውጭ ላሉት የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ፍላጎታቸውን መሰረት በማድረግ የስልጠና፣ የፋይናንስ፣ የቴክኖሎጂና የምክር አገልግሎት የሚያቀርቡ የድጋፍ ድርጅቶችን ያቀናጃል፤
፲፩) በህብረተሰቡ ውስጥ በሥራ ፈጠር ላይ ያለው የተሳሳተ አመለካከትን ለመቀየር የሚያስችሉ የትምህርትና ሥልጠና ሥራዎችን በስፋት እንዲሠሩ የሚረዱ የህዝብ ንቅናቄ እንዲፈጠር ድጋፍ ያደርጋል፤
፲፪) ከሚመለከተው አካል ጋር በመቀናጀት በከተሞች ውስጥ ማህበራዊ ችግሮችና ፀረ ኑሮ የሆኑ ጉዳዮችን እንዲሁም ለህገ ወጥ ዝዉዉር ተጋላጭ የሆኑ ዜጎችን ከድርጊቱ ለመከላከልና የተሀዲሶ ሥራዎች እንዲሠሩ ያደርጋል፤

6) Prepare the long and short term plan and submit to the concerned body based on the strategies and programs designed for facilitating the urban job opportunity creating and food security activities; implement the plan up on its approval; follows up its implementation;
7) Prepare support package for the urban developmental safety net, improvements of livelihood and the micro and small scale enterprises which are out of manufacturing branch; coordinate, follow up its implementation;
8) Identify through research and give solution for the challenges of the cities in ensuring their food security and creation of jobs and on the issues of their development and competitiveness including the manufacturing branch;
9) Prepare the performance ability building support packages for the bodies of each levels in the region which supports and coordinates the urban job opportunity creation and food security;
10) Coordinate the training, finance and consultancy service supplying support organizations for the micro and small scale enterprises which are out of manufacturing branch depending on their demand by following up the interconnections used to increase values;
11) Provide support for the emergence of public mobilization which help the extensive performances of education and training activities that enable to change the wrong attitude within the society regarding job creation;
12) In collaboration with the concerned bodies, cause the performances of activities related to the issues of social problems and anti-lives as well as the prevention of citizens vulnerable to illegal migration from such acts and rehabilitation activities;

13) Ulaagaalee madaalliwwaan fi dorgommii hojiilee misoomaa fi bulchiinsa gaarii magaalotaa sadarkaadhaan adda baasuuf gargaraan keessatti dhimmi carraa hojii uumuu fi wabii nyaataa magaalotaa akka ulaagaa tokkootti galuu isaanii ni hordofa;
14) Intarpiraayizoota maayikiroo fi xixiqqaa damee maanufaakcharingii ala jiran damee isaaniitiin waldaadhaan akka gurmaa'an deeggaruudhaan walitti hidhamiinsa gabaa biyya keessaa irraa fayyadamoo akka ta'an ni deeggara;
15) Naannicha keessatti carraa hojii uumuu fi wabii nyaataa magaalotaa mirkaneessuuf dhimmoota barbaachisoo ta'an kan akka ragaa lammiilee hojii hin qabne, hojjachuu kan danda'anii fi hin daandeenye, rakkoolee hawaasummaaf saaxilamoo kan ta'an qo'annoodhaan adda baasuun walitti ni qaba; ni qaacessa; ni gurmeessa; ni tamsaasa;
16) Fayyadamtoota magaalaa sarara hiyyummaatii gad jiraniif paakeejii addaa bocuudhaan gara hojiitti ni bobbaasa. Daangaa yeroo kaa'ame keessatti akka eebbifaman ni taasisa;
17) Muuxannowwan gaggaarii hojiilee carraa hojii uumuu fi wabii nyaataa magaalotaa irraatti jiran qo'annoon adda baasuun qindeessuudhaan akka babal'atan ni taasisa;
18) Gahee misooma Intarpiraayizoota maayikiroo fi xixiqqaa damee maanufaakcharingii ala jiran qabu akka guddatuu fi misoomni ariifachiisaan akka mirkanaa'u, abbootiin qabeenyaa misoomawaa ta'an baay'inaan akka uumaman, qaama raawwattootaa misooma intarpiraayizoota maayikiroo fi xixiqqaa fi qooda fudhattoota waliin ni hojjata;
19) Qabeenya uumamaa naannichaa carraa hojii uumuu fi wabii nyaataa magaalotaaf ooluu danda'an ilaalchisee qorannoo ni gaggeessa; bu'aa qorannichaa qaama dhimmi ilaaluuf ni dhiyeessa; yammuu hayyamamu hojiirra akka oolu ni taasisa;

፲፫) የከተሞች የልማትና መልካም አስተዳደር ሥራ በደረጃ ለመለየት የሚረዱ የመመዘኛና ውድድር መስፈርቶች ውስጥ የከተሞች ሥራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ጉዳይ እንደ አንድ መስፈርት መግባቱን ይከታተላል፤
፲፬) ከማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ውጭ ያሉ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት በየዘርፋቸው በማህበር እንዲደራጁ በመደገፍ በሀገር ውስጥ የገበያ ትስስር ላይ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደግፋል፤
፲፭) በክልሉ ውስጥ የከተሞች ሥራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ አስፈላጊ የሆኑ ጉዳዮች እንደ ሥራ አጥ ዜጎች ማስረጃ፣ መስራት የሚችሉ እና የማይችሉ፣ ለማህበራዊ ችግሮች ተጋላጭ የሆኑትን በጥናት በመለየት ይሰበስባል፤ ይተነትናል፤ ያደራጃል፤ ያሰራጫል፤
፲፮) ከድህነት ወለል በታች ላሉ የከተማ ተጠቃሚዎች ልዩ ፓኬጅ ቀርፆ ወደ ሥራ ያሰማራል፤ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ እንዲመረቁ ያደርጋል፤
፲፯) በከተሞች ሥራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ሥራዎች ላይ ያሉ ጥሩ ተሞክሮዎችን በጥናት ለይቶ በማቀናጀት እንዲስፋፉ ያደርጋል፤
፲፰) ከማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ውጭ ያሉት የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ያላቸው ሚና እንዲያድግና ፈጣን ልማት እንዲረጋገጥ፤ ልማታዊ የሆኑ ባለሐብቶች በብዛት እንዲፈጠሩ፣ ከጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የልማት አስፈፃሚ አካላትና ከባለ ድርሻዎች ጋር ይሠራል፤
፲፱) ለከተሞች ሥራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ሊውል የሚችለውን የክልሉ ተፈጥሮ ሀብትን አስመልክቶ ጥናት ያካሄዳል፤ የጥናቱን ውጤት ጉዳዩ ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፤ ሲፈቀድም ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

13) Follow-up the incorporation of the issue of the urban job opportunity creation and food security as one criterion in the evaluation and competition criteria which help to identify in ranks the development and good governance activities of the cities;
14) Support the micro and small scale enterprises which are out of the manufacturing branch to be organized in association in their branches and to enable them be beneficiaries from the market integration within the country;
15) Collect; analyze; organize and disseminate the issues necessary to ensure the urban job opportunity creation and food security in the region such as evidences of jobless citizens, those who are able and unable to work and those vulnerable for social problems through identifying with research;
16) Design special package for the beneficiaries of the cities who are below the poverty line and make them engage to works; cause them graduate within the fixed time limit;
17) Identify with research and organize the better experiences regarding the urban job opportunity creation and food security and make them to be expanded;
18) Work with the performing bodies of the micro and small scale enterprise developments and stake holders for the creation of private investors in greater quantity so as to ensure the advancement of the role of micro and small scale enterprises developments which are out of the manufacturing branch and for the realization of rapid development;
19) Undertake study regarding the natural resources of the region, job opportunity creation and food security that can be used for the cities; submit the findings of the study for the concerned body; cause to be implemented up on its approval;

20) Lammiilee hojii dhabdootaa carraa hojii naannicha keessatti uumamuuf akkaataa fedhii isaaniitiin, seera daldalaa fi waldaa hojii gamtaa irratti hundaa'uun dhuunfaan yookiin waldaadhaan ni gurmeessa; hayyama daldalaa fi qaama seerummaa akka argatan ni taasisa;
21) Intarpiraayizoota maayikiroo fi xixiqqaa damee maanufakcharingii ala jiran dhaabbilee, kollejjootaa fi kollejjoota pooliiteeknikii fi dhaabbilee dhiyeessa faayinaansii xixiqqaa fi dhiyeessaa meeshaalee liizii waliin ta'uun haala tajaajila ekisteenshinii industirii, liqii fi maashinii itti argatan ni mijeessa;
22) Paakeejiiwwan deeggarsa carraa hojii uumuu fi wabii nyaataa magaalotaa saffisiisuuf qophaa'an hojiirra ni oolcha;
23) Namoota yookiin dhaabbileen carraa hojii uumamuuf iddoon oomishaa fi gurgurtaa gahaa ta'e qophaa'uu isaa ni mirkaneessa;
24) Wiirtulee kenniinsa tajaajila iddoo tokkoo ni gurmeessa; ni cimsa; sirna fooyya'aa fi haaraa tajaajiloota si'aayina qabu kennuu dandeessisu ni diriirsa; humna wiirtulee ni ijaara;
25) Sirna intarpiraayizonni maayikiroo fi xixiqqaa damee maanufaakcharingii irratti bobba'an ala jiran; itti galmaa'an, gurmaa'an, waraqaa ragaa qaama seerummaa itti argatan qaama dhimmi ilaalu waliin ni hojjata;
26) Tooftaalee adda addaatti fayyadamuun tarsiimoo misooma intarpiraayizoota maayikiroo fi xixiqqaa fi tarsiimoo wabii nyaataa magaalotaa irratti hubannoon hawaasaa akka cimu ni taasisa;
27) Intarpiraayizoota maayikiroo fi xixiqqaa damee maanufaakcharingii ala jiran gorsa qabiinsa herregaa fi tajaajila odiitii akka argatan deeggarsa ni taasisa;
28) Manni Maree carraa hojii uumuu fi wabii nyaataa magaalotaa sadarkaa hundatti akka hundeeffamu ni taasisa; hojii mana marichaa ni qindeessa; deeggarsa barbaachisaa ni kenna;

፳) ሥራ አጥ ዜጎች በክልሉ ውስጥ ለሚፈጠሩ ሥራ ዕድል እንደየፍላጎታቸው፣የንግድ ህግና በሕብረት ሥራ ማሕበራት ላይ በመመሰረት በግል ወይም በማህበር ያደራጃል፣የንግድ ፈቃድና ህጋዊ ሰውነት እንዲያገኙ ያደርጋል፤
፳፩) ከማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ውጭ ያሉት የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ከድርጅቶች፣ከኮሌጆች፣ ከፖሊቴክኒክ ኮሌጆች፣ ከጥቃቅን የፋይናንስ አቅራቢ ድርጅቶችና የሊዝ መሳሪያ አቅራቢ ጋር በመሆን የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን፣ ብድርና የማሽን አገልግሎት የሚያገኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤
፳፪) የከተሞች ሥራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ድጋፍን ለማፋጠን የተዘጋጁ ፓከጆችን ሥራ ላይ ያውላል፤
፳፫) የሥራ ዕድል ለሚፈጠረላቸው ሰዎች ወይም ድርጅቶች በቂ የሆነ የማምረቻና የመሸጫ ቦታ መዘጋጀቱን ያረጋግጣል፤
፳፬) የአንድ ቦታ የአገልግሎት መስጫ ማዕከላትን ያደራጃል፣ያጠናክራል፣ቀልጣፋ አገልግሎት መስጠት የሚያስችሉ የተሻሉና አዲስ ስርዓቶችን ይዘረጋል፣የማዕከላቱን አቅም ይገነባል፤
፳፭) በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ላይ ከተሰማሩት ውጭ ያሉት የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የሚመዘገቡበት፣የሚደራጁበት፣የህጋዊ ሰውነት ምሥክር ወረቀት የሚያገኙበት ሥርዓት እንዲኖር ጉዳዩ ከሚመለከተው አካል ጋር ይሠራል፤
፳፮) የተለያዩ ሥልቶችን በመጠቀም በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የልማት ስትራቴጂና የከተሞች ምግብ ዋስትና ስትራቴጂ ላይ የህብረተሰቡ ግንዛቤ እንዲጠናከር ያደጋል፤
፳፯) ከማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ውጭ ያሉ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የሒሣብ አያያዝ ምክርንና የኦዲት አገልግሎትን እንዲያገኙ ድጋፍ ያደርጋል፤
፳፰) የከተሞች ሥራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ምክር ቤት በሁሉም ደረጃ እንዲቋቋም ያደርጋል፣የምክር ቤቱን ሥራ ያቀናጃል፤ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤

20) Organize the jobless citizens privately or in association as per their own interest for the job opportunity to be created in the region depending on the commercial law and cooperative association; cause them acquire trade license and legal personality;
21) Facilitate conditions whereby they can acquire industrial extension, loans and machine services by working in collaboration with the micro and small scale enterprises which are out of manufacturing branch the institutes, colleges and polytechnic colleges and the small scale finance and lease materials supplying organizations;
22) Implement the support packages prepared for speeding up the urban job opportunity creation and food security;
23) Ensure the preparation of enough production and selling places for the persons or organizations for which the job opportunity is created;
24) Organize one stop service delivery centers; strengthen them; establish a new and reform system which help to deliver effective services; build up the abilities of the centers;
25) Work with the concerned body on extending the system whereby the micro and small scale enterprises which are out of those engage on manufacturing branch be registered, organized, acquire legal personality certificate;
26) Make the societies' understanding to be promoted using various mechanisms on the strategies of the micro and small scale enterprises developments and on the strategies of the urban food security;
27) Make support for the micro and small scale enterprise which are out of the manufacturing branch to get financial management consultancy and audit services;
28) Cause the establishment of the urban job opportunity creation and food security council at all levels; organize the activities of the council; provide the required support;

29) Intarpiraayizoota maayikiroo fi xixiqqaa damee maanufaakcharingii ala jiran irraa gara guddattuu giddugaleessaatti ni ceesisa; waraqaa ragaa ni kenna; adda baasee ragaa ni qabata; qaama dhimmi ilaalutti dabarsuun deeggarsa akka argatan ni taasisa;
30) Herrega intarpiraayizoota maayikiroo fi xixiqqaa damee maanufaakcharingii ala jiran ni qorata; akka qoratamu ni taasisa; raawwii fi qabiinsa qabeenya isaanii irratti hojii inispeekshinii ni gaggeessa; tarkaanfii sirreeffamaa ni fudhata.

**49. Ejensii Babal'ina Waldaa Hojii Gamtaa**

Ejensichi aangoo fi hojii armaan gadii ni qabaata:

1) Imaammata, tarsiimoo, sagantaalee fi seerota waldaa hojii gamtaa ni qopheessa; yammuu hayyamamu hojiirra ni oolcha;
2) Hawaasni magaalaa fi baadiyyaa faayidaa waldaa hojii gamtaa irratti hubannoo akka argatu hojii hubannoo uumuu ni hojjata; ni gurmeessa; ni galmeessa; waraqaa qaama seerummaa ni kenna; ni haqa; ni hordofa; ni too'ata;
3) Waldaaleen hojii gamtaa haala miseensota isaanii fi hawwaasaaf callaa guddistuu, oomisha industirii fi qonnaa fi liqii itti dhiyeessuu danda'an irratti ni hojjata;
4) Sochii hojii waldaalee hojii gamtaa cimsuuf yuuniyeenii yookiin federeeshiniidhaan akka gurmaa'an ni taasisa; walitti dhufeenyi isaanii akka cimu ni hojjata;
5) Waldaaleen hojii gamtaa sochii investimentii irratti akka hirmaatanii fi oomisha qonnaa gara oomisha industiriitti akka jijjiiran deeggarsa ogummaa barbaachisaa ta'e ni kenna; ni jajjabeessa;
6) Dandeettii gaggeesitootaa, hojjattoota waldaalee fi miseensoota waldaa hojii gamtaa ni cimsa; leenjii ni kenna; akka kennamuu qaama dhimmi ilaalu waliin ni hojjata; gidduugaleessa leenjii waldaalee hojii gamtaa ni hundessa; ni bulcha;

፳፱) ከማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ውጭ ያሉ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ወደ መካከለኛ አዳጊ ያሸጋግራል፤ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤ መረጃቸውን ለይቶ ይይዛል፤ ጉዳዩ ለሚመለከተው አካል በማስተላለፍ ድጋፍ እንዲያገኙ ያደርጋል፤
፴) ከማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ውጭ ያሉ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ሂሣብን ይመረምራል፤ እንዲመረመር ያደርጋል፤ በአፈፃፀምና በንብረት አያያዛቸው ላይ የኢንስፔክሽን ሥራ ያካሄጋል፤ የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል።

**፵፱. የሕብረት ሥራ ማሕበራት ማስፋፊያ ኤጀንሲ**

ኤጀንሲው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

፩) የሕብረት ሥራ ማሕበራት ፖሊሲ፣ ስትራቴጂ፣ ፕሮግራሞችንና ህጎችን ያዘጋጃል፤ሲፈቀድም ሥራ ላይ ያውላል፤
፪) የከተማና የገጠሩ ህብረተሰብ በሕብረት ሥራ ማሕበራት ጥቅም ላይ ግንዛቤ እንዲያገኙ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራን ይሰራል፤ ያደራጃል፤ ይመዘግባል፤ የህጋዊ ሰውነት ምስክር ወረቀት ይሰጣል፤ይሠርዛል፤ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤
፫) የሕብረት ሥራ ማሕበራት ለአባሎቻቸውና ለህብረተሰቡ የምርት ማሣደጊያ ግብዓቶችን፣የኢንዱስትሪና የግብርና ምርቶችንና ብድር ማቅረብ በሚችሉበት ሁኔታ ላይ ይሠራል፤
፬) የሕብረት ሥራ ማሕበራትን የሥራ እንቅሥቃሴ ለማጠናከር በዩኒየን ወይም በፌዴሬሽን እንዲደራጁ ያደርጋል፤ግንኙነታቸው እንዲጠናከር ይሠራል፤
፭) የሕብረት ሥራ ማሕበራት በኢንቨስትመንት እንቅሥቃሴ ላይ እንዲሣተፉና የግብርና ምርቶችን ወደ ኢንዱስትሪ ምርቶች እንዲቀይሩ አስፈላጊውን የሞያ ድጋፍ ይሰጣል፣ያበረታታል፤
፮) የሕብረት ሥራ ማሕበራት አመራሮችን፣ የማሕበራት ሠራተኞችንና የአባሎችን ችሎታ ያጠናክራል፣ ስልጠና ይሰጣል፣እንዲሰጥ ከሚመለከተው አካል ጋር ይሠራል፤የሕብረት ሥራ ማሕበራት የስልጠና ማዕከልን ያቋቁማል፣ ያስተዳድራል፤

29) Promote the micro and small scale enterprises which are out of manufacturing branch in to developing medium enterprises; provide certificate; keep evidences isolate; make them acquire support by transferring to the concerned body;
30) Examine the financial accounts of the micro and small scale enterprises which are out of the manufacturing branches; cause same to be examined; conduct inspection activity on their performances and property managements; take corrective measure.

**49. Co-operative Association Expansion Agency**

The Agency shall have the following power and duties:

1) Prepare policy, strategy, programs and laws regarding co-operative association; implement same upon approval;
2) Create awareness for urban and rural community on the importance of co-operative association; organize, register, give legal personality certificate, cancel, follow up and control;
3) Work on how co-operative associations can provide production enhancement inputs, industrial and agricultural products and loan for their members and the community;
4) Cause co-operatives to be organized in union or federation to strengthen their activities, cause their relationship to be strengthened;
5) Give necessary professional support and encourage co-operative associations to participate on investment activities and process agricultural products to industrial products;
6) Build up the capacity of leaders, workers and members of co-operative associations; give training, training to be given work with concerned body; establish and administer co-operative associations training center;

7) Herrega waldaalee hojii gamtaa ni qorata; akkaataa barbaachiisummaa isaatti dhaabbata odiitii beekamtii seeraa qabu bakka buusuun akka qoratamu ni taasisa; raawwii isaas ol'aantummaan ni hordofa; bu'aa qorannoo odiitii yaa'ii waliigalaaf ni dhiyeessa;
8) Odiitaroota waldaalee hojii gamtaa ni leenjisa; ni ramada; waraqaa gahumsaa ni kenna; ni haqa;
9) Raawwii hojii waldaaleen hojii gamtaa waliigalaa, qabiinsa herregaa fi bulchiinsa qabeenyaa seeraan qofa hojjachuu isaanii hojii inispeekshinii ni gageessa; bu'aa qorannoo inispeekshinii irratti hundaa'ee tarkaanfii seeraa ni fudhata; qaama dhimmi ilaalu waliin akka fudhatamu ni taasisa;
10) Qisaasama maallaqaa fi qabeenyaa waldaalee hojii gamtaa keessatti raawwatamu irratti akkaataa seeraatiin tarkaanfii ni fudhata; akka fudhatamu ni taasisa;
11) Waldhabiinsa waldaalee hojii gamtaa waliin walqabatanii uumamaan furmaata akka argatan haala ni mijeessa; addaan bahiinsa, walitti makamiinsaa fi diigamuu waldaalee hojii gamtaa ilaalchisee akkaataa seeraatiin sirreeffama barbaachisaa ta'e ni taasisa;
12) Waldaaleen hojii gamtaa sirna hojimaata fooyya'aa ta'e akka diriirfatan ni taasisa; yeroo yeroon qoratee ni sirreessa;
13) Pirojektoota guddina waldaalee hojii gamtaatiif gargaaran akka qophaa'an deeggarsa ogummaa ni kenna;
14) Miseensotni waldaalee hojii gamtaa oomisha isaanitiif gatii fooyya'aa akka argatan ni hojjata; qorannoo gabaa waldaalee hojii gamtaa ni gaggessa; odeeffannoo gabaa ni kenna; qaama dhimmi ilaalu waliin qindoominaan ni hojjata;
15) Dhaabbilee mootummaa, miti mootummaa fi qaama biroo dhimma waldaa hojii gamtaa irratti hojjatan waliin walitti dhufeenya ni taasisa; waliin ni hojjata; ni qindeessa;

፯) የሕብረት ሥራ ማሕበራትን ሂሣብ ይመረምራል፣እንደአስፈላግነቱ የህግ እውቅና ያለው የኦዲት ተቋም ወክሎ እንዲመረመር ያደርጋል፤ አፈፃፀሙንም በበላይነት ይከታተላል፤ የኦዲት ምርመራ ውጤት ለጠቅላላ ጉባዔዉ ያቀርባል፣
፰) የሕብረት ሥራ ማሕበራት ኦዲተሮችን ያሰለጥናል፤ ይመድባል፣ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤ ይሰርዛል፤
፱) የአጠቃላይ የሕብረት ሥራ ማሕበራት የሥራ አፈፃፀም፣የሂሣብ አያያዝና የንብረት አያያዝን ህጋዊ በሆነ መንገድ ብቻ መስራተቸውን የኢንስፔክሽን ያካሄዳል፤ በኢንስፔክሽን ምርመራ ውጤት ላይ ተመሥርቶ ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል፤ ጉዳዩ ከሚመለከተው አካል ጋር እንዲወሰድ ያደርጋል፣
፲) በሕብረት ሥራ ማሕበራት ውስጥ በሚፈፀመው የገንዘብና የንብረት ብክነት ላይ በህግ መሰረት እርምጃ ይወስዳል፤እንዲወሰድም ያደርጋል፣
፲፩) ከሕብረት ሥራ ማሕበራት ጋር የተያያዙ አለመግባባቶች መፍትሄ እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤ የሕብረት ሥራ ማሕበራትን መቀላቀል፣ መከፋፈልና መፍረስን አስመልክቶ በህግ መሰረት አስፈላጊውን ማስተካከያ ያደርጋል፤
፲፪) የሕብረት ሥራ ማሕበራት የተሻለ የአሰራር ስርዓት እንዲዘረጉ ያደርጋል፤ በየጊዜው እያጠና ያስተካክላል፤
፲፫) ለሕብረት ሥራ ማሕበራት ዕድገት የሚረዱ ፕሮጀክቶች እንዲዘጋጁ የሞያ ድጋፍ ይሰጣል፤
፲፬) የሕብረት ሥራ ማሕበራት አባላት ለምርቶቻቸው የተሻለ ዋጋ እንዲያገኙ ይሠራል፤የሕብረት ሥራ ማሕበራት የገበያ ጥናት ያካሄዳል፤ የገበያ መረጃን ይሰጣል፤ጉዳዩ ከሚመለከተው አካል ጋር በቅንጅት ይሠራል፤
፲፭) በሕብረት ሥራ ማሕበራት ጉዳይ ላይ ከሚሠሩ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶችና ሌሎችም ጉዳዩ ከሚመለከታችው አካላት ጋር ግንኙነት ያደርጋል፤አብሮአቸው ይሰራል፤ ያቀናጃል፤

7) Examine accounts of co-operative associations, cause to be examined by replacing audit organization having legal accreditation as it is necessary; control its implementation chiefly; present the audit inspection result for general assembly;
8) Train and assign the auditors of co-operative associations; give the competency certificate; cancel;
9) Undertake inspection on the overall work performance of co-operative associations; their book of account and resource management is worked according to law; take legal measure based on the result of the inspection; cause to be taken with concerned body;
10) Take measure according to law on the wastage of cash and resource undertaken within co-operative associations; cause to be taken;
11) Facilitate conditions for conflicts raised among co-operative associations to be solved, make necessary correction regarding division, amalgamation, dissolution of co-operative associations;
12) Cause co-operative association establish improved work procedure; investigate and correct periodically;
13) Give professional support for preparation of projects which help for development of co-operative association;
14) Work members of co-operative associations to get better price for their products; undertake co-operative associations market study; give market information; work in coordination with concerned body;
15) Make relation with governmental and nongovernmental organizations and other concerned organs working on co-operative associations, work with and coordinate;

16) Aadaan qusannoo miseensoota waldaalee hojii gamtaa biratti akka babal'atu ni hojjata;
17) Waldaaleen hojii gamtaa misooma naannoo isaanii keessatti akka hirmaatan ni jajjabessa.
18) Bittaa callaa guddistuu biyya keessaa fi alaa ni raawwata; akkaataa barbaachiisummaa isaatti bittaa callaa guddistuu karaa yuuniyeenootaa, federeshinii yookiin qaamolee biraa bakka buusuun bittaan akka raawwatamu ni taasisa;
19) Madda liqii bittaa callaa guddistuuf barbaachisu ni mijeessa; liqii argame ni bulcha; qaama liqeesseef akka deebi'u ni taasisa;
20) Akkaataa fedhii dhiyaatuun callaa guddistuu ni bita; akka bitamu ni taasisa; qonnaan bultootaa fi horsiisee bultootaaf akka raabsaman ni taasisa;
21) Galiin gurgurtaa callaa guddistuu qonnaa fi teeknolojii qonnaan bultootaa fi horsiisee bultootaaf dhiyaatan haala seera qabeessa ta'een walitti qabamee qaama dhimmi ilaaluuf galii akka ta'u ni hojjata;
22) Sochii hojii waldaalee hojii gamtaa yeroo yeroon gamaaggamuun sadarkaa gahumsaa fi beekamtii ni kenna;
23) Tajaajila ekisteenshinii misooma waldaalee hojii gamtaatiif ni kenna; ni hordofa; ni too'ata;
24) Moodeela dambii hundeeffamaa fi ittiin bulmaataa waldaalee hojii gamtaatiif qopheessee ni kenna; kan qophaa'ee dhiyaatu xiinxaluun ni mirkaneessa; hojiirra oolmaa isaa ni hordofa.

**50. Ejensii Misoomaa fi Manajimantii Lafa Magaalaa**

Ejensichi aangoo fi hojii armaan gadii ni qabaata:

1) Imaammataa fi tarsiimoo misoomaa fi manajimantii lafa magaalaa hojiirra ni oolcha; hojiirra akka oolu ni taasiisa; ni hordofa; ni too'ata.
2) Sirna hammayyaa'aa misoomaa, dhiyeessaa fi manajimantii lafa magaalaa qophaa'e hojiirra ni oolcha; hojiirra akka oolu ni taasisa;

፲፮) የቁጠባ ባህል በሕብረት ሥራ ማሕበራት አባሎች ዘንድ እንዲስፋፋ ይሰራል፣
፲፯) የሕብረት ሥራ ማሕበራት በአካባቢያቸው ልማት ውስጥ እንዲሣተፉ ያበረታታል፤
፲፰) የውጭ ሀገርና የሀገር ውስጥ የምርት ማሳደጊያ ግዢ ይፈፅማል፤ እንደአስፈላጊነቱ የምርት ማሳደጊያ ግዢ በዩንየን፣ በፌዴሬሽን ወይም ሌላ አካል በመወከል ግዢ እንዲፈፀም ያደርጋል፤
፲፱) ለምርት ማሳደጊያ ግዢ የሚያስፈልግ የብድር ምንጭ ያመቻቻል፤ የተገኘውን ብድር ያስተዳድራል፤ላበደረው አካል እንዲመለስ ያደርጋል፤
፳) በቀረበው ፍላጎት መሰረት ምርት ማሳደጊያን ይገዛል፤ እንዲገዛ ያደርጋል፤ ለአርሶ አደሮችና ለአርብቶ አደሮች እንዲሰራጭ ያደርጋል፤
፳፩) የምርት ማሳደጊያ ሽያጭና ለአርሶ አደርና አርብቶ አደር የሚቀርበው ቴክኖሎጂ ገቢ ህጋዊ በሆነ ሁኔታ ተሰብስቦ ለሚመለከተው አካል ገቢ እንዲደረግ ይሰራል፤
፳፪) የሕብረት ሥራ ማሕበራትን የሥራ እንቅስቃሴ በየጊዜው በመገምገም የብቃት ደረጃና እውቅና ይሰጣል፣
፳፫) ለሕብረት ሥራ ማሕበራት ልማት የኤክስተንሽን አገልግሎት ይሰጣል፤ ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤
፳፬) የማቋቋሚያና የመመስረቻ ሞዴል ደንብ አዘጋጅቶ ለሕብረት ሥራ ማሕበራት የሰጣል፤ ተዘጋጅቶ የቀረበውን መረምሮ ያፀድቃል፤ ሥራ ላይ መዋሉንም ይከታተላል፡፡

**፶ የከተማ መሬት ልማትና ማኔጅመንት ኤጀንሲ**

ኤጀንሲው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩) የከተማ መሬት ልማትና ማኔጅመንት ፖሊሲና እስትራቴጂ በስራ ላይ ያውላል፤ በስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤ ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤
፪) የተዘጋጀውን ዘመናዊ የከተማ መሬት ልማት፣አቅርቦትና ማኔጅመንት ስርዓት ሥራ ላይ ያውላል፤ ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

16) Work to promote saving culture of members of co-operative associations;
17) Encourage co-operative associations to participate in the development of their areas;
18) Undertake procurement of production enhancement inputs within and out of the Country; cause procurement of production enhancement inputs to be undertaken through union or federation or by representing other bodies;
19) Facilitate source of loan for production enhancement inputs procurement; administer the loan obtained; cause it to be returned to the debtor;
20) Procure production enhancement inputs according to the demand submitted; cause its procurement; cause it to be distributed for farmers and pastoralists;
21) Work income from sell of agricultural production enhancement inputs and technology presented for farmers and pastoralists to be collected legally and submitted to the concerned body;
22) Evaluate work movement of co-operative associations periodically and give competence level and recognition;
23) Give extension service for co-operative associations development; follow up and control;
24) Prepare and give model memorandum of association and article of association for co-operative associations; analyze and approve the prepared and submitted once; follows up its implementation;

**50. Urban Land Development and Management Agency**

The Agency shall have the following powers and duties:

1) Implement or cause the implementation of the policy and strategy of urban land management; follow-up and supervise same;
2) Implement; cause the implementation of the prepared modern development, supply and management of urban land system;

3) Seera liizii fi seerota biroo hojii misoomaa fi manajimantii lafa magaalaa waliin walqabatan hojiirra ni oolcha; hojiirra oolmaa isaa ni hordofa; ni too'ata;
4) Sirna kenniinsa tajaajilaa fi bulchiinsa lafa magaalaa iftoomina, si'ataa, qulqullinaa fi itti gaafatamummaa mirkaneessuuf bahe hojiirra ni oolcha; hojiirra oolmaa isaa ni hordofa; ni too'ata;
5) Lafa magaalaa Investimentii fi tajaajila misooma adda addaatiif oolu, bu'uurri misoomaa guutameef, falmii fi mormii adda addaa irraa bilisa ta'e qoratee ni qopheessa; baankii lafaatti ni kuusa; akkaataa seeraatiin qaama hayyamameef ni dabarsa; kaayyoo barbaadameef ooluu isaa ni hordofa; bakka hanqinni jirutti tarkaanfii sirreeffamaa ni fudhata; akka fudhatamu ni taasisa;
6) Ragaa lafa magaalaa hojii investimentiitiif oolu Komishinii Investimentiitii fi qaama dhimmi ilaaluuf ni dabarsa;
7) Iddoowwan magaalaa dullooman qoratee adda ni baasa; deebi'ee akka misoomu qaama dhimmi ilaalu waliin haala ni mijeessa; raawwii isaa ni hordofa;
8) Lafa magaalaa tajaajila adda addaatiif kenname akkaataa seeraatiin hojiirra ooluu isaa ni hordofa; ni too'ata; hanqinni yoo mul'ate tarkaanfii seeraa ni fudhata; akka fudhatamu ni taasisa;
9) Ulaagaa pirojektootni investimentii lafa magaalaa irratti dhiyaatan ittiin xiinxalamu Komishinii Investimentii naannichaa waliin ni qopheessa; pirojektii investimentii ni xiinxala; kanneen fudhatama argatan hojiirra akka oolan ni taasisa; ni hordofa; ni too'ata; raawwiin isaa qajeelfama bahuun kan murtaa'u ta'a;
10) Gaaffii lafa magaalaa akkaataa seera liiziitiin simachuun Mana Maree Bulchiinsa Mootummaa Naannichaatiif yookiin qaama inni bakka buusuuf ni dhiyeessa; yammuu murtaa'u hojiirra akka oolu ni taasisa; hojiirra oolmaa isaa ni hordofa; bakka hanqinni jirutti qaama dhimmi ilaallatu waliin tarkaanfii ni fudhata; akka fudhatamu ni taasiisa.

፫) ከከተማ መሬት ልማትና ማኔጅመንት ስራ ጋር የተያያዙ የሊዝ ህጎችና ሌሎች ህጎች ስራ ላይ ያውላል፤ ሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤
፬) ግልፅነት፣ ቀልጣፋ፣ ጥራት እና ተጠያቂነት ያለው የከተማ መሬት አገልግሎት አሰጣጥና አስተዳደርን ለማረጋገጥ የወጣ ሥርዓት ሥራ ላይ ያውላል፤ ሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤
፭) ለኢንቨስትመንትና ለተለያዩ የልማት አገልግሎት የሚውል፣ መሰረተ ልማት የተሟላለት፣ ከተለያዩ ክርክርና ተቃውሞ ነፃ የሆነ የከተማ መሬት አጥንቶ ያዘጋጃል፤በመሬት ባንክ ያከማቻል፤ ለተፈቀደለት አካል በህግ መሰረት ያስተላልፋል፣ ለተፈለገው ዓላማ መዋሉን ይቆጣጠራል፤ ጉድለት ባለበት አስፈላጊውን የማስተካከያ ዕርምጃ ይወስዳል፤ እንዲወሰድ ያደርጋል፤
፮) ለኢንቨስትመንት ሥራ የሚውል የከተማ መሬት ማስረጃ ለኢንቨስትመንት ኮሚሽንና ጉዳዩ ለሚመለከተው አካል ያስተላልፋል፤
፯) ያረጁ የከተማ ቦታዎችን በማጥናት ይለያል፤ መልሶ እንዲለማ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን ሁኔታን ያመቻቻል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤
፰) ለተለያየ አገልግሎት የተሰጠ የከተማ መሬት በሕግ መሰረት ሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤ ጉድለት ሲታይ ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል፤ እንዲወሰድ ያደርጋል፤
፱) በከተማ መሬት ላይ የሚቀርቡ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክት የሚመረመሩበትን መስፈርት ከክልሉ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ጋር ያዘጋጃል፤የኢንቨስትመንት ፕሮጀክትን ይመረምራል፤ ተቀባይነት ያገኙትን ሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤ አፈጻጸሙ በደንብ የሚወሰን ይሆናል፤
፲) በሊዝ ህግ መሰረት የሚቀርብ የከተማ መሬት ጥያቄን በመቀበል ለክሉ መንግሥት መስተዳድር ምክር ቤት ወይም እሱ ለሚወክለው ያቀርባል፤ ሲወሰን ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤ ሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፤ ጉድለት ባለበት ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን እርምጃ ይወስዳል፤ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

3) Implement lease and other laws related to the development and management activities of urban lands; follow-up its implementation; supervise same;
4) Implement the service provision and administration system of urban land prepared to ensure transparency, effectiveness, quality and accountability; follow-up its implementation; supervise same;
5) Investigate and prepare urban land to be used for the investment activity and various development services which the infrastructure is fulfilled for, free from different claims; deposit in land bank; transfer to the body permitted for in accordance with the law; follow-up its being used for the purpose intended; take corrective measure where there exist limitations; cause it to be taken;
6) Transfer the evidences of urban land to be used for the investment activity to the Investment Commission and to the concerned body;
7) Study and identify the old urban lands; facilitate condition of its renewed development with the concerned body; follow-up its implementation;
8) Follow-up the urban land provided for various services to be implemented in accordance with the law; supervise; take lawful measure where limitation exists; cause it to be taken;
9) Prepare criteria where by the investment project submitted on urban land be analyzed in collaboration with the Investment Commission of the region; analyze investment projects; cause the implementation of the accepted ones; follow-up; supervise; its implementation shall be decided by the regulation to be issued;
10) Entertain the question of urban land as per the lease law and submit to the Regional Administration Council or to the body it represents; cause its implementation when decided; follow-up its implementation; take measure with the concerned body where there is limitation; cause it to be taken;

11) Abbootii qabeenyaa hojii investimentiitiif lafa magaalaa fudhatan bulchiinsa magaalaa waliin waliigaltee akka mallatteessan ni taasisa; akkaataa waliigalteetiin hojiirra yoo hin oole tarkaanfii sirreeffamaa ni fudhata; akka fudhatamu ni taasisa; waliigaltee mallattaa'e galmeessee ni qaba; Komishinii Investimentii naannichaa fi qaama dhimmi ilaaluuf ragaa isaa ni dabarsa;
12) Gaaffii jijjiirra gosa pirojektii investimentii lafa magaalaa pilaanii fi seera jiru irratti hundaa'uun ni raawwata; Komishinii Investimentii fi qaama dhimmi ilaalu kan biroo ni beeksisa; raawwii isaa ni hordofa; ni too'ata;
13) Magaalaa keessatti shallaggii beenyaa namoota qabiyyee lafa isaanii irraa ka'aniif akkaataa seeraatiin akka raawwatamu ni taasiisa; kaffaltiin beenyaa osoo lafa isaanii irraa hin ka'in dursee akka kaffalamuuf ni taasiisa; qaama dhimmi ilaalu waliin ni hojjata;
14) Kaffaltiin beenyaa gabaa yeroo irratti kan hundaa'e akka ta'u qorannoo gaggeessuun qaama dhimmi ilaaluuf ni dhiyeessa; yammuu mirkanaa'u hojiirra ni olcha;
15) Namoota qabiyyee lafa magaalaa isaanii gadi lakkisan deebi'anii akka of danda'an qaama dhimmi ilaallatu waliin ni hojjata;
16) Sirna itti fayyadama pilaanii lafa magaalaa galma misooma magaalotaa milkeessuuf seerota bahanii fi hojimaata diriire hojiirra ni oolcha; hojiirra akka oolu ni taasisa;
17) Lafti magaalaa pilaanii magaalaa eegee qusannoodhaan faayidaa ol'aanaaf akka oolu ni taasisa; pilaaniin magaalaa sadarkaa isaa eeggatee akka qophaa'u deeggarsa barbaachisaa ta'e ni kenna;
18) Magaalota keessaa fi daangaa magaalotaa irratti ijaarsi seeraan alaa akka hin raawwatamne qaama dhimmi iaallatu waliin ni hojjata; qajeelfamaa fi hojimaata qophaa'e hojiirra ni oolcha; hojiirra oolmaa isaa ni hordofa; ni too'ata; tarkaanfii seeraa ni fudhata; akka fudhatamu ni taasiisa;

፲፩) ለኢንቨስትመንት ሥራ የከተማ መሬትን የወሰዱ ባለሃብቶች ከከተማ አስተዳደር ጋር ውል እንዲፈራረሙ ያደርጋል፤በውሉ መሠረት ሥራ ላይ ካልዋለ የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፤እንዲወሰድ ያደርጋል፤ የተፈፀመውን ውል መዝግቦ ይይዛል፤ለክልሉ ኢንቨስትመንት ኮሚሽንና ለሚመለከተው አካል መረጃውን ያስተላልፋል፤
፲፪) የከተማ መሬት የኢንቨስትመንት ፕሮጀክት አይነት የመቀየር ጥያቄ ባለው ፕላንና ህግ ላይ በመመስረት ይፈፅማል፤ለኢንቨስትመንት ኮሚሽንና ሌላ ለሚመለከተው አካል ያሳውቃል፤አፈጻጸሙንም ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤
፲፫) በከተማ ውስጥ ከይዞታቸው ለሚነሱ ሰዎች በህጉ መሰረት ካሳ እንዲገመትላቸው ያደርጋል፤ ከመሬታቸው ሣይነሱ አስቀድሞ ካሣ እንዲከፈላቸው ያደርጋል፤ከሚመለከተው አካል ጋር ይሠራል፤
፲፬) የካሣ ክፍያ በወቅቱ ገበያ ላይ የተመሠረተ እንዲሆን ጥናት በማካሄድ ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፤ሲፀደቅ ሥራ ላይ ያውላል፤
፲፭) ከከተማ ይዞታቸው የተነሱ ሰዎች መልሰው እንዲቋቋሙ ጉዳዩ ከሚመለከተው አካል ጋር ይሰራል፤
፲፮) የከተማ መሬት ፕላን አጠቃቀም ስርዓት የከተማ ልማት ግብ ለማሣካት የወጡ ህጎችና የተዘረጋ አሰራር ሥራ ላይ ያውላል፤ሥራ ላይ እንዲውልም ያደርጋል፤
፲፯) የከተማ መሬት የከተማ ፕላንን ጠብቆ በቁጠባ ለከፍተኛ ጠቀሜታ እንዲውል ያደርጋል፤ደረጃውን የጠበቀ የከተማ ፕላን እንዲዘጋጅ አስፈላጊ የሆነ ድጋፍ ይሰጣል፤
፲፰) በከተሞች ውስጥና በከተሞች ድንበር ላይ ህገ ወጥ ግንባታ እንዳይፈፀም ጉዳዩ ከሚመለከተው አካል ጋር ይሰራል፤ ያተዘጋጀዉነ መመሪያና አሰራር ሥራ ላይ ያውላል፤ሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤ ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል፤ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

11) Cause the private investors who have taken urban land for investment activity to conclude contractual agreement with the city administration, take or cause to be taken corrective measure where failed to be implemented as per the contractual agreement ; register and keep the signed contract; transfer its evidences to the Investment Commission of the region;
12) Perform the conversion request of the urban land investment project type depending on the plan and the existing law; notify Investment Commission and other concerned body; follow up and supervise its implementation;
13) Cause the estimation of the compensation for the persons displaced from their land possessions in the urban centers to be conducted according to the law; cause the compensation to be paid for them before they are displaced from their possession; work with the concerned body;
14) Undertake a study and submit to the concerned body to make the payment of compensation to depend on the current market; impalement up on approval;
15) Work with the concerned body to enable the persons displaced from their urban lands to be rehabilitated;
16) Implement the urban land plan utilization system; the laws enacted and work procedure established for the achievement of the urban development goal;
17) Cause the urban land to be used economically for greater benefit by respecting urban plan; provide the necessary support for the preparation of standardized urban plan;
18) Work with the concerned body for the avoidance of unlawful construction in the urban centers and on their borders; implement the directive and work procedure prepared; follow-up its implementation, supervise; take legal measure; cause same to be taken;

19) Magaalota sirna liizii keessa hin galle qaama dhimmi ilaalu waliin qoratee Mana Maree Bulchiinsa Mootummaa Naannichaatiif ni dhiyeessa; yammuu mirkanaa'u hojiirra ni oolcha; hojiirra akka oolu ni taasiisa; hojiirra oolmaa isaa ni hordofa;
20) Gatii ka'umsa liizii lafa magaalaa qaama dhimmi ilaalu waliin qoratee Mana Maree Bulchiinsa Mootummaa Naannichaatiif ni dhiyeessa; yammuu murtaa'u hojiirra ni oolcha; hojiirra akka oolu ni taasiisa
21) Investaroota lafa magaalaa irratti hojii investimentii gaggeessaniif jajjabeessituuwwan hayyamaman akkaataa seeraatiin ni raawwata.

## 51. Ejensii Galmeessa Qabiyyee Lafaa fi Ragaa Lafa Magaalaa

Ejensichi aangoo fi hojii armaan gadii ni qabaata:

1) Seerotnii fi istaandardiiwwan galmeessa qabiyyee lafaa fi ragaa lafaa ilaalchisee bahan magaalota naannichaa keessatti bifa walfakkaatuun hojiirra ni oolcha; hojirra ooluu isaanii ni mirkaneessa;
2) Seera irratti hundaa'uudhaan mirga itti fayyadamaa, dhorkaa fi ittigaafatamummaa qabiyyee lafa magaalaa ni galmeessa; akka galmaa'u ni taasisa; ni haaromsa; ni sirreessa; ni haqa;
3) Seera irratti hundaa'uudhaan waraqaa ragaa mirkaneessa mirga abbaa qabiyyummaa lafa magaalaa ni kenna; ni galmeessa;
4) Hojiiwwan mirkaneessa qabiyyee iddoo adda bahee daangeffame tokko keessatti adeemsa mirgi qabiyyee jiru walitti aansamee itti mirkanaa'u ofii isaatiif ni gaggeessa; akkasumas gaaffii abbaa qabiyyee lafaa irratti hundaa'uudhaan iddoo adda bahee daangeffame tokko keessatti mirga abbaa qabiyyee ni mirkaneessa;
5) Ragaa fi odeeffannoo lafaa fi qabeenya lafa magaalaa waliin walqabatan walitti ni qaba; sirna kaadastaraatiin akka qabamuu fi gurmaa'u ni taasisa; ni gurmeessa; ni bulcha; qaama dhimmi ilaaluuf ni tamsaasa;

፲፱) የሊዝ ሥርዓት ውስጥ ያልገቡ ከተሞችን ከሚመለከተው አካል ጋር አጥንቶ ለክልሉ መንግስት መስተዳድር ምክር ቤት ያቀርባል፤ ሲፀድቅም ሥራ ላይ ያውላል፤ ሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፤
፳) የከተማ መሬት የሊዝ መነሻ ዋጋን ከሚመለከተው አካል ጋር በማጥናት ለክልሉ መንግስት መስተዳድር ምክር ቤት ያቀርባል፤ ሲወሰንም ሥራ ላይ ያውላል፤ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤
፳፩) በከተማ መሬት ላይ የኢንቨስትመንት ሥራ ለሚያካሄዱ ኢንቨስተሮች የተፈቀዱ ማበረታቻዎችን በህግ መሠረት ይፈፅማል፡፡

## ፶፩. የከተማ መሬት ይዞታና መረጃ ምዝገባ ኤጀንሲ

ኤጀንሲው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩) የመሬት ይዞታ ምዝገባ እና የመሬት መረጃን አስመልክቶ የወጡ ህጎችና ስታንዳርዶች በክልሉ ከተሞች ውስጥ በተመሳሳይ መልክ ሥራ ላይ ያውላል፤ ሥራ ላይ መዋሉን ያረጋግጣል፤
፪) በህግ ላይ በመመስረት የከተማ መሬት ይዞታ የመጠቀም መብት፤ ክልከላና ኃላፊነት ይመዘግባል፤እንዲመዘገብ ያደርጋል፤ያድሳል፤ያስተካክላል፤ይሰርዛል፤
፫) በህግ ላይ በመመስረት የከተማ መሬት ባለይዞታነት መብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤ ይመዘግባል፤
፬) የይዞታ ማረጋገጫ ሥራዎች ተለይቶ በተከለለ አንድ ቦታ ውስጥ ያለው የባለይዞታነት መብት በተከታታይ የሚረጋገጥበትን ሂደት በራሱ ያካሄዳል፤እንዲሁም በመሬት ባለይዞታው ጥያቄ ላይ በመመስረት ተለይቶ በተከለለ አንድ ቦታ ውስጥ የባለይዞታነት መብት ያረጋግጣል፤
፭) ከከተማ መሬት ጋር የተያያዙ የመሬትና የንብረት ማስረጃና መረጃ ይሰበስባል፤በካዳስተር ሥርዓት እንዲያዙና እንዲደራጁ ያደርጋል፤ያደራጃል፤ያስተዳድራል፤ለሚመለከተው አካል ያሰራጫል፤

19) Investigate the urban that do not enter in to lease system with the concerned body and submit to the Regional Administrative Council; implement up on approval; cause to be implemented; follow-up its implementation;
20) Study the lease benchmark price with the concerned body and submit to the Regional Administrative Council; implement same upon its decision; cause it to be implemented;
21) Provide the incentives permitted for the private investors who have undertaken investment activities on the urban lands in accordance with the law.

## 51. Urban Landholding Registration and Information Agency

The Agency shall have the following powers and duties:

1) Implement the laws and standards enacted regarding registration of landholding and land information in the urban centers of the region uniformly; ensure their implementation;
2) Register rights of utilization, restriction and responsibility of urban land holding; cause it to be registered; renew; rectify; cancel depending on the law;
3) Depending on the law, provide urban landholding right certificate; register same;
4) Conduct itself the process of ascertaining consecutively existing holding rights on landholdings within a defined landholding; as well as ascertain existing holding right on landholdings with in a defined landholding based on the request of the holder;
5) Collect data and information of land and property related with urban land; cause it to be kept and organized in a cadastre system; organize; administer; disseminate to the concerned body;

6 Gaaffii jijjiirraa abbaa qabiyyummaa fi tajaajila qabiyyee lafa magaalaa akkaataa seeraatiin ni raawwata; qaama dhimmi ilaaluuf ni beeksisa; hojiirra oolmaa isaa ni hordofa;

7) Sirna lafti magaalaa adda bahee itti galmaa'uuf qophaa'e hojiirra ni oolcha; hojiirra akka oolu ni taasisa;

8) Ragaa wayitaawaa qabiyyee lafa magaalaa ni calala; ni gurmeessa; qaama dhimmi ilaallatuuf ni kenna; hanqinni yoo mul'ate tarkaanfii seeraa ni fudhata; akka fudhatamu ni taasisa;

9) Istaandardii irratti hundaa'uudhaan koodii yookiin lakkoofsa addaa qabiyyee iddoo kaadaastara seeraatiin galmaa'ee fi daangaan isaa ifatti beekame ilaalchisee ragaa abbaa qabiyyee ni kenna;

10) Ragaa lafaa fi qabeenya qabiyyee lafa wajjin walqabatu dijitaalaa fi waraqaadhaan ni galmeessa; ni bulcha; ni misoomsa; wiirtuu odeeffannoo ragaa qabiyyee lafa magaalaa ta'ee ni tajaajila; ni qaaccessa; qaama dhimmi ilaallatuuf ni kenna;

11) Ragaa sirna odeeffannoo kaadaastara magaalaa ni qindeessa; kaartaa bu'uuraa fi kaartaa kaadaastaraa ni qopheessa; akka qophaa'u ni taasisa; ni bulcha; ni haaromsa;

12) Sirna odeeffannoo kaadaastara seeraa magaalotaa irratti too'annoo nageenya idilee qaama dhimmi ilaallatu waliin ni gaggeessa; rakkoo jiru adda ni baasa; tarkaanfii sirreeffamaa ni fudhata; akka fudhatamu ni taasisa;

13) Sirna teeknolojii kaadaastara seeraa fi bu'uura misooma neetworkii ni misoomsa; akka misoomu ni taasisa; ni fooyyessa; wayitaawaa ni taasisaa; ni bulcha;

14) Ragaalee kaadaastara seeraa akkaataa seerri hayyamuun ummataaf banaa akka ta'u ni taasisa;

15) Sarveeyingii qabiyyee lafaa istaandaardii irratti hundaa'uudhaan daangaa garaagarummaa fudhatamummaa qabu irratti ni murteessa;

፮) የከተማ መሬት ይዞታ የባለይዞታነትና የአገልግሎት ዝውውር ጥያቄ በህግ መሠረት ይፈፅማል፤ለሚመለከተው አካል ያሳውቃል፤ሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፤

፯) የከተማ መሬት ተለይቶ እንዲመዘገብ የተዘጋጀ ሥርዓትን ሥራ ላይ ያውላል፤ ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

፰) የከተማ መሬት ይዞታ ወቅታዊ ማስረጃን ያጣራል፤ያደራጃል፤ ለሚመለከተው አካል ይሰጣል፤ ጉድለት ከታየ ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል፤ እንዲወሰድም ያደርጋል፤

፱) በስታንዳርድ ላይ በመመስረት የይዞታ ኮድ ወይም ልዩ ቁጥር በህጋዊ ካዳስተር የተመዘገበና ወሰኑ በግልፅ የታወቀ ቦታን አስመልክቶ የባለይዞታነት ማስረጃን ይሰጣል፤

፲) የመሬትና ከመሬት ጋር የተያያዘ ንብረት መረጃን በዲጅታልና በወረቀት ይመዘግባል ፤ያስተዳድራል፤ ያለማል፤ የከተማ መሬት ይዞታ ማስረጃ የመረጃ ማዕከል ሆኖ ያገለግላል፤ይተነትናል፤ለሚመለከተው አካል ይሰጣል፤

፲፩) የከተማ ካዳስተር መረጃ ሥርዓት ማስረጃን ያደራጃል፤ መሰረታዊ ካርታና ካዳስተር ካርታን ያዘጋጃል፤እንዲዘጋጅ ያደርጋል፤ያስተዳድራል፤ያድሳል፤

፲፪) የከተማ ህጋዊ ካዳስተር መረጃ ሥርዓት ላይ የመደበኛ ደህንነት ቁጥጥር ከሚመለከተው አካል ጋር ያካሄዳል፤ያለውን ችግር ይለያል፤ የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፤እንዲወሰድም ያደርጋል፤

፲፫) የህጋዊ ካዳስተር ቴክኖሎጂ ሥርዓትንና የኔትዎርክ መሠረተ ልማትን ያለማል፤ እንዲለማ ያደርጋል፤ ያሻሽላል፤ወቅታዊ ያደርጋል፤ያስተዳድራል፤

፲፬) ህጋዊ ካዳስተር ማስረጃዎችን ህግ በሚፈቅደው መሠረት ለህዝብ ክፍት እንዲሆን ያደርጋል፤

፲፭) የመሬት ይዞታ ሰርቨይንግን በስታንዳርድ ላይ በመመስረት ተቀባይነት ያለው የወሰን ልዩነት ላይ ይወስናል፤

6) Perform the request of change of title deed and holding usage of urban lands according to the law; notify to the concerned body; follow-up its implementation;

7) Implement the system prepared for the registration of urban land differently; cause to be implemented;

8) Screen and organize the current urban land holding data; provide to the concerned body; take legal measure where there prevail limitation; cause same to be taken;

9) Depending on the standard, provide holding right evidence regarding the unique code or number of a holding of a place registered in lawful cadastre and its boundary is clearly known;

10) Register data of land and property related with land holding with digital and papers; administer; develop; serve as a center of data of urban land holding; consolidate; provide to the concerned body;

11) Organize data of urban cadaster information system; prepare the base map and cadastre map; cause it to be prepared; administer; renew;

12) Conduct regular safety supervision on the legal cadaster information system of urban with the concerned body; identify the existing problem, take or cause to be taken corrective measures;

13) Develop legal cadastre technology system and network infrastructure development; cause it to be developed; modify; cause up to dated; administer;

14) Make the data of legal cadastre to be open to the public in accordance with the law permits;

15) Decide on the acceptable differentiation boundary Depending on the standard of surveying of land holdings;

16) Tuqaalee too'annoo lafaa (Ground control point) sadarkaa lammaffaa fi sadaffaa qiyyaasa kaadaastaraatiif gargaaruuf dhaabaman akkaataa barbaachisummaa isaatti ni baay'isa; sadarkaa fi qulqullina isaa eeggate daangaa magaalaa keessatti ni dhaaba; akka dhaabbatu ni taasisa; ni bulcha;

17) Sirni wal-jijjiirraa ragaa yookiin odeeffannoo itti fayyadamaa fi galmeessa qabiyyee lafaa magaalota naannoo jidduutti akka diriiru ni taasisa; akkaataa seeraatiin qaama birootiif ni kenna;

